# RICHARD WURMBRAND

# ለክርስቶስ ተሰቃየሁ



ትርጉም
ተስፋዬ መስፍን

# ለክርስቶስ ተሰቃየሁ

Richard Wurmbrand

ይህ መጽሐፍ፣ ለእምነታቸው ለተሰደዱ፣ ከቤት ከንብረታቸው ለተፈናቀሉ፣ በቆሙለት ዓላማ ምክንያት የደረጃ ዕድገትን፣ ከፍተኛ ትምህርት የማግኘት ዕድልን ለተነፈጉ፣ የተለያየ ስቃይና መከራ ለተቀበሉ፣ ከዚያም በላይ ክቡር ሕይወታቸውን መስዋዕት ላደረጉ ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች መታሰቢያ እንዲሆን ተሰጥቶአል።

RICHARD WURMBRANAD
TRANSLATED — BY TESFAYE MESFIN

# ስለ ደራሲው

ሪቻርድ ውምብራንድ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ወንጌላዊ ሲሆኑ ፣ በተወለዱባት አገር ሩማንያ ለእምነታቸው ለሥራ አራት ዓመት ታስረዋል ፤ የተለያየ መከራም ተቀብለዋል ። ውምብራንድ በመላው ዓለም የታወቁ ደራሲ ፣ ክርስቲያን መሪና ምሑር ናቸው ።

በ1945 ዓ.ም ኮሚኒስቶች ሩማንያን በያዙበትና ዓላማቸውን መፈጸሚያ ለማድረግ ቤተ ክርስቲያን ከቁጥጥራቸው ሥር ለማዋል ያደረጉትን ሙከራ በመቃወም ውምብራንድ በባርነት ቀንበር ሥር ለወደቀው ሕዝባቸው ፣ እንዲሁም ለወራሪው የሩስያ ጦር የኅቡዕ ወንጌልን የማስፋፋት አገልግሎት ጀመሩ ። በኋላም በ1948 እሳቸውና ባለቤታቸው ሣቢና ታሠሩ ፤ ሣቢና የሦስት ዓመት ነፃ የክባድ ሥራ አገልግሎት ሲፈረድባቸው ፤ ሪቻርድ ግን ስቃይና መከራ ከሚያደርሱባቸው ኮሚኒስቶች በቀር ማንንም ሣያዩ ሦስት ዓመት በእሥራት እንዲማቀቁ ዕጣቸው ሆነ ። ከሦስት ዓመት በኋላ ግን ሌሎች ስፍር ቁጥር ከሌላቸው እሥረኞች ጋር በተጨማሪ አምስት ዓመት ተንገላቱ ።

ዓለም አቀፍ ታዋቂነት ያላቸው ክርስቲያን መሪ እንደመሆናቸው መጠን ዲፕሎማቶችና የውጭ አገር ኤምባሲዎች ስላሉበት ሁኔታ ለኮሚኒስቱ መንግሥት ጥያቄ ቢያቀርቡም ፣ የተሰጣቸው መልስ ግን "ከሩማንያ ጠፍቶ ሄዶአል" የሚል ነበር ። "ከእሥር ቤት በቀርቡ የወጣን ነን" በሚል ሽፋን ራሣቸውን የሰወሩ የደኅንነት አባሎችም ወደ ባለቤታቸው በመሄድ ውምብራንድ እንደሞቱና በቀብራቸውም ሥነ ሥርአት ላይ እንደተገኙ ነገሩዋቸው ። ከስምንት ዓመት በኋላ ከእሥር ተፈቱ ፤ እርሣቸው ግን በኅቡዕ ወንጌልን ተሰብከ ከነበረችው ቤተ ክርስቲያን ጋር ማገልገል ጀመሩ ። ይሁን እንጂ ከሁለት ዓመት በኋላ እንደገና ታሠሩና ሃያ አምስት ዓመት ተፈረደባቸው ።

በ1964 የሰብዓዊ መብት ተቆርቋሪ ቡድን ባደረገው ጥረት

እንደገና ተፈትተው አሁንም በኅቡዕ ወንጌልን ማስተማልረ ጀመሩ። ሶስተኛ ጊዜ እንዳይታሠሩ በመፍራት በኖርዌይ የነበሩ ክርስቲያኖች ከባለሥልጣኖች ጋር በመደራደር ከሩማንያ እንዲወጡ ተደረገ። ጊዜው ኮሚኒስታዊው መንግሥት የፖለቲካ እሥረኞችን "የሚሸጥበት" ወቀት ነበር። አንድ እሥረኛ ነፃ እንዲወጣ የሚከፈልለት መደበኛ ዋጋ 1900 የአሜሪካ ዶላር ሲሆን፣ ለውምብራንድ የተጠየቀው ቤዛ ክፍያ ግን 10,000 የአሜሪካ ዶላር ነበር።

በ1966 ግንቦት ወር በዋሽንግተን ከተማ በአንድ የሴኔቶች ንዑስ ኮሚቴ ፊት ቀርበው በአካላቸው ላይ በተደረገው ምርመራ አሥራ ስምንት የአጥንት ስብራት እና የግርፋት ቁስል እንደደረሰባቸው ተረጋግጦአል ። ይህም ፣ ታሪካቸው በአሜሪካ ፣ በአውሮፓና በእስያ በተለያዩ የዜና ማሠራጫዎች እንዲዳረስ ምክንያት ሆነ ። በ1966 ደግሞ በኮሚኒስት መሪዎች እንዲገደሉ መወሰኑ ሩማንያ ካሉ ወዳጆቻቸው ደብዳቤ ደረሣቸው ። የተለያየ ማስፈራራትና ዛቻ ቢደርስባቸውም ውምብራንድ ግን ጸጥ አላሉም ። ውምብራንድ "የኅቡዕ ቤተ ክርስቲያን ድምፅ" በመባል ይታወቃሉ ። አንዳንዶች "ሕያው ሰማዕት" ሲሏቸው ሌሎች ደግሞ "የኮሚኒስት አገሮች ጳውሎስ" ይሏቸዋል ።

# ምዕራፍ አንድ

## ካለማመን ወደ ማመን ፤

አባቴም ሆኑ እናቴ ሃይማኖተኞች ስላልነበሩ በልጅነቴ ምንም መንፈሳዊ ትምህርት አልተሰጠኝም ። እንዲያውም ገና በአሥራ አራት አመቴ "እግዚአብሔር የለም" የምል ነበርሁ ፤ ይህም ያሳለፍኩት ምሬት የተሞላበት የልጅነት ጊዜዬ ውጤት ሊሆን ይችላል ። እናትና አባቴ ገና ልጅ እያለሁ ነበር የሞቱት ። አንደኛው የዓለም ጦርነት ላስከተለው ችግርና መከራ ተጋልጬአለሁ ። ልክ ዛሬ ኮሚኒስት ወጣቶች እንደሆኑት ሁሉ እኔም በአሥራ አራት አመቴ እግዚአብሔር ላለመኖሩ እርግጠኛ ነበርሁ ። የተለያዩ የክህደት መፃሕፍትን አንብቤአለሁ ። 'እግዚአብሔር' ወይም 'ክርስቶስ' የሚሉ ቃላቶቹ ራሳቸው ያስጠሉኛል ፤ ሃይማኖታዊ አስተሳሰብ የሰው ልጅ አእምሮ ደካማ ጐን መስለው ይታዩኝ ነበር ። እንግዲህ በሃይማኖት ላይ ይህን የመሰለ ጥላቻ ይዤ ነበር ያደግሁት ፤

ምንም እንኳ ሃይማኖት የለሽ ብሆንም በቃል ልገልጸው የማልችለው ስሜት ወደ ቤተ ክርስቲያኖች እንድገባ ይገፋፋኛል ። እንዲያውም ወደ ውስጥ ጐራ ሳልል በቤተ ክርስቲያን በኩል ያለፍኩበት ጊዜ ቢኖር ጥቂት ነው ። ይሁን እንጂ ፥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚደረጉት ነገሮች ግን ግልጽ አልሆኑልኝም ። ስብከቶችን አድምጬአለሁ ፤ ግን ልቤ ሊደርሱ አልቻሉም ። "እግዚአብሔር አምላክ ስለሆነ ልትታዘዘው ይገባል" የሚለው ሃሣብ ያናድደኛል ፤ ስለ እግዚአብሔር ያለኝን የተሣሣተ አስተሳሰብ እጠላዋለሁ ። በሌላ በኩል ደግሞ እኔን የሚወደኝና የሚንከባከብልኝ አዛኝ ልብ በዚህ ግዙፍ ፍጥረተ ዓለም ውስጥ ቢኖር እመኛለሁ ። በልጅነቴም ሆነ በወጣትነቴ ደስ የተሰኘሁባቸው ቀኖች በጣት የሚቆጠሩ ናቸው ። ታዲያ ፥ የሚወደኝና የሚያፈቅረኝ አዛኝ ልብ እንዲኖር ብመኝ ምን ያስደንቃል?

እግዚአብሔር እንደሌለ አውቃለሁ ፤ ግን የሚወደኝ የፍቅር አምላክ ባለመኖሩ ደግሞ አዝናለሁ ። አንድ ቀን ግን በውስጤ የነበረውን መንፈሳዊ ውጥረት ያረግብልኝ እንደሆነ በማለት ወደ ካቶሊክ ቤተ

ክርስቲያን ገባሁ ። ሰዎች ተንበርክከው ምንነቱን የማላውቀው ቃላት ይናገራሉ ፣ ምን እንደሚሉ ለመስማትና በሕይወቴ ሊያመጣ የሚችለውን ለውጥ ለማየት ወደ ሰዎች ጠጋ ብዬ ተንበረከክሁ ። "ጸጋን የተሞላሽ ማርያም ሆይ" እያሉ ነበር የሚፀልዩት ። ቃላቱን ደጋግሜ አነበነብኳ ቸው፤ ፊት ለፊታችን የነበረውን የማርያም ምስል ትክ ብዬ ተመለከት ኩት ። ምንም አዲስ ነገር አልተፈጠረም ። በጣም አዘንሁ ።

ምንም እንኳ እግዚአብሔር ላለመኖሩ እርግጠኛ ብሆንም አንድ ቀን "እግዚአቤሔር ሆይ ላለመኖርህ እርግጠኛ ነኝ ምናልባት ካለህ ግን ራስህን ግለጽልኝ" በማለት ፀለይኩ ። የእግዚአብሔርን ሕልውና አለመቀበሌ ሰላም ሊሰጠኝ አልቻለም ።

በኋላ እንደተረዳሁት ግን በእንዲህ አይነት ውስጣዊ ውጥረት በነበርኩበት ወቅት በተራራማው ሩማንያ ወረዳ ይኖር የነበረ አንድ ሽማግሌ አይሁዳዊ አናጢ "በዚህ ምድር አገልግየሃለሁ ፣ ስለዚህም በሰማይ የሚገባኝን እንደምትሰጠኝ ሁሉ በዚህ ምድርም የአገልግሎቴን ዋጋ እንድትሰጠኝ እፈልጋለሁ ፤ ኢየሱስ ራሱም የተገኘው ከአይሁድ ሕዝብ ነው ፤ ከመሞቴ በፊት አንድ አይሁዳዊ ሰው በአንተ እንዲያምን እንዳደርግ እርዳኝ ። አርጅቻለሁ ፣ በዚያም ላይ ሕመምተኛ ነኝ ወደ አካባቢው ሄጄ ስለ ክርስቶስ የምመሰክርለትን አይሁዳዊ ማግኘት አልችልም ። በሰፈራችንም አንድ አይሁዳዊ እንኳ የለም ። ወዳለሁበት ስፍራ አይሁዳዊ ሰው ላክልኝ ፣ እኔም በክርስቶስ እንዲያምን ልመስክር ለት" በማለት ይፀልይ ነበር ።

አንድ ቀን ምንም እንኳ ይህ ነው የምለው ጉዳይ ባይኖረኝም ወደዚያ ሽማግሌው አይሁዳዊ ወደሚኖርበት መንደር ሄድሁ ። በዚያን ወቅት ሩማንያ ከአሥራ ሁለት ሺህ መንደሮች በላይ ቢኖራትም ፣ እኔ ግን በቀጥታ ወደዚያ መንደር ነበር የሄድሁት ። አይሁዳዊ መሆኔን ካረጋገጠ በኋላ አንድ ወጣት ልጃገረድን በሚቀርብበት ዓይነት ነበር የቀረበኝ ። እኔን ማግኘቱ የፀሎቶቹ መልስ እንደሆነ ስላወቀ ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ሰጠኝ። ከዚያ በፊት መጽሐፍ ቅዱስን አንብቤአለሁ ፤ ይህ ሽማግሌ የሰጠኝ መጽሐፍ ቅዱስ ግን ከሌሎች የተለየ ሆነብኝ ። ሽማግሌው በኋላ እንደነገረኝ መጽሐፍ ቅዱሱን ከሰጠኝ በኋላ እርሱና ባለቤቱ ጌታን እንድንቀበል የተወሰኑ ሰዓቶች ፀልየዋል ። የሰጠኝ መጽሐፍ ቅዱስ

የተፃፈው በቀለም ሣይሆን ፣ ነበልባላዊ በሆነ ፍቅር መሰለኝ ። ይህም የፀሎት ውጤት ነው ። በዓመፅ የተሞላውን ሕይወቴን ከኢየሱስ ሕይወት ጋር ማነፃጸረው ፣ ጥላቻዬንም ከኢየሱስ ፍቅር ጋር ሳወዳድርው ፣ አምነሬ ማልቀስ ጀመርኩ ። እርሱ ግን ያን ያህል የረከስኩ ብሆንም በፍቅር ተቀበለኝ ።

እኔ በጌታ ካመንሁ በኋላ ባለቤቴም አመነች ። እርሷም ሌሎችን ወደ ክርስቶስ አመጣች ። እነርሱም ሌሎችን ወደ ክርስቶስ በማምጣታቸው በቁጥር አደግን ። ስለዚህም የመጀመሪያው ሉተራውያን ክርስቲያኖች ማኅበረ ምዕመናን ተመሠረተ ።

ወዲያው ናዚዎች ሥልጣን በመያዛቸው በብዙ መከራ ማለፍ ነበረብን ። ናዚዝም አይሁዳውያንን ብቻ ሣይሆን በፕሮቴስታንት ክርስቲያኖችም ላይ ከፍተኛ ጥላቻ የነበረው አምባ–ገነናዊ ሥርዓት ነው ፣

የዚያ ማኅበረ ምዕመናን መሥራች እንደመሆኔ መጠን በሕጋዊ መንገድ ሥልጣነ–ክህነትን (ኦርዲኒሽን) ከመቀበሌና ሰፋ ላለ አገልግሎት ከመዘጋጀቴ በፊት ቤተ ክርስቲያኑን የምመራው እኔ ነበርሁ ። እኔም ሆንሁ ባለቤቴ በናዚዎች በተደጋጋሚ ታስረናል ፣ ተደብድበናል ፤ በባለሥልጣኖች ፊትም ቀርበናል ፤ በናዚዎች ዘመን የታየው ሽብር በጣም ከፉ ነበር ። በኮሚኒስቶች ዘመን ካየነው መከራ ጋር ስናስተያየው ግን አነስተኛ ሆኖ ነበር ያገኘነው ። አይሁዳዊ መሆኑን ካወቁ እንዳይገድሉት በመፍራት የልጄ የሚኻይን ስም ለወጥንላት ።

ከናዚዎች አንድ ነገር ተምረናል ፤ ይኸውም የሰው ልጅ መንፈስ በእግዚአብሐር ኃይል ከታገዘ ፣ ማንኛውንም መከራና ስቃይ ሊቋቋም መቻሉን ነው ። በምስጢር የወንጌልን እውነት የማስፋፋቱንም ዘዴ የተማርነው ከናዚዎች ነው ። ይኸውም ወደፊት በሚነሣው አስከፊ ሥርዓት ውስጥ እንዴት ወንጌልን እንደምናስተምር አዘጋጅቶናል ።

## አገልግሎቴ በሩስያውያን መካከል

ለብዙ ጊዜ 'እግዚአብሔር የለም' ማለቴ ቆጭቶኛል ፤ ስለዚህም በእግዚአብሔር ካመንኩበት ጊዜ ጀምሮ ሰዎችን ወደዚህ እውነት ለማምጣት ቆርጬ ተነስቼአለሁ ። በሩሲያውያን መካከል ወንጌልን ለመስበክ የተነሣሁትም በዚህ ምክንያት ነው ። ሩስያውያን ገና

ከልጅነታቸው ጀምሮ እግዚአብሔር የለም በሚል ትምህርት ተኮትኩተው ያደጉ ናቸው ፤ ለሩስያውያን ወንጌልን የመስበክ ናፍቆቴ ተፈጸመ ፡ በሩማንያ ውስጥ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሩስያውያን የጦር እሥረኞች ነበሩ።

ሥራው ስሜትን የሚቀሰቅስ ነበር ፤ ለመጀሪያ ጊዜ ለሩስያውያን ወንጌልን ስሰብክ የተፈጠረውን ሁኔታ አልረሣውም ። አንድ ጊዜ ከአንድ ሩሲያዊ የጦር እሥረኛ ጋር እነጋገር ነበር ፤ እንደነገረኝ መሐንዲስ ነው ። በእግዚአብሔር ያምን እንደሆነ ጠየቅሁት ። "አላምንም" ቢለኝ እንኳ ግድ አይኖረኝም ። ምክንያቱም ማንም ሰው ቢሆን የማመን ወይም ያለማመን መብት አለው ። በእግዚአብሔር ያምን እንደሆነ ስጠይቀው ቦዘዝ ባሉ አይኖቹ ተመለከተኝና "እንዲህ ያለ ወታደራዊ መመሪያ አልተሰጠኝም ፤ ቢኖረኝ ኖሮ ግን አምን ነበር" አለኝ ።

በሁኔታው በጣም ከማዘኔ የተነሣ አይኖቼ እንባ አቀረሩ ። ይህ አብሮኝ ያለው ሰው እግዚአብሔር ለሰዎች ሁሉ የሰጠውን ለራስ የማሰብን ፤ ለራስ የመወሰንን ፤ በጠቅላላው ሌላውን ሣይሆን ራስን የመሆንን ፀጋ ተነፍጐአል ። ይህ ደግሞ እግዚአብሔር ለሰዎች ካደላቸው ታላላቅ ስጦታዎች አንዱ ነው ። ይህ ሰው የሚያምነውም ሆነ የማያምነው ኮሚኒስቶች በሚሰጡት መመሪያ መሠረት በመሆኑ ለራሱ መወሰን አይችልም ። ይህ ነው እንግዲህ ኮሚኒዝም በሰዎች አእምሮ ሲሰለጥን የሚከተለው ውጤት ። እነዚህ ሰዎች በራሣቸው ሰብዕና እንዲመሩ በእግዚአብሔር ማመን አለባቸው ፤ ለሩስያውያን ወንጌልን የመስበክ ፍላጐቴ ከምን ጊዜውም ይልቅ ተነሣሣ ።

ለሩሲያውያን ወንጌልን ለመስበክ ወደ ሞስኮ መሄድ አልነበረብኝም ። ከነሐሴ 23/1944 ጀምሮ ወደ አንድ ሚሊዮን የሚደርስ የሩሲያ ሠራዊት ወደ ሀገራችን እየጐረፈ ነው ። ጥቂት ቆይቶ ደግሞ ኮሚኒስቶች ሥልጣን ያዙ ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ይህ ነው የማይባል ሥቃይና መከራ በሩማንያ መታየት ጀመረ ። ናዚዎችን ያደረሱብንን ስቃይ ሳስበው ቀላል መስሎ ታየኝ ።

ሩማንያ በዚያን ጊዜ አሥራ ዘጠኝ ሚሊዮን ዜጐች ሲኖራት ፡ የኮሚኒስት አባሎች ግን አሥር ሺህ ብቻ ነበሩ ። በጊዜው የሶቪየት የውጪ ጉዳይ ዋና ፀሐፊ የነበረው ቪሺንስኪ ተወዳጅ ወደነበረው ንጉሣችን ቀዳማዊ ሚካኤል ቢሮ በመግባት በቡጢ ጠረጴዛውን እየደበ

ደበ "በመንግሥታዊው መዋቅር ውስጥ ኮሚኒስቶች ሥልጣን እንዲኖራቸው መሾም አለብህ" በማለት አስፈራራ ። የጦርም ሆነ የፖሊስ ሠራዊታችን ፈራርሶአል ። ሁሉም ቢጠላቸውም ኮሚኒስቶች በኃይል ሥልጣን ያዙ ። ለዚህም በዘመኑ የነበሩ የአሜሪካና የእንግሊዝ መሪዎች እጅ ነበረበት ።

ሰዎች በግላቸው ብቻ ሣይሆን ፡ በሕዝብ ወይም በመንግሥት ደረጃ ለሚያደርጉት ኃጢአት ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ተጠያቂ ናቸው ። በመሆኑም አሜሪካም ሆነች እንግሊዝ በባርነት ቀንበር ሥር ለወደቁት ሕዝቦች ዕጣ ከተጠያቂነት አያመልጡም ። አሜሪካኖችም ሣያውቁት አንዳንድ አገሮች በሶቪየቶች እጅ እንዲወደቁ ማድረጋቸውን መዘንጋት የለባቸውም ። ስለዚህም አሜሪካኖች እነዚህ ምርኮኞች ወደ ክርስቶስ ወንጌል ብርሃን እንዲመጡ የሚቻላቸውን ሁሉ ማድረግ ይኖርባቸዋል ።

## .. ማታለል– የፍቅ አነጋገር ሲመስል

ኮሚኒስቶች ሥልጣን ከያዙ በኋላ በተለመደ ማጭበርበሪያ ቃላቸው ቤተ ክርስቲያንን ማሳሳት ጀመሩ ። አንዳንድ ጊዜ የማታለልን አነጋገርና የፍቅርን አነጋገር መለየት ያዳግታል ። አንዲት ልጃገረድን ለማግባት የሚፈልግም ሆነ ከተጠቀመባት በኋላ ዞር ብሎ እንኳ የማያያት ወጣት ሁለቱም ልጃገረዲቱን የሚቀርቧት "እወድሻለሁ" በሚል ቃል ነው ። እየሱስ ግን በፍቅርና በማታለል ፡ በበጐችና የበግን ለምድ በደረቡ ተኩላዎች መካከል ያለውን ልዩነት ጠንቅቀን እንድንረዳ አስጠንቅቆናል።

ኮሚኒስቶች ሥልጣንን በያዙበት ወቅት በሺህ የሚቆጠሩ ቀሣውስት ፣ ፖስተሮች ፣ ጳጳሣትና የወንጌል መልእክተኞች ትክክለኛ ማንነታቸውን አልተረዱም ነበር ።

ኮሚኒስቶች ከመላው የሃይማኖት ክፍል የተውጣጡ አራት ሺህ መሪዎችን ፓርላማ ውስጥ ሰብስበው ንግግር አደረጉላቸው ። ይህን ጉባኤ በሊቀ መንበርነት እንዲመራ ጆሴፍ ስታሊንን የመረጡት ራሳቸው ሃይማኖተኞቹ ነበሩ ። በሌላ በኩል ደግሞ ይኸው ስታሊን "የዓለም አቀፍ አምላክ የለሽ እንቅስቃሴ" ፕሬዚዳንትና ብዙ ክርስቲያኖችን በግፍ ያስጨፈጨፈ መሪ ነበር ። ጳጳሳቱ ተራ በተራ እየተነሱ ኮሚኒዝምና

ክርስትና ተመሣሣይ በመሆናቸው አብረው መሥራት ይችላሉ ፤ በማለት ተናገሩ ። አንዱ ቄስ ከሌላው ቄስ በመቀጠል ለኮሚኒዝም የምሥጋና ቃላት ያዥጐደጉዱ ጀመር ። እንዲያውም ለቤተ ክርስቲያን የወርቃማ ዘመን ምዕራፍ የተከፈላት መስሎ ነበር የታየው ።

እኔና ባለቤቴም በስብሰባው ተገኝተን ነበርን ። ጐኔ ተቀምጣ ሁኔታውን ሁሉ በአንክሮ ትከታተል የነበረችው ባለቤቴ "ሪቻርድ እነዚህ ነውረኞች በክርስቶስ ፊት እየተፉበት ነው ፤ ተነሣና ምራቃቸውን ጥረግለት" አለችኝ ። እኔም "የምትይኝን ካደረግሁ ባል አልባ ሴት እንደምትሆኚ እወቂው" አልኳት ። እርሷም "ፈሪ ባል ከሚኖረኝ ቢቀር ይሻለኛል" አለችኝ ።

ከዚያ በኋላ ከመቀመጫዬ ተነሣሁና ፣ የአያሌ ክርስቲያኖችን ሕይወት ያጠፉ ነፍሰ ገዳዮችን ሣይሆን እግዚአብሔርን በማመስገን ተናገርሁ ። የመጀመሪያ ታማኝነታችን ለእርሱ መሆን እንዳለበትም አስታወቅሁ ። ስብሰባው በመላው አገሪቱ በሬዲዮ ይተላለፍ ስለነበር ፣ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች አደመጡት ። እኔን ግን ዋጋ አስከፍሎኛል ።

እኔ እቀድም ፣ እኔ እቀድም በመባባል የፕሮቴስታንትና የኦርቶዶክስ መሪዎች እየተነሱ ለኮሚኒዝም ያለቻውን ድጋፍ ይገልጡ ጀመር ። አንድ የኦርቶዶክስ ጳጳስ የኮሚኒዝም ዓርማ የሆነውን ማጭድና መዶሻ በልብሱ ላይ አስጠልፎ "ከዛሬ ጀምሮ ብፁዕ አባታችን ፣ ብቻ ሣይሆን ጓድ አባታችን" መባል እንዳለበት ተናገረ ። ሬዚታ በሚባል ስፍራ በአንድ የባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን ስብሰባ ተገኝቼ ነበር ። ቤተ ክርስቲያኑ ላይ ቀይ ባንዲራ ይውለበለባል ፤ ሁሉም ቆመው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሶቭዬትን ሕዝብ መዝሙር እየዘመሩ ነበር ። እንዲያውም ይግረማችሁ ብሎ የባፕቲስቶቹ ፕሬዚዳንት "ስታሊን የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ፈጻሚ እንጂ ምንም አላጠፋም" ብሎ ተናገረ ። 'ታላቅ የመጽሐፍ ቅዱስ መምህር ነው' በማለት ያወድሰው ያዘ። እንደ እነ ፓትራስኩ እና ሮዚያኖን የመሳሰሉ ቀሳውስት ደግሞ የሕዝብ ደኅንነት አባል ሆኑ ። አንድ በሉተራውያን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከፍተኛ ሥልጣን የነበረው ሰው በሥነ መለኮታዊ ሰሚናር ውስጥ "እግዚአብሔር በሶስት ሰዎች አማካይነት ፈቃዱን ለዓለም አሣውቆአል፤ እነርሱም ሙሴ ፣ ኢየሱስና ስታሊን ናቸው ። የመጨረሻው ግን ከሁሉም ይበልጣል" ብሎ ያስተምር ጀመር ።

ይሁን እንጂ በጣም የምወዳቸው እውነተኞቹ ባፕቲስቶች ለክርስ ቶስ ያላቸውን ታማኝነት አስመስክረዋል ። ስለዚህም ተሰቃይተዋል ። ነገር ግን የቤተ ክርስቲያን መሪ እንዲሆኑ "ፓስተሮችን" የሚመርጡላ ቸው ራሳቸው ኮሚኒስቶቹ በመሆናቸው ምንም ማድረግ አልቻሉም ።

ክርስቶስን ሳይሆን ኮሚኒዝምን የሚያገለግሉ መሪዎች ሊተባበሩዋ ቸው ፈቃደኛ ያልሆኑትን እውነተኛ ምዕመናን አሣልፈው መስጠት ጀመሩ ።

ከሩስያ አብዮት በኋላ ሩሲያውያን ክርስቲያኖች በኅቡዕ መሥራት እንደጀመሩ ሁሉ ፣ ከተፈጠረው ችግር የተነሣ የሩማንያ ክርስቲያኖችም በኅቡዕ ወንጌልን እንዲሰብኩ ተገደዱ ። ይቺ በኅቡዕ የምትሠራ ቤተ ክርስቲያን ወንጌልን ታስፋፋለች ፤ ወጣቶች በክርስቶስ እንዲያምኑ ታደርጋለች ፤ ይህንን ደግሞ ኮሚኒስቶቹ አልወደዱልንም ። ክርስቲያን ያልናቸው መሪዎችም ከእነርሱ ጋር ተስማሙ ።

እኔም በኅቡዕ ወንጌልን ከሚያስፋፉ አንዱ ነበርሁ ። የኖርዌጅያንሉ ተራን ሚሲዮን ፓስተርና በሩማንያ የዓለም አብያተ ክርስቲያን ምክር ቤት ተወካይ ስለነበርኩ በኅቡዕ ለምሠራው የወንጌል አገልግሎት ሽፋን ሆኖልኛል ። (በዚያን ጊዜ ይህ ድርጅት በሩማንያ ውስጥ የእርዳታ አገልግሎት ብቻ ነበር የሚሰጠው) ከነበረኝ የሥራ ፀባይ የተነሣ ከባለሥልጣኖቹ ጋር መልካም ግንኙነት ነበረኝ ። ስለሆነም በኅቡዕ ስለምሰጠው መንፈሳዊ አገልግሎት አያውቁም ።

ይህም ሁለት ክፍሎች ነበሩት ።

የመጀመሪያው በሀገራችን ለነበሩ አንድ ሚሊዮን ወታደሮች ወንጌልን መስበክ ሲሆን ፣ ሁለተኛው ደግሞ በሩማንያውያን መካከል በኅቡዕ ወንጌልን ማስፋፋት ናቸው ።

## የምሥራቹን ቃል የተጠሙት ሩሲያውያን

በበኩሌ ለሩስያውያን ወንጌልን መስበክ በጣም ነው የሚያረካኝ ። ለተለያየ አገር ሰዎች ወንጌልን ሰብኬአለሁ ፤ ይሁን እንጂ እንደሩሲያው ያን የወንጌልን እውነት የሚቀበል ሕዝብ አልገጠመኝም ። ነፍሳቸው ለመንፈሳዊ እውነት ተጠምታለች ።

ጓደኛዬ የሆነ አርቶዶክሳዊ ቄስ ስልክ ደወለና ስለ መንፈሳዊ ጉዳይ ሊያነጋግረው ወደ ቤቱ መጥቶ ስለነበር ሩሲያዊ ባለሥልጣን ነገረኝ ።

ጓደኛዬ የሩሲያ ቋንቋ አያውቅም ፤ የሩሲያ ቋንቋ እንደምችል ስለሚያውቅ ግን ለዚህ ሰው አድራሻዬን ሰጥቶ ወደ እኔ ላከው ። ወደ እኔ የመጣው በሁለተኛው ቀን ነበር ። ይህ ሰው እግዚአብሔርን በጣም ይወዳል ። ስለ እግዚአብሔር ብዙ ለማወቅ ከፍተኛ ፍላጐት አለው ፤ ይሁን እንጂ የራሱ መጽሐፍ ቅዱስ እንኳ የለውም ። በሩስያ ውስጥ ብዙ ቤተ ክርስቲያኖች ተዘግተው ስለነበር ፣ በማንኛው አምልኮ ስፍራ ተገኝቶ አያውቅም ። ሃይማኖታዊ ትምህርትም የለውም ፤ ስለ እርሱ ምንም ሳያውቅ ነበር እግዚአብሔርን የሚወድደው ።

የተራራውን ስብከትና ኢየሱስ የተናገራቸውን ምሣሌዎች አነበብኩለት ። በታላቅ ደስታ ተመስጦ ነበር ያደመጠኝ ። ለመሆኑ ይህን ክርስቶስን ሳላውቅ እንዴት ይህን ያህል ዘመን ኖርሁ? አለ ። ክርስቶስን በማመን የሚገኘውን ደስታ በሰዎች ሕይወት ለመጀመሪያ ጊዜ ያየሁት ያን'ጊዜ ነበር ።

ሳላውቀው ግን አንድ ስህተት ሠራሁ ፣ የሰውየውን ልብ ሳላዘጋጅ ክርስቶስ ስለደረሰበት መከራና በመስቀል ላይ መሞቱን የሚያወሳውን ክፍል አነበብኩለት ፤ እንዲህ ያለ ነገር ይሆናል ብሎ አልጠበቀም ፣ ክርስቶስ ስለ ደረሰበት መከራና በመጨረሻም ተሰቅሎ እንደ ሞተ ሳነብለት ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ ። በክርስቶስ አምኖ ነበር ፤ አሁን ግን ይህ ያመነበት አዳኝ እንደሞተ ተነገረው ።

ክርስቲያን ከመሆኔም በላይ ፓስተር ነኝ ። ይሁን እንጂ የኢየሱስን መከራ እና ስቃይ እንደዚህ ሰው አይቼው አላውቅም ። ትኩር ብዬ ስመለከተው በመስቀሉ አጠገብ ሆና ፣ እንዲሁም እየሱስ በተቀበረበት መቃብር ስታለቅስ የነበረችውን ማርያም መግደላዊትን አሳሰበኝ ። ወዲያውኑ ኢየሱስ ሞትን ድል አድርጐ እንደተነሣ ስነግረው "በርግጥም ሕያው ! ነው በእርግጥም ሕያው ነው!" እያለ ይፈነድቅ ጀመር ።

እንፀልይ አልኩትና ሁለታችንም ለፀሎት ተንበረከክን ፣ ተንበርክከን በነበረበት ጊዜ "እግዚአብሔር ሆይ ፣ እኔ አንተን ብሆን ኖሮ ፣ በደልህን ይቅር አልልህም ነበር ፤ አንተ ግን በእርግጥ መልካም አምላክ ነህ በፍጹም ልቤ እወድሃለሁ" እያለ ይፀልይ ነበር ።

እንዲህ አይነቱን ቅንነትና ፍጹም የዋህነት የተሞላበትን ፀሎት የሰማይ መላእክት እንኳ የሚሠሩትን ሥራ አቋርጠው በጽሞና እንዳደመጡት አስባለሁ ።

አንድ ጊዜ ደግሞ አንድ ሩስያዊ ሻምበልና አንዲት ከፍተኛ ባለሥልጣን በአንድ ሱቅ ውስጥ አገኘሁ ። ዕቃ ሣይመርጡ ያገኙትን ነበር የሚገዙት ፤ ነጋዴው ምንም የሩስያ ቋንቋ ስለማይችል አስተረጉምላቸው ጀመር ። ወዲያውኑ ተግባባን ፤ ምሣ ጋበዝኳቸውና ወደቤት ይዤአቸው ሄድሁ ። ምሣ ቀርቦ እያለ "ያላችሁት ክርስቲያን ቤት ነው ከምግብ በፊት የመፀለይ ልምድ አለን" አልኳቸው ። የገበታ ፀሎቱን የፀለይኩት በሩስያ ቋንቋ ነበር ። እንግዶቼ በዚህ ሁኔታ አልተደሰቱም ። ስለ እግዚአብሔር ፣ ስለ ክርስቶስ እና ስለመጽሐፍ ቅዱስ በተከታታይ ይጠይቁኝ ነበር ። ምንም የሚያውቁት አልነበረም ።

ከእነርሱ ጋር ስለመንፈሳዊ ነገር መነጋገር ቀላል አልነበረም ። መቶ በጐች ስለ ነበሩትና አንዲቱ በግ ብትጠፋበት ፍለጋ ስለሄደው ሰው ምሣሌ ከመጽሐፍ ቅዱስ አነበብኩላቸው ። ሊገባቸው ስላልቻለ "እንዴት አንድ ሰው ብቻውን የመቶ በጐች ባለቤት ሊሆን ቻለ ..? የኅብረት እርሻ ማኅበሩ እንዴት ሣይወስድበት ቀረ ..?"በማለት ጠየቁኝ ።

እኔም ይህን ምሣሌ የተናገረው ኢየሱስ ንጉስ'ኮ ነው ። አልኳቸው ። እነርሱ ግን "እንደምናውቀው ንጉሶች ሁሉ ጨቋኞች ናቸው ፤ ይህ እየሱስ የምትለው ንጉስ ከሆነ ከጨቋኞቹ አንዱ መሆን አለበት" የሚል መልስ ነበር የሰጡኝ ። ስለ ወይኑ አትክልት ሠራተኞች ምሣሌ ስነግራቸውም "የወይኑ አትክልት ሠራተኞች ባለቤቱ ላይ ማመፃቸውን ደግ አድርገዋል ፤ እንደ እውነቱ ከሆነ የዚያ ወይን አትክልት ባለቤት መሆን የነበረበት የኅብረት እርሻ ማኅበሩ ነው" በማለት መለሱልኝ ። ለእነርሱ ማንኛውም ነገር አዲስ ነው ። ስለ ኢየሱስ ልደት ስነግራቸው "እሃ ! ማርያም የእግዚአብሔር ሚስት ናት ማለት ነው?" የሚል ጥያቄ አቀረቡልኝ ። ይህ አባባል ለብዙ ክርስቲያኖች ስድብ መስሎ ሊታይ ይችላል ፤ ከእነዚህና ከሌሎችም ብዙ ኮሚኒስቶች ጋር በመነጋገር የተማርኩት ነገር ቢኖር ለረጅም ዓመታት በኮሚኒዝም አስተዳደር ሥር ለነበሩ ወጣቶች ወንጌልን ስንሰብክ ከእነርሱ አስተሳሰብ ጋር በሚጣጣም ቋንቋ ማቅረብ እንዳለብን ነው ።

ወደ ማዕከላዊ አፍሪካ የሚሄዱ የወንጌል መልእክተኞች "ሃጢአታችሁ እንደ አለላ ብትሆን እንደ በረዶ ትነፃለች" የሚለውን ቃል ለሀገሬው ሰዎች ለመተርጐም ችግር አለባቸው ። በማዕከላዊ አፍሪካ ያሉ ሰዎች በረዶ አይተው ስለማያውቁ ራሱ ቃሉ የላቸውም ፤ ስለዚህም የበረዶን

ንጣት ለማጣየት ሌላ በአካባቢያቸው ባለ ነጭ ነገር በመጠቀም መተርጐም ይኖርባቸዋል ።

እኛም ብንሆን የወንጌልን መልእክት ማርክሲስቶች ሊገባቸው በሚችል አቀራረብ ልናቀርብላቸው ይገባል ። ይህንንም እኛ ብቻችንን ልናደርግላቸው ስለማንችል መንፈስ ቅዱስ ማስተዋልን ሊሰጠን ያስፈልጋል ።

እነዚህ ሁለት ሰዎች በዚያው ቀን ጌታን ተቀበሉ ። ከዚያ በኋላ በሩስያውያን መካከል ለነበረን ኅቡዕ የወንጌል አገልግሎት ከፍተኛ እገዛ አድርገውልናል ።

ወንጌሎችንና ሌሎች ክርስቲያናዊ ጽሑፎችን በድብቅ እያተምን ለሩሲያውያን እናድል ነበር ። እነዚህንም ጽሁፎች ወደ ሩሲያውያኑ የምናደርሰው አስቀድመው ጌታን ተቀብለው በነበሩ ሩሲያውያን አማኞች ነው ።

ከዚህም ሌላ በሩሲያውያን መካከል ወንጌልን የምናስፋፋበት ዘዴ ነበረን ። እንደሚታወቀው ሩሲያውያኑ ረጅም ዓመታት በጦር ሜዳ አሣልፈዋል ። ከልጆቻቸው ከተነጠሉ ዓመታት ስለተቆጠሩ የቤተሰቦቻቸውና የልጆቻቸው ናፍቆት እንዳለባቸው ግልጽ ነው ።

ሩስያውያን ከፍተኛ የልጆች ፍቅር አላቸው ። ስለዚህ በዚህ አጋጣሚ በመጠቀም ልጄ ሚኻይንና ሌሎች ከአሥር ዓመት በታች የሆኑ ሕፃናትን መጽሐፍ ቅዱሶችና ሌሎች ክርስቲያን ሥነ ጽሑፎችን አስይዘን ወደ ሩሲያውያኑ ወታደሮች እንልካቸዋለን ። ሩሲያውኑ ወታደሮች አገራቸው ያሉዋቸው የራሳቸው ልጆች ትዝ ስለሚሉዋቸው ፀጉራቸውን እያሻሹ ጉንጮቻቸውን እየደባበሱ በፍቅር ይቀበሉዋቸዋል ። ሩሲያውኑ ለሕፃናቱ ቸኮላት ሲሰጧቸው ፣ ሕፃናቱ ደግሞ ቅዱሳት መፃሕፍትንና ሌሎች ክርስቲያናዊ ጽሑፎችን ይሰጧቸዋል ። ወታደሮቹ ጽሑፎቹን የሚቀበሉት በታላቅ ጉጉት ነበር ። ስለዚህም ለእኛ በጣም አስቸጋሪ ሊሆንብን የሚችለውን ሥራ ሕፃናቱ ያለ ምንም ችግር ይሠሩልን ጀመር ። አዎን ሕፃናቱ ለሩሲያውያን የተላኩ "ወጣት ሚስዮናውያን" ናቸው ። በዚህ አሠራር አጥጋቢ ውጤት አግኝተንበታል ።

# የወንጌል ስብከት በወታደሮች ካምፕ ውስጥ

ለሩሲያውያን የምንሰጠው የወንጌል አገልግሎት በግለሰብ ምስክር ነት ብቻ አልተወሰነም ፤ መጠነኛ ስብሰባ በማድረግ ማስተማር ጀምረን ነበር ።

ለሩሲያውያን የእጅ ሰዓት ብርቅቸው ስለነበር ፣ በየመንገዱ ከሚያገኙት አላፊ አግዳሚ ሁሉ ሰዓት የማስፈታት ልምድ ነበራቸው ፣ የሩሲያ ወታደሮችን ብዙ የተለያዩ ሰዓቶችን በሁለት እጃቸው አድርገው መመልከት የተለመደ ጉዳይ ነበር ። አንዳንድ ሩሲያውያን ሴት ባለሥል ጣኖች የጠረጴዛ ሰዓት እንደ ሐብል ሁሉ አንገታቸው ላይ አንጠልጥለው ይታያሉ ። ከዚህ በፊት ሰዓት ስላልነበራቸው አጋብሰው አይረኩም ። በካምፓቸው ውስጥ የተሠረቁ ወይም የተዘረፉ ሰዓቶች ይሸጡ ስለነበር ሰዓት የሚፈልጉ ሩማንያውያን ወደ ካምፕ በመሄድ አማርጠው ይገዛሉ ። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የተሠረቀባቸውን ወይም የጠፋባቸውን የራሣቸውን ሰዓት ገዝተው ይመለሳሉ ። እኛም ሰዓት ለመግዛት በሚል ሽፋን ወደ ካምፕ እንሄድና አጋጣሚው ሲያመቸን ወንጌል እንሰብካለን ።

በበኩሌ ወደ ካምፑ የሄድሁት ጴጥሮስ ወጳውሎስ የሚባል የሩሲያ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በዓል በሚከበርበት ጊዜ ነበር ፣ ወደ ካምፑ የገባሁት ሰዓት ለመግዛት በሚል ሰበብ በመሆኑ አንዱን ከአንዱ በማማረጥ አንዱን በጣም ውድ ነው ፤ ሌላውን በጣም ትንሽ ነው ፤ ሌላውን ደግሞ በጣም ትልቅና ከርፋፋ ነው ፤ በማለት ሁናታዎችን አመቻች ጀመር ። ብዙ ሰዓት ሻጭ ወታደሮች ከበቡኝ እያንዳንዱ "ይሄኛው ይሻልሃል ፣ ይሄኛው በጣም ጥራት ያለውና ዋጋውም መጠነኛ ነው" እያሉ ሰዓታቸውን ያቀርቡልኝ ነበር ። እኔም ፈቱንም የሄድሁት ሰዓት ለመግዛት አልነበረምና "ለመሆኑ ከእናንተ መካከል ጳውሎስ ወይም ጴጥሮስ የሚባል ይኖራል? በማለት ጠየቅኋቸው ። በጣት የሚቀጠሩ ሰዎች "አዎን" የሚል መልስ ሰጡኝ ። ወዲያውኑ ቀጠል አደረግሁና" ዛሬ የሩሲያ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የጴጥሮስ ወጳውሎ ስን ቀን የምታከብርበት ዕለት መሆኑን ታውቃላችሁ? አልኳቸው ከሽማግሌዎች በቀር ወጣቶቹ እንደማያውቁ ነገሩኝ ። ጴጥሮስና ጳውሎስ እነማን ነበሩ? አልኳቸው ፤ የመለሰልኝ ግን አልነበረም… እኔም ጴጥሮስና

ጳውሎስ እነማን እንደነበሩ በመናገር ላይ እያለሁ ከሽማግሌዎቹ ወታደ ሮች አንዱ አቋረጠኝና" ፊቱንም አንተ የመጣኸው ሰዓት ለመግዛት ሳይሆን ስለ ሃይማኖት ለመስበክ ነው ፤ እስቲ አረፍ በልና ንገረን ፤ ግን ልብ አድርግ እዚህ አካባቢ ያሉት ሁሉም ደኅና ሰዎች ናቸው ከማን መጠንቀቅ እንዳለብን ስለምናውቅ እጄን ጉልበትህ ላይ ሣደርግ ስለ ሰዓት ተናገር እጄን ከጉልበትህ ሳነሣ ግን ካቆምክበት ቦታ ስብከትህን ቀጥል" አለኝ። ብዙ ሰዎች ተሰበሰቡ ፤ እኔም ስለ ጳውሎስና ስለ ጴጥሮስ ፡ እነርሱም ሲያገለግሉት ስለነበረው ክርስቶስ ነገርኳቸው ፤ የማይተማመኑ በት ሰው ወደ አጠገባችን ሲመጣ ያ ወታደር እጁን ጉልበቴ ላይ ያደርጋል፤ እኔም ስብከቴን አቋርጥና ስለ ሰዓት አወራለሁ ። ተጠርጣሪው ሲሄድ ደግሞ ካቆምኩበት ስፍራ ስለ ኢየሱስ አዳኝነት መስበኬን እቀጥላለሁ ። በካምፑ ውስጥ በነበሩ ክርስቲያን ሩሲያውያን አማካይነት በተደጋጋሚ እየሄድሁ ወንጌል ስለሰበኩሁላቸው ብዙዎች ጌታን ተቀ በሉ ፣ ብዙ ቅዱሳት መፃሕፍትንም አሠራጨን ።

ምንም እንኳ ብዙ የእምነት ወንድሞቻችንና እህቶቻችን በተለያየ ሁኔታ ወንጌልን ሲሰብኩ በመገኘታቸው ቢደበድቡም ፣ እነርሱ ግን ስለ ጌታ ኢየሱስ አዳኝነት መመስከራቸውን ለማቆምም ሆነ ሌሎችን አሣልፈው ለመስጠት አልፈለጉም ።

በዚህ እንቅስቃሴያችን በሩሲያ ውስጥ እንደእኛው ወንጌልን በኅቡዕ ያስፋፉ የነበሩ ክርስቲያኖችን አገኘን ፤ ስለ ሥራ ልምዳቸውም ያካፈሉን ሃሣብ በጣም ነበር የጠቀመን ። እነዚህ ክርስቲያኖች ለብዙ ዓመታት ኮሚኒስታዊ የክህደት ትምህርት ሲስፋፋበት በነበረ አገር የኖሩ ናቸው ። አንዳንዶቹም በኮሚኒስት ዩኒቨርስቲዎች ያተማሩ ነበሩ ። ይሁን እንጂ ዓሣ በጨው ባሕር ውስጥ ቢኖርም ፣ ዓሣነቱ ተለውጦ ጨው እንደማይሆን ሁሉ እነዚህ ወገኖች በኮሚኒስቶች ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የተማሩ ቢሆኑም እምነታቸውን አልካዱም ። በክርስቶስ ኃይል ነፍሳቸውን በቅድስና ጠብቀዋል ።

እነዚህ ሩሲያውያን ክርስቲያኖች "በባርኔጣችን ላይ ያለው መዶሻና ኮከብ የክርስቶስ ተቃዋሚ ዓርማ እንደሆነ እናውቃለን ሆኖም ምንም ማድረግ አንችልም" በማለት ሲናገሩ በታላቅ ኀዘን ነው ። በሩሲያውያን ወታደሮች መካከል ወንጌልን እንድሰብክ ከፍተኛ ድጋፍ

ያደረጉልኝ እነዚህ ወገኖች ነበሩ ።

ምንም እንኳ ማንኛውም የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ በነዚህ ክርስቲያኖች ሕይወት በግልጽ ቢታይም ደስተኞች ግን አልነበሩም ። ደስታን የተለማመዱት ጌታን በተቀበሉበት ወቅት ነበር ። ግን ያ የደስታ ሕይወት ወዲያውኑ ተቋረጠ ። አንድ ጊዜ አንድ የባፕቲስት አባል የሆነ ክርስቲያንን "ምንም ደስተኛነት የማላይብህ ለምንድን ነው?" ስል ጠየቅሁት "ክርስቲያን መሆኔን ደብቄ በምኖርበት ሁኔታ እንዴት ደስተኛ ልሆን እችላለሁ?" የሚል መልስ ነበር የሰጠኝ ። እያንዳንዱ አማኝ ከደኅንነቱ ያገኘው ይህ ነው የማይባል ደስታ በጥልቅ ልቦናው ውስጥ አለው ። ካለው ሁኔታ የተነሣ ግን ይህን ደስታ በውጫዊ መልኩ ሊገልጸው አይችልም ።

በነፃው አገር ያሉ ክርስቲያኖች አንድን ሰው ወደ ክርስቶስ ሲያመጡ ወደ ምዕመናን ኅብረትና አንድነት ነው የሚያመጡት ። እኛ በኮሚኒስት አገሮች ያለን ክርስቲያኖች ግን አንድን ሰው ወደ ክርስቶስ ስናመጣው እሥራት እንደሚጠብቀው በማወቅ ነው ። ምናልባትም ልጆቹ ያለ እናትና አባት ይቀሩ ይሆናል ። አንድን ሰው ወደ ክርስቶስ ማምጣቱ የራሱ ደስታ ቢኖረውም ለዚህ የምንከፍለው ዋጋ አለ ።

ከአዲስ ክርስቲያን ማኅበረ ሰብ ጋር ነው የተዋወቅነው ፤ በኅቡዕ ወንጌልን ከሚያስፋፉ ክርስቲያን ማኅበረ–ሰብ ጋር ።

እዚህ ላይ አንዳንድ አስደናቂ ሁኔታዎች ማንሣት ይቻላል ። ክርስቲያን ሣይሆኑ ክርስቲያን የሆኑ የሚመስላቸው እንዳሉ ሁሉ ፣ ከሃዲ የሆኑ ቢመስላቸውም ከሃዲ ያልሆኑ ብዙ ሰዎች ገጥመውናል ።

አንድ ጊዜ ከሩሲያውያን ባልና ሚስት ጋር እየተጫወትሁ ነበር ። የተለያዩ ምስሎችን በድንጋይ የመቅረጽ ሙያ ያላቸው ናቸው ። ስለ እግዚአብሔር ልነግራቸው ስጀምር "እኛ ቤዝቦንሽኪ (አምላክ የለሾች) ነን ስለዚህም በእግዚአብሔር ሕልውና አናምንም፡ ይሁን እንጂ አንድ ጊዜ የገጠመንን አስደናቂ ነገር ልንገርህ እንወዳለን" አሉኝ ።

የስታሊንን ሐውልት በመሥራት ላይ በነበርንበት ወቅት ባለቤቴ "ለመሆኑ ስለ አውራ ጣት አስበህ ታውቃለህ? ሌሎች ጣቶቻችን ከአውራ ጣት ጋር በአንድነት ባይሠሩ ኖሮ ምንም ነገር ለማንሣት ባልቻልንም ነበር ፣ ታድያ ይህን አውራ ጣት የሠራው ማነው? እኔም ሆንኩ አንተ ማርክሲዝምን ተምረናል ፣ ሰማይና ምድርም ያለ አንዳች አስገኚ ኃይል

እንደተፈጠሩ ነው የተማርነው ። እግዚአብሔር የሰማይና የምድር ፈጣሪ ባይሆንም የትንሿ አውራ ጣት ፈጣሪ ብቻ በመሆኑ እንኳ ሊመሰገን ይገባዋል ።

የኤሌክትሪክ አምፖልን ፡ ስልክንና የባቡር ሐዲድን ሌሎችንም ስለ ሠሩ ኤዲሰንን ቤልንና ስቲቬንሰንን እናደንቃቸዋለን ታድያ ይህን አውራ ጣት የሠራው ፈጣሪ መደነቅ ይበዛበታል? ኤዲሰን አውራ ጣት ባይኖረው ኖሮ ምናልባትም ምንም ነገር ላይሠራ ይችል ይሆናል አውራ ጣትን ስላፈጠረ ብቻ እግዚአብሔር ሊመሰገን ይገባዋል

ብዙ ጊዜ ሚስቶች ከእነርሱ የሚሻል አስተሳሰብ ሲያቀርቡላቸው እንደሚናደዱት ሁሉ ይህም ባል ሚስቱ ባቀረበችለት ሃሣብ በጣም ተናደደ "እንዲሁ ያለ የማይረባ ነገር አትናገሪ እግዚአብሔር እንደሌለ ተነግሮሻልና ይህንኑ ተቀበይ በሰማይ ምንም አምላክ ስለሌለ እርሺው ይልቅ ሥራሽ ላይ በርቺ" አላት ።

እርሷም "እስከ ዛሬ ድረስ አባቶቻችን በድንቁርናቸው በእግዚአብ ሔር ሲያመልኩ ኖረዋል ፤ ይህ አምላክ ካለ ደግሞ አውራ ጣትን የሠራልን እርሱ ነው ማለት ነው ፤ በሰማይ ምንም አምላክ ባይኖርም ፡ እኔ ግን በዚህ በሌለው የአውራ ጣት ፈጣሪ አምናለሁ" አለችው ።

ስለዚህም በአውራ ጣት ፈጣሪ ማመን ጀመረች ፡ የኋላ ኋላ ግን እርሷ እና ባለቤትዋ እግዚአብሔር የአውራ ጣት ፈጣሪ ብቻ ሣይሆን የሰማይና የምድር የከዋክብት የአበቦች ፡ የሰዎችና በጠቅላላው የነገሮች ሁሉ ፈጣሪ መሆኑን ማመን ጀመሩ ።

ሐዋርያው ጳውሎስ ለወንጌል አገልግሎቱ ወደ አቴንስ በሄደበት ወቅት "የማይታወቅ አምላክን" ከሚያመልኩ ሰዎች ጋር ተገናኝቶ ነበር።

እኔም ለእነዚህ ሰዎች እግዚአብሔር የፍቅር ፡ የጥበብ ፡ የዕውነትና የኃይል መንፈስ በመሆኑ በሰማይ ሊወሰን እንደማይችልና ባያውቁትም እንኳ በእርሱ ማመናቸው ትክክል እንደሆነ ነገርኳቸው ። ይህም አምላክ ፍቅር ስለሆነ በእነርሱ ምትክ እንዲሞት አንድ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ወደዚህ ዓለም እንደላከው አስረዳኋቸው ።

ምንም እንኳ ባያውቁትም እነዚህ ሰዎች አማኞች ነበሩ ፡ እኔ ያደረግሁት ቢኖር አንድ እርምጃ ወደፊት ሄደው የደኅንነትን ልምምድ እንዲያገኙ ማድረግ ነበር ።

አንድ ጊዜ በመንገድ ላይ አንዲት ሩሲያዊት የጦር መኮንን አገኘሁ። አስቀድሜ ይቅርታ በመጠየቅ ቀረብ አልኳትና "በመንገድ ላይ የማያውቋትን ሴት ማነጋገር ጨዋነት እንዳልሆነ አውቃለሁ ፣ ይሁን እንጂ የቤተ ክርስቲያን መሪ ስለሆንኩ ዓላማዬ ቅን መሆኑን ልገልጽልሽ እወዳለሁ "እስቲ ስለ ክርስቶስ ጥቂት ላነጋግርሽ" አልኳት ።

እርሷም "ለመሆኑ አንተ ራስህ ክርስቶስን ትወደዋለህ?" አለችኝ። "አዎን በሙሉ ልቤ ክርስቶስን እወደዋለሁ" በማለት መለስኩላት እየደጋገመች ሳመችኝ አንድ የቤተክርስቲያን መሪ በእንዲህ አይነት ሁኔታ በመንገድ ላይ መታየቱ ስላሳፈረኝ እኔም መልሼ ሳምኳት ይህን ያደረግሁት ዘመዳሞች እንደሆንን ለማስመሰል ነበር ። "እኔም እንዳንተ ክርስቶስን እወዳለሁ" አለችኝ ። ወደቤት ይገድእት ሄድሁ ። ስለ ክርስቶስ የምታውቀው በጣም በጥቂቱ ነው ፤ ክርስቶስ አዳኝ መሆኑን ፣ የዘላለም ሕይወት የሚገኘውም በእርሱ በማመን እንደሆነ አታውቅም ፤ ግን ትወደዋለች ። ሁኔታዋ ሥነ ልቦናዊ ጉጉትን አሳደረብኝና ስለ ክርስቶስ እንደሚገባ ሳታውቂ እንዴት ልትወጂው ቻልሽ? በማለት ጠየቅኋት ።

እርሷም — "በልጅነቴ በስዕል ማንበብን ተምሬአለሁ ። ለምሣሌ — በ—በግ—ቡ—ቡና—ቢ— ቢላዋ በማለት ። ሁለተኛ ደረጃ ከደረስኩ በኋላም ኮሚኒስት እናት አገሬን ለማገልገል ስላለብኝ ቅዱስ ተግባር ተነገረኝ ። ኮሚኒስታዊ ሞራልንም አስተማሩኝ ፤ ይሁን እንጂ "ቅዱስ ተግባር" ወይም "ሞራል" ምን እንደሚመስሉ ግን እርግጠኛ አልነበርኩም ። እነዚህን ነገሮች ለመረዳት ገለፃ የሚሰጠኝ ነገር ፈለግሁ ። አባቶቻችን በሕይወት ለሚገጥሙን ውብ — ድንቅና እውነታ ላላቸው ነገሮች ስዕላዊ ገለፃ እንደነበራቸው አውቃለሁ ። አያቴ እነዚህን ነገሮች ሁሉ ይወክላል በምትለው ስዕል ፊት ሁል ጊዜ በአክብሮት ስትንበረከክ እመለከታት ነበር ። ያ ስዕል የክርስቶስ ስዕል እንደሆነ ነግራኛለች ። ታድያ ከጊዜ ብዛት ያን ስዕል ወደድሁት ፤ ስዕሉ ፈጠራ ብቻ ሳይሆን እውነት ሆነልኝ ፣ "ክርስቶስ" የሚለው ስም ራሱ ይህ ነው ብዬ ልገልፀው የማልችለውን ደስታ ይሰጠኛል አለችኝ ።

የምትናገረውን እየሰማሁ እያለ ሐዋርያው ጳውሎስ ለፊሊጵስዩስ ሰዎች በፃፈው መልእክቱ — "ጉልበት ሁሉ ለክርስቶስ ክብር ይንበረከክ ካል። እንደበትም ሁሉ ክቡር ስሙን ያመሰግናል" በማለት የፃፈው ትዝ

አለኝ ። ምናልባትም የክርስቶስ ተቃዋሚ ሰዎች ስለ እግዚአብሔር ያላቸውን ፍቅር ለተወሰነ ጊዜ ያደበዝዘው ይሆናል ፤ የክርስቶስ ስም ግን ወደ እውነተኛ ብርሃን የሚመራበት ኃይል ነው ።

በዚያው ቀን በቤቴ ውስጥ በታላቅ ደስታ ጌታን ተቀበለች ። በስም ብቻ ትወደው የነበረው ክርስቶስ የሕይወቷ አዳኝና ጌታ ሆነ ።

ለሩሲያውያን ወንጌልን በመስበክ ያሳለፍኩት ጊዜ በሙሉ ቅኔያዊ ውበት እና ጥልቅ የሕይወት ትርጉምን የተረዳሁበት ጊዜ ነው ። አንድ ጊዜ አንዲት ክርስቲያን እህት አድራሻዬን ሰጥታ የላከችው ሩሲያዊ ባለሥልጣን ወደ ቤቴ መጣ ።

ይህ ረጅምና መልከ–ቀና ሩሲያዊ ሻለቃ በዚያች ምሽት ወደ ቤቴ በመጣበት ወቅት "የእኔ ወንድም ምን ልርዳህ?" በማለት ጠየቅሁት ።

"ስለ ብርሃን እንድትነግረኝ ነው የመጣሁት" አለኝ ።

ለጊዜው በጣም አስፈላጊ ናቸው ብዬ ያሰብኳቸውን ክፍሎች ከመጽሐፍ ቅዱስ አነበብኩለት ። በእጁ እጄን ያዝ አደረገና– "በጨለማ እንዲኖሩ ከተደረጉት ሰዎች አንዱ ነኝ ፣ እባክህን – በተሣሣተ መንገድ አትምራኝ ፣ ለመሆኑ ይህ የምትነግረኝ ትክክለኛው የእግዚአብሔር ቃል ነው?" አለኝ ። እኔም የማነብለት የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ ካረጋገጥኩለት በኋላ ያለአንዳች መሰልቸት ለጥቂት ሰዓቶች ያህል የወንጌልን ቃል በጽሞና አደመጠ ። በዚያው ቀን በክርስቶስ አመነ ።

ሩሲያውያን በያዙት ነገር ጠንካሮች ናቸው ። ኀይማኖትን ከፈለጉ እንዲሁ ላይ ላዩን ሣይሆን በሙሉ ልባቸው ነው የሚፈልጉት ነፍሳቸው የምትፈልገውን ክርስቶስን ካላገኙ በቀር አይረኩም ። ኃይማኖትን ከተቃወሙም እንደዚያው ናቸው ። ለዚህ ነው ማንኛውም ሩሲያዊ ክርስቲያን ሌሎችን ወደ ክርስቶስ ለማምጣት የሚተጋው ። ሩሲያ ከማንኛውም አገር ይልቅ ለወንጌል ዘር ለም ምድር ነች የሚባለውም ለዚህ ነው የወንጌልን እውነት ብንሰጣቸው የዓለም ገጽታ በተለወጠ ነበር ።

ሩሲያውያን ለእግዚአብሔር ቃል እውነት የተራቡና የተጠሙ ቢሆንም የዓለም ሕብረተ ሰብ ግን የዘነጋቸው ይመስላል ።

አንድ ጊዜ በባቡር በመጓዝ በነበርኩበት ወቅት ፊት ለፊቴ አንድ ሩሲያዊ ባለስልጣን ተቀምጦ ነበር ፣ ለጥቂት ደቂቃዎች ስለ ክርስቶስ

ነገርኩት ፤ ሰውየው በእግዚአብሔር የማያምን ስለነበር የተማረውን የክህደት መከራከሪያ ሃሳቦች ያዥጐደጉደው ጀመር ። እግዚአብሔር አለመኖሩን ሊያሳምነኝ ከማርክስ ፤ ከስታሊን ፤ ከቮልቴር ፤ ከዳርዊንና ከሌሎችም የተለያዩ ጥቅሶችን እየጠቀሰ ከአንድ ሰዓት ለማያንስ ጊዜ ተናገረ ። ምንም የመናገር ዕድል አልሰጠኝም ። ንግግሩንም ከጨረሰ በኋላ "እሺ እግዚአብሔር የለም የምትል ከሆነ ለምንድን ነው ችግር ሲገጥመህ የምትፀልየው?" በማለት ጠየቅሁት ፤ "እንደምፀልይ ማን ነገረህ?" አለኝ። እኔ ግን ምንም ማምለጫ መንገድ እንዳያገኝ በመጀመሪያ ለጠየቅሁህ መልስ ስጠኝ ፤ ለምንድን ነው በችግርህ ጊዜ የምትፀልየው? በማለት ያዝኩት "አዎን በውጊያ ላይ በነበርንበት ወቅት በጀርመን ወታደሮች ከበባ ሲደረግብን ማንኛችንም ብንሆን እንፀልያለን ። በመሠረቱ ስለ ፀሎት ብዙ የምናውቀው የለንም ። ብቻ እንዲሁ በደፈናው የእናቴ አምላክ አውጣኝ እንላለን" አለኝ ። ልብን የሚመረምር አምላክ እንዲህ ዓይነቱን ፀሎት እንኳ አይንቅም ።

ለሩሲያውያን የምንሰጠው አገልግሎት ብዙ ፍሬ አስገኝቶአል ። ፒዮትር (ጴጥሮስ) ምን ጊዜም ትዝ ይለኛል ፤ በየትኛው እሥር ቤት እንደሞተ ማንም አያውቅም ። ምናልባትም ከሃያ ዓመት የማይበልጠው ወጣት ሲሆን ወደ ሩማንያ የመጣው ከሩሲያ ወታደሮች ጋር ነበር ። ጌታን የተቀበለው በኅቡዕ በምናደርገው የወንጌል ስብሰባ ነበር ። እርሱ ራሱ በጠየቀው መሠረት አጠመቅሁት ።

ከተጠመቀ በኋላ ወደ ጌታ እንዲመጣ ልቡን የነካው የትኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል እንደሆነ ጠየቅሁት ።

እርሱ እንደነገረኝ አንድ ጊዜ በስብሰባ ስፍራ በኤማሁስ መንገድ ይጓዙ የነበሩት ሁለት ደቀ መዛሙርት እንዴት ከክርስቶስ ጋር እንደተገናኙ ከሉቃስ 24 በምሰብክበት ጊዜ በጽሞና ያዳምጥ ነበር ። ወደ መንደሩም በቀረቡ ጊዜ እየሱስ መንደሩን አልፎ የሚሄድ መሆኑን ሲረዱ ቀኑ በመምሸቱ አብሮአቸው እንዲያድር ጠየቁት ። እርሱም በአሳባቸው ተስማምቶ ከእነርሱ ጋር ወደ ቤት ገባ ። ለምንድን ነው ጊዜው እንደመሸ ቢያውቅም እንኳ ወደ ቤታችን ና እስኪሉት ድረስ የጠበቀው? አለኝ ። እኔም እየሱስ ጨዋ ነው ሰዎች እንደሚፈልጉት እርግጠኛ መሆን ይፈልጋል ፤ የሚፈልጉት ከሆነ ግን በቤታቸው ገብቶ ይስተናገዳል ፤

ኮሚኒስቶች ግን ማንም ማይጋብዛቸው ልባችንና አእምሮአችንን በር‌ግ ደው መግባት ይሞክራሉ ። ከጥዋት እስከ ማታ ድረስ እነርሱን ብቻ እንድናደምጥ ነው የሚፈልጉት ። ወደድነውም ጠላነውም በትምህርት ቤቶች ፡ በሬዲዮ ፡ በጋዜጦችና መጽሔቶች በፖስተሮች በሲኒማዎች በየጊዜው በሚያዘጋጁት እምላክ የለሽ ስብሰባዎች የሚያሠራጩትን ፕሮፓጋንዳ መስማት አለብን ። እየሱስ ግን ጨዋ ስለሆነ ነፃ የመምረጥ መብታችንን ያከብራል ። ስለዚህ ነው – "እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ ፡ ማንም ድምጼን ሰምቶ በሩን ቢከፍትልኝ ወደ እርሱ እገባለሁ" ያለው። ይህንንም ወጣት በክርስቶስ እንዲያምን ያደረገው በኮሚኒዝምና በክርስ ቶስ መካከል ያለውን ልዩነት በመረዳቱ ነበር ። "በክርስቶስ እንዳምን ያደረገኝ ጨዋነቱ ነው" አለ ፒዮትር ።

በክርስቶስ ባሕርይ ከሚመለከቱት ውበት የተነሣ የብዙ ሩሲያው ያን ልብ ሊነካ ችሎአል (ፓስተር ብሆንም በበኩሌ በዚህ መልክ አስቤበት አላውቅም)

በጌታ ካመነ በኋላ ፒዮትር ሕይወቱንና ነፃነቱን መስዋዕት በማድ ረግ ከነፃው ዓለም ክርስቲያናዊ ጽሑፎችን በድብቅ በማስገባት በሩማን ያና በሩሲያ ላሉ ክርስቲያኖች ወንጌልን ማሠራጨት ጀመረ ። በመጨረ ሻም ክርስቲያን ጽሑፎችን ማሠራጨቱ እንደ ወንጀል ተቆጥሮበት ታሠረ ። እስከ 1959 ዓ.ም ድረስ እሥር ቤት ውስጥ እንደነበር አውቃለሁ። ዛሬስ ሞቶ ይሆን? ሩሜውን ጨርሶ በሰማይ ይሆን ወይስ ገና በዚህ ምድር መልካሙን የእምነት ገድል እየተጋደለ ይሆን? የት እንዳለ የሚያውቅ እግዚአብሔር ብቻ ነው ።

ሰዎችን ወደ ክርስቶስ በማምጣት ብቻ መርካት የለብንም ፡ ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ማምጣት ግማሽ ሥራ ነው ። ወደ ክርስቶስ የመጡት ሁሉ ሌሎቹንም ወደ እርሱ ማምጣት አለባቸው ። ሩስያውያን ግን በክርስቶስ ሲያምኑ ፡ ሌሎችን ወደ እርሱ የሚያመጡ የወንጌል መልዕክተኞች ይሆናሉ ፡ ሕይወቱን በመስጠት ክርስቶስ ከከፈለላቸው መስዋዕትነት አንፃር ይህ በጣም ትንሽ እንደሆነ ነው የሚያስቡት ።

# ኅቡዕ የወንጌል አገልግሎት – የባርነት ቀንበር ለተጫናቸው ሰዎች

ሁለተኛው የአገልግሎታችን ገጽታ ለሩማንያውያን ክርስቲያኖች መካከል በኅቡዕ ወንጌልን የማሠራጨት ነው ።

ገና ብዙ ሳይቆዩ ኮሚኒስቶች አጥልቀውት የነበረው ጭምብል ወደቀና እውነተኛ ገጽታቸው ገሃድ ወጣ ። ሥልጣን እስኪይዙ ድረስ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ድጋፍ ለማግኘት ለዘብተኞች ሆነው ነበር የቀረቡት ። የሚፈልጉትን ካገኙ በኋላ ግን ዛቻና ማስፈራራት ጀመሩ ። በሺህ የሚቆጠሩም ታሠሩ ፤ አንድን ሰው ወደ ክርስቶስ ማምጣት አስቸጋሪ የሆነበት ጊዜ መጣ ። ይህንን ግን ከእኛ ቀደም ብለው ሩሲያውያን ተለማምደውታል ።

እኔ ራሴም በእግዚአብሔር ፀጋ ወደ ክርስቶስ ካመጣኋቸው ሰዎች ጋር አብሬ ወኅኒ ወረድሁ ። አብረውኝ ከታሠሩት ሰዎች አንዱ ሚስትና ስድስት ልጆች ነበሩት ፤ እርሱ ስለ ታሠረ ሚስቱና ልጆቹ መራብ ነበረባቸው ። ምናልባትም ዓይን ለዓይን ላይተያዩ ይችላሉ ። ታድያ – አንድ ቀን ይህንን ክርስቲያን ወንድም–"አንተ ታስረሃል ፤ ሚስትና ልጆችህም ችግር ላይ ናቸው ፤ ይህም የደረሰብህ በእምነትህ ምክንያት ነው፤ ወደዚህ እምነት የመጣኸውም በእኔ ምክንያት ነው ፤ ለመሆኑ እኔ ላይ ቅሬታ ይኖርህ ይሆን?" በማለት ላቀረብኩለት ጥያቄ የሰጠኝ መልስ በፍጹም ያልጠበቅሁት ነበር ። "በዚህ አስደናቂ ጌታና አዳኝ በማመኔ የተሰማኝን ደስታ በቃላት ልገልፀው አልችልም ፤ ከዚህ እምነት ውጪ ይህን ደስታ ማግኘት አልችልም" ነበር አለኝ።

አዲስ በተፈጠረው ሁኔታ ስለ ክርስቶስ መስበክ ቀላል አልነበረም። በስንት ችግር በኮሚኒስቶች ሣንሱር ከተደረገ በኋላ ጥቂት ክርስቲያናዊ ፓምፍሌቶችን ለማሳተም ቻልን ። አንድ ጊዜ ለሳንሱር ያቀረብናቸው ጽሑፎች የኮሚኒዝም መሥራች የሆነው የካርል ማርክስ ስዕል ያለባቸው ሲሆኑ ፣ ሳንሱር አድራጊዎችን ለማማላት "ሃይማኖት – ኅብረተሰብን የሚያደነዝዝ ዕፅ" ወይም ደግሞ ሌሎች ይህን የሚመስሉ አርዕስት እንሰጣቸዋለን ሳንሱር አድራጊው ጥቂት አገላብጦ ከተመለከተ በኋላ

ያው ጊዜው የወደደው የኮሚኒስቶች ጽሑፍ ስለሚመስለው ያለ አንዳች ችግር ማኅተም ያደርግባቸውና እንዲታተሙ ይፈቅድልናል ። የእነዚህ መጻሕፍት ጥቂት ገጾች የማርክስ ፣ የሌኒንና የስታሊን ቃላት የሰፈረባቸው ሲሆኑ ፣ አብዛኞቹ ግን የክርስቶስ ትምህርቶች ናቸው ። ሌላ ዘዴ ብናጣ ወንጌልን በዚህ መልክ ማቅረብ ጀመርን ።

ሕዝብ በሚበዛባቸው አደባባዮች እነዚህን ጽሑፎች ለሽያጭ እናቀርባቸዋለን ። ሕዝቡም የማርክስን ስዕል ስላየ ብቻ ተሻምቶ ይገዛናል። ቢያንስ እስከ አሥረኛው ገጽ ካነበቡ በኋላ የሚያገኙት ስለ እግዚአብሔር ወይም ስለ ክርስቶስ የሚናገሩ ጥቅሶችን ነው ። ያን ጊዜ ደግሞ እኛ ከአካባቢው ስለምንርቅ ሊያገኙንና ጥያቄ ሊያቀርቡልን አይችሉም።

ይሁን እንጂ በዚህ መልክ የሚደረገው አገልግሎት ቀላል አልነበረም ። ሰዎቻችን በከፍተኛ ችግር ነበሩ። ኮሚኒዝም ካስከተለው ችግር ማንም ያልተነካ የለም ። ከገበሬው እርሻውንና ከብቱን ነጠቁ ፣ ከልብስ ሰፊዎችና ፀጉር አስተካካዮች እንኳ ሳይቀር ሱቆቻቸው ተወሰዱ ። ሀብት ንብረታቸውን የተነጠቁት ቡርዣዎች ወይም አድሃሪዎች ብቻ ሳይሆኑ የባሰባቸው ድሆች እንኳ ያችኑ ያለቻቸውን ተነጥቀዋል ። በዚህ ላይ ቢያንስ ከእያንዳንዱ ቤተሰብ ዘመድ ያልታሠረበት ሰው ፈልጐ ማግኘት አስቸጋሪ የሆነበት ወቅት ነበር ። ስለዚህም ሰዎች በየሥፍራው "ለመሆኑ እግዚአብሔር አለ? እንደሚነገርለት የፍቅር አምላክ ከሆነስ ይህ ሁሉ ግፍ ሲደረግ እንዴት ዝምብሎ ይመለከታል? እያሉ ሲጠየቁ መስማት የተለመደ ሆኖ ነበር ።

"አምላኬ ፣ አምላኬ ፣ ለምን ተውኸኝ?" በማለት እየሱስ በመስቀል ላይ በሞተበት ዕለተ ዐርብ ወንጌልን መስበክ ለደቀ መዛሙርቱ ምን ያህል ከባድ እንደነበር መገመት አዳጋች አይደለም ።

በዚያ ሁሉ ችግር ግን ሥራው መሰራቱ ኃይሉ የእግዚአብሔር እንጂ የእኛ እንዳልነበረ ማስረጃ ነው ። የክርስትና እምነት ለእንዲህ ዓይነት ጥያቄዎች መልስ አለው ።

እየሱስ አልዓዛር ስለሚባል ድሃ ሰው ምሣሌ ተናግሮአል ። ይህ ሰው እንደማንኛችንም ሁሉ ረሀብተኛና በችግር የጉሰቆለ ነበር ፤ ቁስሎቹን ውሾች ይልሱለት ነበር ። በመጨረሻ ግን መላእክት ወደ አብርሃም እቅፍ

ወሰዱት ።

በመኖሪያ ቤት ፣ በምድር ቤቶች ፣ በጫካዎችና አመቺ ሆኖ በተገኘው ስፍራ ሁሉ ነበር የምንሰበሰበው ። ጊዜውን ጠብቆ ይፋ የሚወጣ ሥራን በኅቡዕ አዘጋጅተናል ። አንድ ጊዜ ደግሞ በየመንገዱ ላይ መሰብክ ጀመርን ። ሥራው ለችግር የሚያጋልጥ ቢሆንም በሌላ ዘዴ ለመድረስ የማንችለውን የወንጌል መልእክት ለብዙ ሰዎች ማዳረስ ችለናል ። ባለቤቴ በዚህ አገልግሎት ንቁ ተሣትፎ ነበራት ። ክርስቲያኖች በየመንገዱ ማዕዘን ላይ ይሰበሰቡና ይዘምራሉ ፣ ሕዝቡ መዝሙራቸውን ለማዳመጥ ሲሰበሰብ ባለቤቴ ደግሞ ስለክርስቶስ ትነግራቸዋለች ። ወዲያውኑ ግን እንበታተንና ወደየቤታችን እንሄዳለን ። እንደዚህ የምናደርገውም ራሳችንን ከሚሰጢር ፖሊሶች ለመጠበቅ ነበር ። አንድ ጊዜ ደግሞ እኔ በሌላ ስፍራ በማገለገልበት ወቅት ባለቤቴ በቡካሬስት ከተማ በነበረ ማላክሣ በሚባል ፋብሪካ መግቢያ በር ላይ ለነበሩ ሠራተኞች ስለ እግዚአብሔርና ስለ ደኅንነት ትነግራቸው ነበር ። በሚቀጥለው ቀን ሠራተኞቹ በኮሚኒዝም አማካይነት የደረሰባቸውን የፍትሕ መዛባት በመቃወም ሠላማዊ ሰልፍ በማድረጋቸው ብዙዎቹ አደባባይ ላይ በጥይት ተቆሉ ። ይሁን እንጂ ለዘለቄታው ሕይወት የሚያስፈልገውን መልእክት ጥቂት ቀደም ብለው አግኝተዋል ።

ዋናው አገልግሎታችን በኅቡዕ ቢሆንም ልክ እንደ መጥመቁ ዮሐንስ ሁሉ ለባለሥልጣኖችና ለተራ ሰዎችም ስለ ክርስቶስ በግልጽ እንናገር ነበር ።

አንድ ጊዜ ደግሞ ሁለት ክርስቲያን ወንድሞች እንደ ምንም ተሹሎክልከው አጠገቡ ደረሱና በጊዜው የሃገራችን ጠ/ሚኒስትር ለነበረው ጆርጅሁ ደጅ የወንጌልን እውነት መሰከሩለት ። በነበራቸው ጥቂት ደቂቃ ውስጥ ክርስቶስን እንዲቀበል ከኀጢአቱ እንዲመለስና አማኞችን ማሳደዱን እንዲያቆም ነገሩት ። በዚህም ድፍረታቸው ወህኒ እንዲወርዱ አደረጋቸው ። ይሁን እንጂ ከብዙ ዓመታት በኋላ ይኸው ጠቅላይ ሚኒስትር በጽኑ በታመመበት ጊዜ እነዚያ ሁለት ክርስቲያን ወንድሞች የዘሩት የወንጌል ዘር ፍሬ ሊያፈራ ችሎአል ። ተስፋ ያደረገው ነገር ሁሉ በከዳው ጊዜ የተነገረው የወንጌል ቃል ትዝ አለው ፡ “የእግዚአብሔር ቃል ሁለት አፍ ካለው ሠይፍ ይልቅ የተሳለና ልብን የሚወጋ ነው ።”

ከዚህም የተነሣ ከብዙ ጊዜ በፊት በተነገረው መሠረት ኃጢአቱን ተናዝዞ ክርስቶስን ከተቀበለ በኋላ ብዙ ሣይቆይ ሞተ ። እነዚያ ሁለት ክርስቲያ ኖች ከከፈሉት መስዋዕትነት የተነሣም በቅርቡ ወደ ተዋወቀው አዳኝ ሄደ።

ስለዚህ አገልግሎታችን ኅቡዕ ብቻ ሳይሆን አመቺ ሁኔታ ሲፈጠር በኮሚኒስቶች አደባባዮች ላይ መመስከርንና ለኮሚኒስት መሪዎችም የወንጌልን እውነት መናገርንም ያጠቃልል ነበር ። ለዚህ ግን ዋጋ እንከፍልበታለን ፤ ዋጋውን ለመክፈልም ዝግጁ ነበርን ።

የምትቃወማቸው እርሷ ብቻ መሆንዋን ስለተረዱ የምስጢር ፖሊሶች ይህችን በኅቡዕ የምትሠራ ቤተ ክርስቲያን ከፉኛ ይከታተሉዋ ትና ሊያጠፉዋት የሚችሉትን ሁሉ እያደረጉ ነበር ። በዚህ ሁኔታ ካልተዋጉዋትና ካላጠፉዋት በቀር ከእነርሱ ክህደት ትምህርት ይልቅ ተቀባይነትን እንደምታገኝና ጉልታ እንደምትታይ ያውቃሉ ። በክርስ ቶስ እውነተኛ እምነት ያለው ሰው አእምሮውን እንደማይጥልና እንደ ሌሎች ሁሉ ትምህርታቸውን አሜን ብሎ እንደማይቀበል አሳምረው ያውቁታል ። ስለዚህም እውነተኞችን አማኞች ለማጥፋት የማይፈነቅ ሉት ድንጋይ ፣ የማይሸርቡት ሴራ የላቸውም ። ኮሚኒስቶች ሰዎችን ማሠር ይችላሉ ፤ በእግዚአብሔር ያላቸውን እምነት ማሠር ግን አይች ሉም።

ሌላው ቀርቶ በራሳቸው በኮሚኒስት ባለሥልጣኖችና በምስጢር ፖሊሶች መካከል እንኳ ብዙ ወዳጆችና ደጋፊዎች ነበሩን ። አንዳንድ ክርስቲያኖችም እምነታቸውን በልባቸው ይዘው ከሕዝብ ደኅንነቶች ወይም ከሚስጢር ፖሊሶች ጋር አብረው እንዲሠሩ ስላደረግን ማንኛው ንም ምስጢር ይነግሩናል ። ይህንን የማያውቁት አንዳንድ ክርስቲያኖችና ዘመዶቻቸው ግን ከሕዝብ ደኅንነት ጋር በመሥራታቸው ይጠሉዋቸ ዋል።

እኔ ራሴ ከመንገድ ታፍኜ ከተወሰድሁ በኋላ ማንም ያለሁበትን አያውቅም ነበር ፣ አንድ ክርስቲያን ዶክተር ግን የት እንደገባሁ ለማወቅ ሲል ከሕዝብ ደኅንነቶች ጋር አብሮ ሠርቶአል ፤ የሚሠራው ከሚስጢር ፖሊሶች ጋር እንደመሆኑ መጠን ማንኛውም እሥር ቤት ውስጥ የመግባት ነፃነት ነበረው ።

ይህን ያልተረዱ ክርስቲያኖች ግን ኮሚኒስት የሆነ መስሎአቸው ሸሹት ። የእሥረኞችን ዩኒፎርም ከመልበስ ይልቅ የሚሰጢር ፖሊሶችን ዩኒፎርም ለብሶ መታየት በጣም የሚያሣፍር ቢሆንም አንዳንድ ክርስቲያ ኖች ግን ሌሎች ክርስቲያኖችን ለመርዳት ሲሉ ይህንን ዩኒፎርም ለብሰዋል ። ይህም ትልቅ መስዋዕትነት ነው ።

ይህ ዶክተር ከብዙ ፍለጋ በኋላ በአንድ ጠባብና ጨለማ ክፍል ውስጥ አገኘ። ሞተ ብለው ተስፋ ቆርጠው ለነበሩ ወገኖቼም በሕይወት መኖሬን የተናገረው እርሱ ነው ። ብዙ ዓመታት ከታሠርኩ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ያገኘሁት ክርስቲያን ጓደኛ ይህንን ዶክተር ነው ። በሕይወት መኖሬን ለመጀመሪያ ጊዜ የተናገረውም እርሱ ነው ። ከዚያ በኋላ በአይዘንአወርና በክሩስቾቭ መካከል ከተደረገው ድርድር የተነሣ ብዙ እሥረኞች በተፈቱበት ወቅት በሌሎች እሥረኞች አማካይነት በሕይወት መኖሬ ይፋ ወጣ ። ክርስቲያኑ ማኅበረ–ሰብ ካቀረበው አቤቱታ የተነሣም ለአጭር ጊዜ ተፈታሁ ።

እኔን ፈልጎ ለማግኘት ብሎ ይህ ክርስቲያን ዶክተር ከሕዝብ ደኅንነቶች ጋር ባይሠራ ኖሮ አልፈታም ነበር ። ምናልባትም እንደታሠ ርኩ ልሞት እችል ነበር ።

እነዚህ ከሕዝብ ደኅንነት ጋር የሚሠሩ ክርስቲያኖች ማንኛውም ችግር ከመምጣቱ በፊት ያስጠነቅቁናል ። አንዳንዶቹ ከፍተኛ ኮሚኒስት ባለሥልጣኖች ቢሆኑም በልባቸው ግን በክርስቶስ የሚያምኑ ክርስቲያን ወንድሞች ናቸው ። እንዲህ ዓይነት ወገኖች መኖራቸው ብዙ ጠቅሞናል። ዛሬ በስውር ያገለገሉት ጌታ አንድ ቀን በሰማይ ዋጋቸውን በግልጽ ይከፍላቸዋል ። ይህም ሁሉ ሆኖ እንኳ ብዙ ክርስቲያኖች ከመታሠር አላመለጡም ። በመካከላችን ሆነው በክርስቲያኖች ላይ የሚጠቁሙ “ይሁዳዎች” ነበሩብን ።

# ምዕራፍ ሁለት

## "ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ማንም የለውም.."

እስከ የካቲት 29/1948 ድረስ በጎቡዕ ወንጌልን ከምታስፋፋውና የመንግሥት ፈቃድ ካላት ቤተ ክርስቲያን ጋር ነበር የማገለግለው ። ቀኑ እሁድ ነበር ፤ ደስ የሚል እሑድ ። በዚያኑ ዕለት ወደ ቤተ ክርስቲያን በመሄድ ላይ እያለሁ በሕዝብ ደኅንነት ሠራተኞች ከመንገድ ላይ ታፍኜ ተወሰድሁ ። እስከ አሁን ንብረት ሲዘረፍ ነበር የምናውቀው ፣ ኮሚኒዝም ግብ ንብረቱን ሳይሆን ሰውየውን ራሱን ከነነፍሱ መዝረፍ ምን እንደሆነ አስተምሮናል።

ከዚያ በፊት ብዙዎች በተመሳሳይ ሁኔታ ታፍነው መወሰዳቸውን እናውቃለን ። ሳላስበው አንድ ሽፍን መኪና እፊቴ ቆመ ። አራት ሰዎች እየዘለሉ ወጡና እየገፈታተሩ ወደ ውስጥ አስገቡኝ ። ከዚያ ወዲህ ለስምንት ዓመት ተኩል ያህል ልሙት ወይም በሕይወት ልኑር ማንም አላወቀም ። በቅርቡ ከእሥር ቤት የወጡ በመምሰል ወደ ባለቤቴ ሄደው መሞቴን አረዱአት ። ይህን ያደረጉት ራሳቸው የሕዝብ ደኅንነቱ አባሎች ናቸው ። የባለቤቴም ልብ በኀዘን ተሰበረ ፣ በዚያ ዘመን ከየትኛውም የእምነት ድርጅት በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች ታሠሩ ። የሚታሠሩት ካህናቱ ብቻ ሣይሆኑ እምነታቸውን ሲያስፋፉ የተገኙ አርሶ አደሮች ፣ ወጣቶችና ልጃገረዶች ጭምር ናቸው ። የሩማንያ ወህኒዎች ከምን ጊዜውም ይልቅ ከመጠን በላይ በእሥረኞች ተጨናንቀዋል ።

የደረሰብን ስቃይ ልገልጽ ከምችለው በላይ በመሆኑ ባልናገረው ይሻላል ። ዛሬም ቢሆን ሳነሣው ይዘገንነኛል ። ስለዚህ ጉዳይ ሰፋ ባለ ሁኔታ ለማወቅ ከፈለጋችሁ "ኢንጎድስ አንደር ግራውንድ" የሚለውን መጽሐፌን እንድታነቡ አሳስባችኋለሁ ።

ይህ ነው የማይባል ፍዳ...

አንድ ፍሎሬስኩ የሚባልን ፓስተር በእሣት በጋለ ቢላዋ እየጠበሱ

አሠቃዩት ፣ ከፉኛ ደበደቡት ፤ ይህም አልበቃ ብሎአቸው እነበረበት ክፍል ውስጥ የተራቡ ዓይጦች በብዛት እንዲገቡ ተደረገ ። ሌሊቱን ሁሉ እንቅልፉን አጥቶ አይጦቹን መከላከል ነበረበት። ትንሽ ሸለብ ካደረገው ግን አይጦቹ ይነክሱታል ።

ለሁለት ሣምንት ያህል ቀንና ሌሊት እንዲቆም ተደረገ ። ይህ ሁሉ የደረሰበት ሌሎች ክርስቲያን ወንድሞችን አሣልፎ እንዲሰጥና ስለ ሥራ እንቅስቃሴአቸውም እንዲጠቁማቸው ያቀረቡትን ጥያቄ ባለመቀበሉ ነበር ። እርሱ ግን ፍንክች አላለላቸውም ። በመጨረሻም የአሥራ አራት ዓመት ልጁን አስመጥተው የሚፈልጉትን እስኪነግራቸው ድረስ እፊቱ ይገርፉት ጀመር ። በልጁ ስቃይ እንደ እብደት ያደረገው አባት "አሌክሣንደር ስቃይህን ማየት አልችልም የሚፈልጉትን ልናገር ነው" አለ ። ልጁ ግን በእምነቱ እንዲፀና ነበር ለአባትየው የመለሰለት በዚህ በጣም የተናደዱት ኮሚኒስቶችም እስኪሞት ድረስ ልጁን ደበደቡት ። ደሙም በግድግዳዎቹ ላይ ተፈናጠቀ ።

ሆኖም እግዚአብሔርን እያከበረ ነበር የሞተው ። ይህን ካየ በኋላ የወንድማችን ፍሎረስኩ እምነት ከመድከም ይልቅ በይበልጥ በረታ ።

ከውስጥ በኩል መውጊያዎች ያሉት ካቴና እጆቻችን ላይ ይደረጋል። እነዚህ መውጊያዎች እስካልተንቀሣቀስን ድረስ ብዙ አያሰቃዩንም፤ በተንቀሣቀስን ቁጥር ግን ሚስማሮቹ ቆዳችንን ጠልቀው ይገባሉ ።

ክርስቲያኖች ተዘቅዝቀው ይታሠሩና ይገረፋሉ ፤ ከዚያ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀ ማቀዝቀዣ (ፍሪጅ) ውስጥ ይከተታሉ ። እኔ ራሴ በዚህ ማቀዝቀዣ ውስጥ ገብቼአለሁ ። ከቅዝቃዜው የተነሣ ልንሞት ስንል ይህንኑ ለመከታተል የተመደቡ ዶክተሮች ለዘበኞቹ ማስጠንቀቂያ ይሰጧቸዋል ። ከዚያም ከማቀዝቀዣው ያወጡንና ሙቀት እንድናገኝ ያደርጉናል ። ሰውነታችንን በሙቀቱ መጋል ሲጀምር ደግሞ እንደገና ወደ ፍሪጁ ያገቡናል ። ነፍሳችን ልትወጣ ሁለት ወይም ሶስት ደቂቃ ሲቀራት ደግሞ ያወጡንና ሙቀት እንድናገኝ ያደርጋሉ ። ይህ ሁኔታ ቀኑን በሙሉ ሲፈራረቅብን ይውላል ። ከስቃዬ ጽናት የተነሣ ዛሬም እንኳ ቢሆን እቤቴ ውስጥ ያለውን ማቀዝቀዣ መንካት ይሰቀጥጠኛል ።

ከቁመታችን ጥቂት የሚበልጥ ሣጥን ውስጥ እንከተታለን ፣ ሣጥኑ ምንም መንቀሣቀሻ የለውም ። ቀጥ ብለን እስከቆምን ድረስ ምንም ችግር የለብንም ግን ምን ያህል ሰዓት ቀጥ ብሎ መቆም ይቻላል ? ከመድከማችን

የተነሣ ሣጥኑን ከተደገፍነውም ውስጠኛው ክፍል ዙሪያውን ያሉት ሹል ሚስማሮች ሰውነታችንን ይወጉናል ። ቀጥ ብለን ለመቆም ይደክመናል እንዳንቀመጥ ደግሞ ሣጥኑ በጣም ጠባብ ነው ። ጥቂት ደገፍ ካልን ሹል ሚስማሮቹ ሰውነታችንን ይቀረድዱታል ።

ኮሚኒስቶች ክርስቲያኖች ላይ ያደረሱትን ስቃይ የሰው አእምሮ ሊቀበለው ከሚችለው በላይ ነው ።

ኮሚኒስቶች ክርስቲያኖችን ሲያሰቃዩ አይቼአለሁ ፤ እኔም ራሴ ከተሰቃዩት አንዱ ነኝ ። ግን ከሚያሰቃዩት ይልቅ የሚሠቃዩት ክርስቲያ ኖች ፊት ፈገግታ ያለው መስሎ ይታየኛል ። ክርስቲያኖችን ሲያሰቃዩ “እኛ ዲያብሎሶች ነን” እያሉ ነው ።

ቅዱስ መጽሐፍ እንደሚለው መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር ሳይሆን ከክፉት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው ። ኮሚኒዝም የሰው ሥራ ሳይሆን የራሱ የዲያብሎስን ሥራ መሆኑን ከደረሰብን ስቃይ አረጋግጠ ናል ። ኮሚኒዝም ክፉ መንፈስ ነው ። ክፉ መንፈስ የሚሸነፈው ደግሞ ከእርሱ በሚበልጥ መንፈስ ማለትም ፣ በእግዚአብሔር መንፈስ ነው ።

አንዳንድ ጊዜ እነዚህ ሰውን በማሠቃየት እርካታ የሚያገኙ ገራፊዎች– “ለመሆኑ ሰውን ያህል ፍጡር እንደዚህ ስታሰቃዩ ምንም ሃዘን አይሰማችሁም ?” በማለት እጠይቃቸዋለሁ ። እነርሱ ግን ፦ ጥሩ የእንቁላል ጥብስ ለመብላት አስቀድሞ ቅርፊቱ መሰበር አለበት” “ግንድ ሲቆረጥ ጥቃቅን እንጨቶች መፈናጠራቸው አይቀርም” በማለት ሌኒን የተናገረውን ነበር የሚመልሱልኝ ። እኔም “ይህን የምትሉትን የተናገ ረው ሌኒን እንደሆነ አውቃለሁ ፤ ታዲያኮ በሰው ልጅና በግንድ መካከል ከፍተኛ ልዩነት አለ ። እንጨት ሕመም አይሰማውም ። እናንተ አሁን የምታሰቃዩት ግን የሰው ልጅን ነው ፤ እያንዳንዷ በትር ታምማለች ፤ ብዙ የሚያለቅሱ እናቶች መኖራቸውን መዘንጋት የለባችሁም አልኳቸው ። የተናገርኩት ግን ልባቸው አልደረሰም ። ማቴሪያሊስቶች ናቸው ፤ ለማቴሪያሊስቶች ደግሞ ሰው ከግንድና ከእንቁላል ተለይቶ አይታይም ። ማቴሪያሊስት መሆናቸው ለጭካኔያቸው ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው ። የኤቲስቶችን (እግዚአብሔር የለም የሚሉ ሠዎች) ጭካኔ በቃላት ለመግለጽ አዳጋች ነው ። አንድ ሰው ለመልካም ሥራዬ ዋጋ አገኝበታ ለሁ፤ ለክፉ ሥራዬ ደግሞ እቀጣበታለሁ ፤ የሚል እምነት እስከሌለው

ድረስ ምንም ሰብአዊነት ሊሰማው አይችልም ። በልቡ የታመቀውን ዓመፅ እንዳያወጣው የሚያግደው ነገር አይኖርም ። ኮሚኒስቶቹ—"እግዚ አብሔር የለም ፤ ከዚህ በኋላ ሕይወት ስለሌለ ለመልካም ሥራ ሽልማት ፥ ለክፉ ሥራም ቅጣት የለም ፤ የፈለግነውን ማድረግ መብት አለን" በማለት አዘውትረው ይናገራሉ ። አንድ ጊዜ ደግሞ በእግዚአብሔር የማያምን ሰው "እንደልቤ ክፉ ነገርን እንዳደርግ እስከዚህች ሰዓት ድረስ ያቆየኝ የማላምንበት እግዚአብሔር ክብር ምሥጋና ይግባው" በማለት ሲያፌዝ ሰምቼዋለሁ ። ስለዚህም ምንም ሀዘን ወይም ቅሬታ ሳይሰማው ይህ ነው በማይባል ግፍ እሥረኞችን ያሰቃያል ።

አዞ ሰውን ቢበላ በጣም አዝናለሁ ፤ ሆኖም ሞራላዊ ፍጡር ባለመሆኑ አዞውን አልወቅሰውም ። ልክ ይህንኑ በሚመስል ሁኔታ ኮሚኒስቶችንም መውቀስ ያስቸግራል ። ኮሚኒዝም ሞራላዊ ሕግን በልባቸው አጥቦ አውጥቶታል ። እንዲያውም በጭካኔያቸው ሲኩሩበት ነው ያየኋቸው ።

ከእነርሱ የተማርሁት አለኝ ፤ በልባቸው ለክርስቶስ ምንም ቅንጣት ታህል ሥፍራ እንደነፈጉት ሁሉ እኔም ለሰይጣን ቅንጣት ታህል ስፍራ ላለመስጠት ወስኜአለሁ ።

በኮሚኒስቶች ክርስቲያኖች ላይ የሚደርሰውን ጭካኔ በአሜሪካ ሴኔት ንዑስ ኮሚቴ አባላት ፊት ቀርቤ ተናግሬአለሁ ። ክርስቲያኖች ለአራት ቀንና ሌሊት ያህል በመስቀል ላይ ታስረው እንዲሰቃዩ መደረጋቸውንም ገልጬአለሁ ። በመስቀል መሬት ላይ ይታሠሩና በታሠሩት ክርስቲያኖች ደግሞ እሥረኞቹ እንዲሸኑባቸው ይደረጋል ። እንደገና መስቀሉ እንዲቆም ይደረግና "እዩት የእናንተ ክርስቶስ ሲያ ምር፤ እንዴት ያምራል" እያሉ ያፌዙባቸዋል ። አንድ ቄስ በስቃይ ሕሊናውን እንዲስት ከተደረገ በኋላ የገዛ ሠገራውን ቅዱስ ቁርባን ነው ብሎ ለክርስቲያኖች እንዲሰጥ አስገድደውታል ። ይህ የሆነው ፒቴ ስቲ በሚባል የሩማንያ እሥር ቤት ውስጥ ነው ። በኋላም ያንን ቄስ ይህን ከምታደርግ ለምን ሞትን አልመረጥህም ነበር" በማለት ላቀረብሁለት ጥያቄ—"አትፍረድብኝ ከራሱ ከክርስቶስ ይበልጥ ተሰቃይቼአለሁ" በማለት ነበር የመለሰልኝ ። በገሃነም ውስጥ ስላለው ስቃይ ከመጽሐፍ ቅዱስና ከዳንቴ ኢንፌርኖ አንብቤአለሁ ። በኮሚኒስቶች እሥር ቤት

ያለውን ስቃይ ግን ልገልጽ ከምችለው በላይ ነው ። ይህን ሁሉ ነው እንግዲህ በአሜሪካ ሴኔት ንዑስ ኮሚቴ ፊት የመሰከርሁት ።

ይህ ፔቲስቲ በሚገኘው እሥር ቤት በየእሁድ ቀን ከሚደረገው ግፍ አንዱ ሲሆን የተቀረውን ግን መናገር አልፈልግም ። በጽሑፍ ማስቀመጡ ራሱ ራሱን የቻለ ስቃይ ያሳድርብኛል ። በኮሚኒስት እሥር ቤቶች የሚሰቃዩ ክርስቲያን ወንድሞቻችሁና እህቶቻችሁ መከራ ይህን ይመስ ላል ።

በጣም ከማደንቃቸው የእምነት አርበኞች አንዱ ፓስተር ሚላን ሀይሞቪቺ ነው ።

ከእሥረኞቹ ብዛት የተነሣ ዘበኞቹ በየስማችን አያውቁንም ። የእሥር ቤቱን ደንብ ተላልፋችኋል በመባል ሃያ አምስት ጅራፍ እንዲገረፉ የተፈረደባቸው እሥረኞች ተጠሩ ። ፓስተር ሚላን ሃይሞቪቺ ስለ ሌሎች ብዙ ጊዜ ሲገረፍ ተመልክቼአለሁ ። ይህ ሰው በጣም የተከበረ ከመሆኑም ሌላ ለእኛ ለእሥረኞቹም መኩሪያ ሆኖአል ። ያመነበትን ጌታ ክርስቶስንም አስከብሮአል ።

ኮሚኒስቶች ያደረሱብንና ስቃይና ክርስቲያኖች የሚከፍሉትን መስዋዕትነት ዘርዝሬ አልጨርሰውም ። ስቃዩን ዓይነት ብቻ ሳይሆን፣ ስቃዩን በጽናት የተቋቋሙ ጀግኖችንም ታሪክ ማቅረብ ይቻላል ። የእነዚህ ሰዎች ታሪክ ሌሎችንም ያበረታል ።

በኀቡዕ ወንጌልን የምታስፋፋ ቤተ ክርስቲያናችን አባል የሆነች አንዲት ልጃገረድ ነበረች ። ወንጌልን እንደምታሠራጭና ሕፃናትን ስለ ክርስቶስ እንደምታስተምር ኮሚኒስቶች ቢደርሱበትም ስቃይዋን ይበ ልጥ መራራ ለማድረግ እስከ ሠርጓ ቀን ድረስ ጠበቋት ። የምታገባው በቅርቡ ነበር ። የሠርጓ ዕለት የሙሽራ ልብሷን ለብሳለች ማንኛችንም ብንሆን የሠርግ ቀን በልጃገረድ ሕይወት ውስጥ የከፍተኛ ደስታ ቀን መሆኑን እናውቃለን ። በድንገት የሕዝብ ደኅንነቶች ወደ ክፍሉ ገቡ ። ሙሽሪት ሰዎቹን ስታያቸው ገና ሁለት እጆችዋን ለእሥራት አዘጋጅታ ነበር የጠበቀቻቸው ። ያጠለቁላትን የእጅ ካቴና "ሰማያዊው ሙሽራ የላከልኝ ስጦታ በማለት ሳመችው ። ኮሚኒስቶቹ ግን እያዳፉ ወሰዱ አት። በኮሚኒስቶች እጅ የገባች ልጃገረድ እሥረኛ ምን እንደሚደርስባት ስለሚያውቁ በስፍራው የነበሩት ሁሉ ተላቀሱ ። ከአምስት ዓመት በኋላ

እንዳልሆነ ሆና ተፈታች ። ያለ እድሜዋ ገርጅፋ ፣ የሠላሣ ዓመት ሴት ብትመስልም እርስዋ ግን ክርስቶስ ከተቀበለው መከራ አንፃር የደረሰባት በጣም ጥቂት እንደሆነ ትናገራለች ። ሙሽራውም እርስዋን ሲጠብቅ አላገባም ።

እእምሮ ጠረጋ (ብሬን ዎሺንግ) ምንድን ነው ...?

በኮርያ ፣ በቪየትናምና በሌሎችም ጦርነቶች ስለ ተደረገው አእምሮ ጠረጋ ሰምተን ይሆናል ። እኔ ግን ብሬንዎሺንግን የማውቀው በወሬ ሳይሆን ራሴ ብሬንዎሽ ተደርጌአለሁ፤ እጅግ አሰቃቂ ነው።

ለብዙ ሰዓት ያህል — ኮሚኒዝም ጥሩ ነው ፤

ኮሚኒዝም ጥሩ ነው !
ኮሚኒዝም ጥሩ ነው !
ኮሚኒዝም ጥሩ ነው !
ክርስትና መጥፎ ነው !
ክርስትና መጥፎ ነው !
ክርስትናችሁን ተውት !
ክርስትናችሁን ተውት !
ክርስትናችሁን ተውት !
ክርስትናችሁን ተውት !

የሚሉትን ቃላት ለሳምንትና ለወራት በተደጋጋሚ እንድንሰማ ይደረጋል ።

ብዙ ክርስቲያኖች ብሬንዎሺንግን እንዴት እንደተቋቋምነው ይጠይቁኛል ፤ ብሬንዎሺንግን መቃወም የሚቻለው ልብን ከማንኛውም ቁምና ጥላቻ በማፅዳት ብቻ ነው ። የአንድ ሰው ልብ በኢየሱስ ፍቅር ታጥቦ ከነፃ ፣ ክርስቶስን በሚገባ የሚወደው ከሆነ ፣ በማንኛውም አይነት መከራ ውስጥ ማለፍ ይችላል ። ሙሽሪት ለሙሽራዋ ምን የማትሆንለት ነገር አለ ? እናት ከልጅዋስ ምን የምትደብቀው ይኖራታል ? እናቱ ማርያም ትወደው እንደነበር ሁሉ ክርስቶስን ከወደድነው ፣ ሙሽሪት ሙሽራውን እንደምትወደው ሁሉ ከወደድነው ፣ ማንኛውንም ነገር ተቋቁመን ማለፍ እንችላለን ።

በእግዚአብሔር ፊት የሚመዘነው ምን ያህል ማፍቀራችን እንጂ፣ ምን ያህል መከራ መቀበላችን አይደለም ። በኮሚኒስት እሥር ቤት ያሉት

ክርስቲያኖች እግዚአብሔርንና ሰዎችን የሚወድዱ ለመሆናቸው ምስክር ነኝ ።

ስቃያችን ያለማቋረጥ ቀጠለ ፤ ከስቃዩ የተነሣ ሕሊናዬን ስቼ ስዘረር ወይም ደግሞ ከእኔ የሚፈልጉትን ምንም ፍንጭ ካላገኙ እንደገና ወደ እሥር ቤቱ ይመልሱኛል ። በእሥር ቤቱ ውስጥ ምንም ጥንቃቄ ሣይደረግልኝ ለጥቂት ሰዓት ተዘርሬ ከቆየሁ በኋላ ማንሠራራት ስጀምር ማሰቃየታቸውን እንደገና ይጀምራሉ ። በዚህ ሁኔታ ብዙዎች ሞተዋል። የእኔ ነፍስ ግን አልወጣ አለች ። ከእሥር ቤት ወደ እሥር ቤት ተንገላትቻለሁ ። ከደረሰብኝ ከባድ ድብደባ የተነሣ አራት የጀርባ አጥንቶቼና ሌሎች አጥንቶቼ ተሰብረዋል ። አሥራ ስምንት ቦታ በእሣት ጠብሰውኛል ጠባሣዎቹም ዛሬም ቢሆን አብረውኝ ናቸው ።

በኖርዌይ ዋና ከተማ አስሎ ያሉ ዶክተሮች እነዚህንና በሳምባዬ ላይ ያለውን ቁስል ከመረመሩ በኋላ በሕይወት መኖሬ ራሱን የቻለ ተአምር እንደሆነ ተናግረዋል ። እነርሱ እንደነገሩኝ ወይም ደግሞ የሕክምና ጥበባቸው እንደሚለው ከሆነ ገና ድሮ መሞት ነበረብኝ ። እኔ ራሴም ብሆን በሕይወት ልኖር የቻልኩት በተአምር እንደሆነ አውቃለሁ። እግዚአብሔር የተአምራት አምላክ ነው ።

እግዚአብሔር ይህን ተአምር ያደረገው በኮሚኒስት አገር ክርስቲያ ኖች ላይ የሚደርሰውን ስቃይ ለእናንተ መግለጽ እንድችል እንደሆነ እርግጠኛ ነኝ ።

## ከእሥር ነፃነት በኋላ እንገደና ስለመታሠሬ ፤

ወቅቱ 1956 ሲሆን ፣ በእሥር ያሳለፍኩት ጊዜ ስምንት ዓመት ተኩል ሆኖታል ፣ የሰውነቴ ክብደት ከመጠን በላይ ቀንሶአል ። በጭካኔ ተደብድቤአለሁ ፤ ሰውነቴ እስኪዝል ተርቤአለሁ ፣ ሌላም የተለያየ ግፍ ተደርጐብኛል ። ሆኖም ግን ከእኔ የሚፈልጉትን ሊያገኙ ባለመቻላቸው በነፃ ለቀቁኝ ። ከእሥር እንዲፈቱኝም ብዙ ተቃውሞ ተደርጐባቸዋል ።

ለአንድ ሳምንት ያህል ወደ ቀድሞ ቦታዬ ተመለስኩ ። በዚህ ጊዜ ውስጥ ሁለት ጊዜ ሰብኬአለሁ ። በኋላ ግን አስጠርተው መስበክ ወይም በማንኛውም ዓይነት ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴ መሳተፍ እንደሌለብኝ

ነገሩኝ ። ስለዚህም የመንግሥት ፈቃድ ካላቸው ቤተ ክርስቲያኖች ጋር መሥራት ስላልቻልኩ በኅቡዕ ማገልገል ጀመርኩ ። እግዚአብሔር የለም የሚሉ ኮሚኒስቶች ምን ያህል ጨካኝ እንደሆነ ምስክሩ በሰውነቴ ላይ ያሉት ጠባሣዎች ናቸው ፤ ይህንን ማስረጃ በማቅረብ አማኞች ይበልጥ በእግዚአብሔር እንዲታመኑና በእምነት እንዲበረቱ መናገር ያዝኩ ። በሚስጢር ወንጌልን የሚያስፋፉ ወንጌላውያንን አሰማራሁ ። ብዙ ጊዜ ከሚከታተሉን ኮሚኒስቶች ዓይን እግዚአብሔር ሰውሮናል ። የእግዚአብ ሔርን ሥራ ሊያዩ ያልቻሉ ዓይኖች እንዴት የወንጌላውያንን ሥራ ማየት ይችላሉ !

ከብዙ ክትትል በኋላ እንደገና ታሠርሁ ። በሕብረተሰቡ ዘንድ እውቅናን ስላገኘሁ በአሁኑ ጊዜ ግን ቤተሰቦቼን አላሰሩአቸውም ። ስምንት ዓመት ተኩል ታሠርኩ ለሶስት ዓመት ደግሞ በአንፃራዊ ነፃነት መንቀሣቀስ ቻልኩ ። አሁን ደግሞ ተጨማሪ ለአምስት ዓመት ተኩል ተፈረደብኝ ።

ሁለተኛው እሥራት ከመጀመሪያው ይብሳል ። የጤንነቴ ሁኔታ ከምን ጊዜውም ይልቅ ተባባሰ ፤ የምጠብቀው ሞቴን ነበር ። ሆኖም በእሥር ቤት ውስጥ ሆነን እንኳ የኅቡዕ ወንጌል ማስፋፋት አገልግሎታችንን አላቋረጥንም ።

እኛ እንሰብካለን ፤ እነርሱም ይደበድቡናል ። በእሥር ቤት ውስጥ ወንጌልን መስበክ በጥብቅ የተከለከለ ነው ። ወንጌልን ሲሰብክ የተገኘ አይቀጡ ቅጣት እንደሚደርስበት እናውቃለን ። በልባችን ከኮሚኒስቶቹ ጋር አንድ ውል አደረግን ፤ ይኸውም — እኛ ልንሰብክ ፤ እነርሱ ደግሞ ሊደበድቡን ። እኛ መሰበኩ ደስ የሚለንን ያህል ለእነርሱ ደግሞ መግረፉ ያስደስታቸዋል ። ስለዚህም ሁለታችንም ደስተኞች ነን ማለት ነው !

አንድ ጊዜ አንድ ወንድም ለእሥረኞች ጓደኞቹ በመስበክ ላይ እያለ፣ ዘበኛው በድንገት በሩን በርግዶ ገባ ፤ እያዳፋና መሬት ለመሬት እየጐተተ ወደ መግረፊያው ክፍል (ቶርች ማድረጊያ) ይዘውት ሄዱ ። ብዙ ከደበደቡት በኋላ ሕሊናውን በመሳቱ እየጐተቱ እንደወሰዱት ሁሉ እየጐተቱ አመጡና በእሥር ቤቱ ወለል ላይ ዘረሩት ። ሕሊናውን ሲያውቅ እያቃሰተ እንደምንም ቀና አለና “ይቅርታ ፤ ወንድሞቼ ቅድም ስብከቴን ምን ላይ ነበር ያቆምሁት ? በማለት እንደገና ስብከቱን ቀጠለ።

እንዲህ ዓይነት ሁኔታዎችን አይቼአለሁ ። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ወንጌልን ሲሰብኩ የምመለከታቸው ተራ ምዕመናን ናቸው ። በመንፈስ ቅዱስ የተነሳሱ ተራ ሰዎች የሚሰብኩት ስብከት ብዙ ጊዜ ልብ ይነካል ። ምንም ሃሣባቸውን የሚከፋፍል ነገር ባለመኖሩ የሚሰብኩት በሙሉ ልባቸው ነው ። ዘበኞቹ ደግሞ ሲሰብኩ ያገኟቸውን ሕሊናቸውን እስኪስቱ ድረስ ይገርፏቸዋል ።

ግሔራ በሚባለው እሥር ቤት ውስጥ አንድ ክርስቲያን ተደብድቦ እንዲገደል ተፈረደበት ። ሕይወቱ እስክትወጣ ድረስ ግን ጥቂት ማምንታት መሰቃየት ነበረበት ። ቀስ በቀስ ነበር የሚያሠቃዩት ። ውስጥ እግሩን ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀ ጐማ ከተገረፈ በኋላ ይተውታል ። ከዚያ በኋላ ደግሞ እንደገና ይገርፉታል ። አባለ ዘሩን ይመቱታል ። ከዚያ ደግሞ ሕክምና ይደረግለታል ። ጥሩ ጥሩ ምግብ ይሰጡና እንዲያገግም ይደረጋል ። እንደገና ደግሞ ይደበደባል ። ይህ የሚቀጥለው እስከሚሞት ድረስ ነው ። ይህን ፍርድ የፈረደው ሬክ የሚባል የማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ነበር ።

እንደሌሎች ኮሚኒስቶች ሁሉ ሬክ "እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ በሕይወታችሁም ሆነ በሞታችሁ ሥልጣን አለኝ ፤ በሰማይ አለ የምትሉት እግዚአብሔር ምንም ማድረግ አይችልም ፤ ከፈለግሁ በሕይወት ትኖራላችሁ ፤ ካልፈለግሁ እገድላችኋለሁ ፤ እግዚአብሔር ነኝ" በማለት ክርስቲያኖች ላይ የሚሳለቅ ሰው ነው ።

ወንድማችን ግሬኩ በእንዲህ አይነት መከራ ሆኖ ለሬክ እንዲህ የሚል መልስ ሰጠው — አላወቅኸውም እንጂ በጣም እውነተኛ ነገር ነው የተናገርከው ፣ በእግዚአብሔር አምሳል ነበር የተፈጠርከው ፣ የተፈጠርከው ም ሰዎችን እንድታሰቃይ ወይም እንድትገድል አልነበረም፤ ተፈጥሮህን ለተሳሳተ ዓላማ አውለኸዋል ። ኢየሱስ ራሱ በዘመኑ ለነበሩት አይሁዳውያን "አማልክት ናችሁ" ብሎአቸዋል ። አምላካዊ ባሕርይ በውስጥህ ነው ያለው ። ስንት የተሻለ ነገር ማድረግ ሲችሉ እንደአንተ ወይም እንደሐርያው ጳውሎስ ሰዎችን ሲያሣድዱ የነበሩ በድርጊታቸው አፍረው በታል ። ተጸጽተውበታል ። ከክፉ ሥራቸውም ተመልሰው የመለኮታዊው ባሕርይ ተካፋይ ሆነዋል ። ስለዚህ ሚስተር ሬክ ብታምነኝም ባታምነኝም የተፈጠርከው የመለኮታዊው ባሕርይ ተካፋይ እንድትሆን

እንጂ ሰዎችን እንድታሰቃይ አልነበረም” አለው ። ጊዜ ካለፈ በኋላ ይህን የነገረኝ ራሱ ሬክ ነው ።

ምንም እንኳ እስጢፋኖስ ሲገደል የሰጠውን ምስክርነት ቢሰማና ቢያይም የጠርሴሱ ሳውል እንዳላስተዋለ ሁሉ ይህም ሰው የተነገረውን ለመቀበል አልፈለገም ነበር ። ይሁን እንጂ የሰማቸው ቃላት ፍሬ ማፍራቱ አልቀሩም ። ስለዚህም ከብዙ ጊዜ በኋላ ፤ የተፈጠረው በእውነትም የመለኮት ባሕርይ ተካፋይ ለመሆን እንደነበር ሊረዳ ችሎአል ።

ከሚኒስቶች ከሚያደርሱብን ድበደባና ስቃይ የተረዳነው ትልቁ ቁም ነገር ቢኖር ፣ መንፈስ በሥጋ ላይ የበላይ ወይም ጌታ መሆኑን ነው ። በእርግጥ ስንሰቃይ ያምመናል ፤ ግን ከእውነተኛው እኛነታችን ማለትም ከመንፈሳችን በጣም ርቆ ነበር የሚሰማን ። እውነተኛው እኛነታችን (መንፈሳችን) ግን በክርስቶስ ክብር ተውጦአል ።

በየሳምንቱ ከሚሰጠን የዳቦ ቁራጭና በየዕለቱ ከሚሰጠን ሾርባ “አሥራታችንን” በታማኝነት እናወጣ ነበር። በየአሥረኛው ሳምንት የሚታደለንን የዳቦ ቁራጭ ከእኛ በጣም ለባሰባቸውና በጣም ለደከሙ ወንድሞች ማገገሚያ እንዲሆን እንሰጣቸዋለን። ለጌታ የምንሰጠው “አሥራት” መሆኑ ነው።!

አንድ ክርስቲያን እንዲገደል ተፈረበት። ከመሞቱ በፊት ግን ሚስቱን እንዲያይ ተፈቅዶለት ነበር። ለሚስቱ የተናገረው የመጨረሻ ቃል ግን “የምሞተው የሚገድሉኝን ሰዎች እየወደድሁ እንደሆነ እንድታውቂ እፈልጋለሁ፡ የሚያደርጉትን አያውቁም ፣ ለአንቺም ቢሆን የምተውልሽ ምክር ቢኖር፡ እንድትወጃቸው ነው ባልሽን ስለገደሉብሽ ቂም አትያዢባቸው። በሰማይ እንገናኛለን” የሚል ነበር። ይህ አነጋገር በአጠገባቸው ቆሞ ይሰማ የነበረው ሹም ልብ ስለነካው እርሱ ራሱ ጌታን ተቀበለ ። ክርስቲያን በመሆኑ ታስሮ በነበረበት ጊዜ ነው ይህንን የነገረኝ።

ቲርጉ ኦሲና በሚባል እሥር ቤት አንድ ማቼቪቺ የሚባል የአሥራ ስምንት ዓመት ወጣት ታስሮ ነበር። ከስቃዩ የተነሣ ሳምባ ነቀርሣ ያዘው። ቤተሰቡ መታመሙን ስለሰሙ አንድ መቶ ብልቃጥ ስትሮፕቶማይሲን ላኩለት። ይህ መድሃኒት ለሞቱ ወይም ለሕይወቱ ሊሆንለት ይችል ነበር። የእሥር ቤቱ ፖለቲካ ክፍል ሃላፊ ይህንን ወጣት አስጠራውና “ይህ

መድሃኒት ከሕመምህ ሊያድንህ ይችላል። እንደ እውነቱ ከሆነ ከቤተሰ ብህ ምንም ነገር መቀበል አልነበረብህም። በበኩሌ ልረዳህ እፈልጋለሁ፣ ገና ለጋላጋ ወጣት ነህ ። በዚህ እሥር ቤት እንድትሞት አልፈልግም። እንድረዳህ ከፈለግህ የምንግርህን እሺ በለኝ። ክርስቲያኖች በሚስጢር ስለሚያደርጉት ስብሰባ ብትነግረኝ ይህን መድሃኒት እሰጠሃለሁ። ምናል ባት አለቆቹ ቢጠይቁኝ እንኳ ምክንያት ይሆናል'' በማለት ነገረው ። ወጣቱ ክርስቲያን ግን "ዘወትር ፊቴን በመስታወት ባየሁ ቁጥር ከሃዲነቴ ትዝ እያለኝ በፀፀት ከምቃጠል ብሞት ይሻለኛል። ያቀረቡልኝ ድርድር ከመቀበል ይልቅ ሞትን እመርጣለሁ" በማለት ነበር የመለሰለት። በዚህ እንዳልተስማማ የተረዳው ባለሥልጣን እንዲህ የሚል ሌላ ምርጫ አቀረበለት " እሺ ሌላ ምርጫ ላቅርብልህ ፤ አንዳንድ እሥረኞች ሰላዮቻችን ናቸው። ኮሚኒስቶች ስለሆኑም ስላንተ ብዙ መጥፎ ነገር ነግረውኛል። ግን ወላዋዮች ስለሆኑ በእነርሱ ብዙም እምነት የለንም። ምን ያህል እውነተኛ እንደሆኑ ለማወቅ እንፈልጋለን። ስለምታደርገውና ስለምትናገረው ሁሉ ነግረውኛል። በክርስተያኖች ላይ መጠቆም እንደማ ትፈልግ አውቃለሁ፤ በተቃዋሚዎችህ ላይ ብትጠቁም ግን ከእሥር ቤት ትወጣለህ" ወጣቱ ክርስቲያን ግን እንደበፊቱ ሁሉ— " የክርስቶስ ተከታይ ነኝ። ክርስቶስ ጠላታችንን እንኳ እንድንወድ ነው ያስተማረን። በእኛ ላይ ክፉ ወሬ የሚያስወሩ እንደሚጐዱን አውቃለሁ። ይሁን እንጂ፣ ክፉ ላደረገብኝ ክፉ ማድረግ አልፈልግም። ስለ እነርሱም እንኳ ቢሆን ምንም ክፉ ነገር ልነግርህ አልፈልግም።" በማለት ቁርጥ ያለ መልስ ሰጠው። ወጣቱ ክርስቲያን ከፖለቲካው ሃላፊ ቢሮ ከተመለሰ በኋላ ባለሁበት ክፍል ነበር ሕይወቱ ያለፈችው። እግዚአብሔርን እያከበረ ሕይወቱ አለፈች። ፍቅር፣ በሕይወት ለመኖር ያለንን ተፈጥሮአዊ ጉጉት እንኳ ያሸንፋል።

አንድ ሰው ሙዚቃ የሚወድ ከሆነ ሙዚቃ ለመስማት ሲል የመጨረሻውን ብር ቢከፍልም እንኳ ቅሬታ አይሰማውም። ምክንያቱም የሚወደውን በማግኘቱ ።

ብዙ አስደናቂ ነገሮችን በማየቴ በእሥር ቤት ያሳለፍኩዋቸው አያስቆጩኝም። በበኩሌ ተራና እዚህ ግባ የምባል ፡ ሰው ባልሆንም የጥንት ሰማዕታትን የሚመስሉ ታላላቅ የእምነት አርበኞችን በእሥር

ቤት አግኝቻለሁ። በእነዚህ ቅዱሳን ላይ ያየሁትን መንፈሳዊ ውበት በቃላት ልገልፀው አልችልም።

የምናገረው ስለ አንዳንድ ልዩ ሰዎች አይደለም። ለእምነታቸው በሚሰቃዩ ክርስቲያኖች መካከል መለኮታዊ ልምምድ ተራና ዕለት በዕለት የሚታይ ጉዳይ ነው።

"የመጀመሪያው ፍቅር" የሚታየው በእነዚህ ክርስቲያኖች መካከል ነው ።

ከመታሠሬ በፊት ክርስቶስን በጣም እወደው ነበር። አሁን ደግሞ ክርስቶስን ብቻ ሳይሆን ፡ የክርስቶስ አካል የሆነችውን ቤተክርስቲያንን በበለጠ ሁኔታ እወዳለሁ። ውበቷንና መስዋዕትነቷን አይቼአለሁ።..›

ታፍኜ ከተወሰድሁ ወዲህ ሚስቴ ምን እንደሆነች አላወቅሁም። መታሠርዋን የሰማሁት ከብዙ ዓመታት በኋላ ነበር። ክርስቲያን ሴቶች ከወንዶቹ በበለጠ ሁኔታ ነው በእሥር ቤት የሚሰቃዩት። ልጃገረዶች የእሥር ቤቱ ዘበኞች መጫወቻ ነው የሚሆኑት። መዘባበቻና መቀለጃ ያደርጓቸዋል። ግድብ ለመሥራት ስለታሰበ ሴቶች ከወንዶቹ እኩል እንዲሠሩ ይጠበቅባቸዋል። ሴተኛ አዳሪ እስረኞች በክርስቲያን እህቶች ላይ ይሰልላሉ። ሕይወቷን ለማቆየት ስትል ሚስቴ እንደ ከብት ሣር በልታለች። የተራቡ እሥረኞች አይጥና እባብ ሣይቀር በልተዋል ።እሑድ እሑድ ዘበኞቹ ዳኑቤ በሚባል ወንዝ ውስጥ ይወረውሩዋቸውና እንደ ዓሣ በመንጠቆ ያወጡዋቸዋል። ከዚያም ደግሞ እንደገና ወደ ወንዙ ይወረውሩዋቸዋል። ያላግጡባቸዋል፡ ይህ ነው እንግዲህ የእነርሱ ዕለተ—ሰንበት መዝናኛ! ሚስቴን ራሷ በዚህ መልክ ተጫውተውባታል።

እናቱና አባቱ ከታሠሩ ወዲህ ልጃችን ያለ አንዳች ታዛቢ ተንከራታች ሆነ። ሚኻይ ገና ከልጅነቱ ጀምሮ ሃይማኖተኛ ነው። መንፈሳዊ ነገሮች ስሜቱን ይስቡታል። ዘጠኝ ዓመት ሲሞላው ነበር ወላጆቹ የታሠሩበት። ስለ እምነቱ መስዋዕትነት መክፈል የጀመረውም ያን ጊዜ ነበር። ከዕድሜው በላይ መከራ ተቀበለ። ስለ ዕለት ምግቡ እንኳ ይጨነቅ ነበር። በዚህ ጊዜ ነው ታድያ የሃይማኖት ጥቅም ምንድ ነው— ? በማለት ራሱን መጠየቅ የጀመረው።

ለእሥረኛ ክርስቲያኖች ቤተሰብ እንክብካቤ ማድረግ ራሱን የቻለ

ወንጀል ነበር። ሚኻይን ሲረዱት በመገኘታቸው ሁለት ሴቶች ክፉኛ ተደብድበዋል። ከዚያም የተነጣ ሽባ ሆነዋል። አንዲት ሴት በሕይወቷ ቀርጣ የእስረኞችን ልጆች በመርዳቷ ስምንት ዓመት ተፈርዶባታል። በድብደባ ጥርሶቿ ሁሉ ረገፉ። አጥንቶቿም ተሰበሩ። ከእንግዲህ ወዲህ ሠርታ መኖር አትችልም። ዕድሜ ልኳን ሽባ መሆንዋ ነው።

"ሚኻይ በክርስቶስ እመን!"

አሥራ አንድ ዓመት ሲሆነው ሚኻይ ራሱን ለመርዳት አነስተኛ ሥራ አገኘ። ከደረሰበት መከራ የተነሣ እምነቱ ተናውጦአል። እናቱ ሁለት ዓመት ከታሠረች በኋላ ግን እንዲያያት ተፈቀደለት። እናቱን በብረት በታጠረው የእሥር ቤቱ ክፍል ውስጥ አያት። በጣም ከስታለች። ቆሽሻለች፤ ቡቱቶ የእሥረኞችን ዩኒፎርም ለብሳለች። እናቱ መሆኗን እንኳ በጥቂቱ ነው ያወቀው። እርሷ ግን ገና እንዳየችው "ሚኻይ በክርስቶስ እመን!" በማለት ጮኸች። ገና አይቶ ሳይጠግባት ጨካኞቹ ዘበኞች እየጎተቱ ወደ ውስጥ አስገቡዋት ።በዚያን ጊዜ ነበር የተናወጠው እምነቱ የተረጋጋለት። በእንደዚያ ዓይነት መከራ ውስጥ ሆነው ክርስቶ ስን መውደድ ከቻሉ እርሱ በእርግጥም እውነተኛ አዳኝ ነው።

ሚኻይ ትምህርቱን ቢጀምርም፣ ኑሮውን ለማሸነፍ መድከም ነበረበት። በትምህርቱ ጉበዝ ስለነበር በሽልማት መልክ ወጣት ኮሚኒስ ቶች የሚያደርጉት ቀይ ከረባት ተሰጠው። እርሱ ግን"እናትና አባቴን ያሰሩ ኮሚኒስቶች ከረባት አላደርግም" በማለቱ ከትምህርት ቤት ተባረረ። አንድ ዓመት ካሳለፈ በኋላ የክርስቲያን እሥረኞች ልጅ መሆኑ እንዳይታወቅ ልዩ ጥንቃቄ በማድረግ እንደገና ትምህርቱን ጀመረ።

በኋላም መጽሐፍ ቅዱስን የሚቃወም ቴሲስ እንዲጽፍ ተነገረው፡ እርሱ ግን "በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተሰነዘረው ተቃውሞ ደካማ ነው። የተጠቀሱት ጥቅሶችም እውነተኛ አይደሉም። ይህ የሚያሣየው ፕሮፌሰ ራችን መጽሐፍ ቅዱስን እንደሚገባ እንዳላነበቡ ነው። መጽሐፍ ቅዱስና ሳይንስ ይስማማሉ..." የሚል ነበር የፃፈው ። በዚህም ምክንያት ከትምህርት ቤት እንዲወጣ ተደረገና ሁለት ዓመት ያለ ትምህርት አሳለፈ።

እንደገና የሥነ—መለኮት ሰሚናር እንዲገባ ተፈቀደለት። ያስተማሩ

ትም "ማርክሣዊ ሥነ መለኮት" (ማርክሲስት ቲዎሎጂ) ነበር። ማንኛ ውም ነገር የሚተረጐመው ወይም የሚተነተነው በማርክሣዊ አተረጓ ጐም ባሕል ነበር። ሚኻይ ይህንን ተቃወመ። ሌሎች ተማሪዎችም አብረውት ተቃወሙ። ስለዚህም ትምህርቱን ሳይጨርስ ከሴሚናር ተባረረ።

አንድ ጊዜ ደግሞ ፕሮፌሰሩ እግዚአብሔር ላለመኖሩ ለተማሪዎቹ ገለፃ እያደረገ እያለ ሚኻይ ተነስቶ ተቃወመው። ሌሎች ተማሪዎችም ደገፉት። አንድ ሰው ደፍሮ ከተናገረ ሁሉም እንደሚደግፉት የታወቀ ነው። ከትምህርቱ እንዳይባረር ሲል የክርስቲያን እሥረኞች ልጅ መሆኑን መደበቅ ነበረበት። ብዙ ጊዜ ግን ስለሚታወቅበት ወደዳይሬክተሩ ቢሮ ተጠርቶ ከቀረበ በኋላ ያው እንደልማዱ ከትምህርት ቤት ይባረራል።

የክርስቲያን እሥረኞች ልጆች ጠኔ እስኪይዛቸው ድረስ ይራባሉ። አንድ ጊዜ ደግሞ አንድ ክርስቲያን ወንድም በኅቡዕ ወንጌልን ከምታሠራ ጨው ቤተ ክርስቲያን ጋር ተባባሪ በመሆኑ እሥራት ተፈረደበት። ስድስት ልጆቹንና ሚስቱን ትቶ ነበር ወኅኒ የወረደው። አሥራ ሰባትና አሥራ ዘጠኝ ዓመት የሞላቸው የደረሱ ልጃገረድ ልጆቹ ሥራ ማግኘት አልቻሉም። እንደሚታወቀው ደግሞ በኮሚኒስት አገሮች ሥራ የሚሰ ጠው መንግሥት ብቻ በመሆኑ ለ "ወንጀለኛ" ክርስቲያን ልጆች ሥራ አይሰጥም። ይህን ታሪክ እውነትነቱን እንድትቀበሉት እንጂ በሞራላዊ ሚዛን እንድትገመግሙት አልፈልግም፡ እነዚህ ሁለት ልጃገረዶች ሕመምተኛ እናታቸውንና ትንንሽ ወንድሞቻቸውን የሚረዱበት ዘዴ በማጣታቸው ሴተኛ አዳሪዎች ሆኑ። ይህንን ያየ የአሥራ አራት ዓመት ወንድማቸውም አእምሮውን ስቶ ሆስፒታል እንዲገባ ተደረገ። ከጥቂት ዓመታት በኋላ አባታቸው ከእሥራት ቢፈታም ጥዋት ማታ "አምላኬ ሆይ፡ ይህን ከምታሳየኝ እዚያው እስር ቤት ብመለስ ይሻለኛል" ነበር ፀሎቱ። ወንጌልን ለሕዝናት ሲያስተምር በመገኘቱ እንደተመኘው እንደ ገና ታሰረ። በአሁኑ ጊዜ ሴቶቹ ልጆች ለሚስጢር ፖሊሶች የሚፈለገውን በመሟላታቸው ደኅና ሥራ አግኝተዋል። ሥራውም በክርስቲያኖች ላይ መጠቆም ነው። የክርስቲያን እሥረኛ ልጆች በመሆናቸው ክርስቲያኑ ሕብረተሰብ በአክብሮት ይመለከታቸዋል። ማንኛውንም ሚስጢር አይደ ብቋቸውም። እነርሱ ደግሞ የሰሙትንና የሚያዩትን ሁሉ ለሚስጢር ፖሊሶች ያቀብላሉ።

# ምዕራፍ ሶስት

## የቤዛ ክፍያና ወደ ምዕራብ ስለመሄዴ

ከታሠርኩ አሥራ አራት ዓመት ሆነኝ። በእሥር ቤት በነበርኩበት ወቀት መጽሐፍ ቅዱስም ሆነ ሌላ መጽሐፍ ማግኘት አልቻልኩም። መፃፍ እንኳ ድንግርግር ይለኛል ። ብዙ ጊዜ ተርቤአለሁ። ብዙ አሠቃቂ መከራም ደርሶብኛል። በቃሌ ያጠናሁዋቸው የቅዱሣት መፃሕፍት ጥቅሶችም እየተዘነጉኝ ነው። አሥራ አራቱን ዓመት ከሞላሁ በኋላ በድንገት— ያዕቆብም ስለ ራሔል አሥራ አራት ዓመት ተገዛ እርስዋንም ይወድዳት ስለነበር በእርሱ ዘንድ እንደ ጥቂት ቀን ሆነለት" የሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ወደ አእምሮዬ መጣ።

ይህ ከሆነ ከጥቂት ቀን በኋላ የአሜሪካ ባለሥልጣናትና ሕዝብ፣ እንዲሁም የመላው ዓለም ክርስቲያን ሕብረተሰብ ባቀረበው አቤቱታ ማቢያ ከእሥር ቤት ወጣሁ።

እንደገና ለብዙ ዓመት በታማኝነት ስትጠብቀኝ ከኖረችው ሚስቴ ጋር ተገናኘሁ። በኮሚኒስት አገር አንድ ሰው ሲታሠር ንብረቱ ይወረሳል። ስለዚህም እኔና ባለቤቴ ኑሮአችንን የጀመርነው በጣም ድህነት በተሜላ ነው ሁኔታ ነበር።

አብረውኝ የተፈቱት ቄሶችና ፓስተሮች ትናንሽ ቤተ ክርስቲያኖች ውስጥ መሥራት ጀመሩ። ለእኔ የተሰጠኝ ደግሞ አርሶቫ በሚባል መንደር ያለው ቤተክርስቲያን ነበር። ሥራውን ከመጀመሬ በፊት ግን የሃይማኖቶች ጉዳይ ባለሥልጣን አስጠርቶ በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ሠላሳ አምስት ምዕመናን መኖራቸውንና ሠላሣ ስድስት ሆነው ቢገኙ ግን ከባድ ችግር እንደሚገጥመኝ አስጠነቀቀኝ። በተጨማሪም ማንኛውም ወጣት ወደ ቤተክርስቲያኑ እንዳይመጣና የእያንዳንዱን ምዕመናን እንቅስቃሴና አዝማሚያ በመጠቀም ከሚስጢር ፖሊሶች ጋር አብሬ እንድሠራ ነገረኝ። ይህን በመሰለ ሁኔታ ነው ኮሚኒስቶች አብያተ ክርስቲያናትን ሕብረተሰ

ቡን ለመቆጣጠር "መጣሪያ" የሚያደርጓቸው።

የስብከት ሥራዬን ብጀምር ብዙ ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያናችን እንደሚጎርፉ አውቃለሁ። ይሁን እንጂ፣ በመንግሥት እውቅና ካላት ቤተክርስቲያን ጋር መሥራቱን አልፈለግሁም። ምንም እንኳ ችግር እንደሚያስከትልብኝ ባውቅም ከችግሩ ጋር አብሮ ውበትዋ ስለሚታየኝ በኅቡዕ ከምታገለግለው ቤተ ክርስቲያን ጋር መሥራቱን ነበር የመረጥሁት።

እኔ በታሠርኩበት ወቅት አንዳንድ አስደናቂ ሁኔታዎች ተከናውነዋል። ለእኛ መስሎ እንደታየን ይህቺ በኅቡዕ የምትሠራው ቤተክርስቲያን በዓለም ሕብረተሰብ ዘንድ ተዘንግታ አልቀረችም። የአሜሪካና የመላው ዓለም ክርስቲያኖች ሲፀልዩልን ነበር። አሁን ደግሞ የማይናቅ እርዳታ እያደረጉልን ነው።

አንድ ቀትር ላይ ጓደኛዬ መኝታ ቤት ውስጥ ጋደም ብዬ እያለሁ ቀሰቀሰኝና "ከውጭ አገር የመጡ ክርስቲያን ወንድሞች ሊያነጋግሩህ ይፈልጋሉ" አለኝ። በምዕራቡ ዓለም የነበሩ ክርስቲያኖች አልዘነጉንም አልተውንም።

በውጪ አገር ያሉ ክርስቲያኖች የክርስቲያን እሥረኞችን ቤተሰብ የሚረዱና ፡ ወንጌል በታገደባቸው አገሮች ክርስቲያናዊ ጽሁፎችን የሚያስገባ ማኅበር አቋቁመዋል።

ወደ ግሎን ስሄድ ይህንኑ ተግባር ለማከናወን የመጡ ስድስት ሰዎች አገኘሁ። ብዙ ከተነጋገርን በኋላ አንድ አሥራ አራት ዓመታት በእሥራት የማቀቀ ሰው መኖሩን እንደሰሙና በዚህ አድራሻ ሊያገኙት እንደሚችሉ እንደተነገራቸው አጫወቱኝ። ሰውየው እኔ መሆኔን ስነግራቸው ሊያምኑኝ አልቻሉም። " ያ ሰው አንተ ልትሆን አትችልም፡ ምክንያቱም እንደምናይህ ደስተኛ ነህ፡ ያ ሁሉ መከራ የደረሰብህ ሰው ልትሆን አትችልም" አሉኝ። እኔ ግን የተነገራቸው ሰው እኔ እንደሆንሁና የደስታዬም ምክንያት በውጪ ባሉ ክርስቲያኖች አለመረሳታችንና ለዚህ ማስረጃው የእነርሱ መምጣት እንደሆነ አስረዳኋቸው። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በኅቡዕ ለምናካሂደው ወንጌልን የማስፋፋት አገልግሎት በየጊዜው እርዳታ ያደርጉልን ጀመር። ብዙ መጽሐፍ ቅዱሶች፣ ክርስቲያናዊ

ሥነ ጽሁፎችና ለክርስቲያን እሥረኛ ቤተሰቦች የምናከፋፍለው እርዳታ ማግኘት ቻልን። ሥራችንንም በተሻለ ሁኔታ ማከናወን ቻልን።

በጣም ያስደሰተን እርዳታ ማግኘታችን ብቻ ሳይሆን የሚወዱንና የሚያስቡልን ወገኖች መኖራቸው ጭምር ነበር። መጽናናትን ይዘውልን ነበር የመጡት።

ብሬንዎሽድ በተደረግንባቸው ዓመታት "ማንም አይወዳችሁም፤ ማንም አይወዳችሁም ፤ ማንም አይወዳችሁም" የሚሉ ቃላትን ነበር በተደጋጋሚ እንድንሰማ ይደረግ የነበረው። አሁን ግን ለሕይወታቸው ሳይሳሱ እኛን ለመርዳት ብለው ክርስቲያን ወገኖች ከተለያየ ሀገር መጥተዋል። እነዚህ ሰዎች በኀቡዕ ወንጌልን በማስፋፋት ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል።

እነዚህ ሰዎች ይዘውልን የመጡት መጽሐፍ ቅዱሶች በእንዴት አይነት አክብሮትና ፍቅር እንደተቀበልናቸው የምናውቅ እኛ ብቻ ነን። የእምነት ነፃነት ባለባቸውና መንፈሳዊ መፃሕፍትን እንደፈለጉ ማግኘት በሚችሉበት ዓለም ያሉ ሰዎች የተስማማን ደስታ እንደማይረዱልን ይገባናል።

በሌላው ዓለም የነበሩ ክርስቲያኖች በፀሎት ባይተባበሩልን ኖሮ እኔም ሆንኩ ቤተሰቤ እንዲሁም ሌሎች ፓስተሮችና የኮሚኒስት አገር ሰማዕታት በሕይወት መገኘታችን ራሱ አጠራጣሪ ይሆን ነበር። ከእነዚህ ሰዎች ያገኘነው የማቴሪያልና የሞራል እርዳታ ከፍተኛ መጽናናትና ድጋፍ ሆኖልናል። በእርግጥም እነዚህ ሰዎች በመከራችን ጊዜ እግዚአብሔር የላካቸው የሚያጽናኑ መላእክት ናቸው ማለት እችላለሁ።

በኀቡዕ የምናደርገው ወንጌልን የማስፋፋት አገልግሎት እየሰፋ በመምጣቱ ምናልባት ለሶስተኛ ጊዜ እንዳልታሠር ስጋት አስከተለ። በዚህ ጊዜ ነበር "ኖርዌጅያን ሚሽን ቱ ዘጂውስ " እና "ሒብሩ ክርስቲያን አሊያንስ" የተባሉ ሁለት ክርስቲያን ድርጅቶች እኔን ከሀገሬ ለማስወጣት 10.000 ዶላር የቤዛ ክፍያ ለመክፈል የተስማሙት።

ለምን ከሩማንያ ወጣሁ—?

ምንም እንኳ አደጋ እያንዣበበና ሁኔታውም አስፈሪ ቢሆንም

ከሩማንያ ለመውጣት አልፈለግሁም ነበር። በነቡዕ ወንጌልን የምታስፋፋው ክርስቲያናዊ አካል መሪዎች ግን ከሩማንያ እንድወጣና ያለንበትን መከራ ለ"ለነፃው ዓለም" እንዳሰማላቸው ገፋፉኝ፡ ያለው አጋጣሚም ይኸው ነበር።

ሩማንያን ለቅቄ ከመውጣቴ በፊት ግን ሁለት ጊዜ ወደ ሚስጢር ፖሊሶች ቢሮ አስጠሩኝና ገንዘብ መቀበላቸውን ነገሩኝ። (በጊዜውም ሩማንያ ኮሚኒዝም ባስከተለባት ከፍተኛ የኢኮኖሚ ቀውስ ውስጥ ስለነበረች የራሷን ዜጎች እንኳ እየሸጠች ነበር) "ወደ ምዕራቡ ዓለም እንድትሄድ ተፈቅዶልሃል፤ ኀይማኖትህን እንደፈለግህ ስበክ፡ ግን እኛን አትንካን፤ ይህን ሳታከብር ብትቀር ግን ታፍነህ ወደዚሁ እንድትመጣ እናደርጋለን፤ እና ተጠንቀቅ ብታስብበት ይሻላል" አሉኝ። በእሥር ቤት በነበርኩበት ጊዜ ከኦስትሪያ ታፍኖ ከተመለሰ ቫዚሌ ሊውል ከሚባል የኦርቶዶክስ ጳጳስ ጋር ተገናኝቻለሁ። ጥፍሮቹን ሁሉ ነቃቅለው እያሰቃዩት ነበር። በቅርቡ ደግሞ ከበርሊን ከኢጣሊያና ፓሪስ ታፍነው ወደ ሩማንያ የተመለሱ ሰዎች ጋር ተዋውቄአለሁ "ካስፈለገም" አሉ እነዚህ ባለሥልጣኖች "ካስፈለገም የሰው ሚስት ስታማግጥ እንደተያዝክ ወይም ደምሞ ሌባና አጭበርባሪ እንደሆንህ በማሠራጨት የሞራል ስብራት እናደርስብሃለን። ምዕራባውያን በተለይም ደግሞ አሜሪካውያን የተወራውንና የተፃፈውን ሁሉ እንደሚያምኑ አሳምረን እናውቃለን። ስለዚህ ተጠንቅቆ፡ ብታስብበት ይሻላል" በማለት አጠንክረው ነገሩኝ።

ይህ ሁሉ ዛቻና ማስጠንቀቂያ ከተሰጠኝ በኋላ ወደ ምዕራቡ ዓለም እንድሄድ ተፈቀደልኝ። አስቀድሞ እንደነገርኳችሁ ብሬንዎሽድ ተደርጌ አለሁ፤ ኮሚኒስቶቹ ባለሥልጣኖችም ይህ ብሬንዎሺንግ አስፈላጊውን ውጤት እንዳስገኘላቸው ነው የሚያስቡት። ብሬንዎሽ የተደረጉና ብዙ ብዙ መከራ የተቀበሉ ሰዎች ፀጥ ሲሉላቸው ተመልክተዋል። እንዲያውም አንዳንዶቹ ኮሚኒዝምን እያመሰገኑ ነው። እኔም እንደ ሌሎቹ አንገቴን እንደምደፋና ፀጥ እንደምል እርግጠኛ ናቸው። እኔና ቤተሰቤ ታህሳስ 1965 ሩማንያን ለቀን እንድንወጣ ተወሰነ። አገሩን ለቅቄ ከመውጣቴ በፊት ግን እንድታሠርና ይህ ሁሉ ስቃይ እንዲደርስብኝ ወዳዘዘው ኮሎኔው መቃብር ሄድሁና አበባ አኖርሁ፤ ይህንንም ማድረጌ መንፈሳዊ ድርቀትና ባዶነት ለተጠናወታቸው ኮሚኒስቶች የክርስቶስን

ፍቅር ለማድረስ ላደረግሁት ውሣኔ ምስክር እንዲሆንልኝ ነበር።

የኮሚኒዝምን ሥርአት እጠላለሁ፤ ሰዎቹን ግን እወዳለሁ። ኃጢአትን እጠላለሁ፤ ኃጢአተኛን ግን እወዳለሁ። ኮሚኒስቶች ክርስቲያኖችን መግደል ይችላሉ፤ ክርስቲያናዊ ፍቅርን ግን ሊገድሉት አይችሉም። ባሰቃዩኝ ሰዎች ላይ ቅንጣት ታህል ቂም ወይም ጥላቻ የለኝም።

# ምዕራፍ አራት

## ኮሚኒዝምን በክርስቶስ ፍቅር ማሸነፍ፣

አንድ የአይሁዳውያን አፈ ታሪክ (ተውፊት) እንደሚያመለክተው፥ እስራኤላውያን ከግብፅ ባርነት በሚወጡበት ጊዜ ቀይ ባሕር ተከፍሎ እየተሻገሩ ነበር። ወደ ባርነት ሊመልሱዋቸው ይከታተሉዋቸው የነበሩት ግብፃውያን ግን በባህሩ ሰጥመው ቀሩ። ይህንንም ያዩ እሥራኤላውያን በሁኔታው ደስ ብሎአቸው ይጨፍሩ ጀመር። መላእክትም ከእነርሱ ጋር አብረው ማሽብሸብ ያዙ። በዚህ ጊዜ ግን እግዚአብሔር—"እሥራኤላውያን ሰዎች በመሆናቸው ደስ ሊላቸው ይችላል፤ ከእናንተ ግን የበለጠ መረዳትን እጠብቃለሁ። ግብፃውያንስ የእኔ ፍጡሮች አይደሉምን? አልወዳቸውምን? በእነርሱ ላይ የደረሰው ጥፋት እኔን እንዳሣዘነኝ እናንተንስ እንዴት እያሣዝናችሁም" በማለት ገሰፃቸው።

"እንዲህም ሆነ ኢያሱ በኢያሪኮ አጠገብ ሳለ ዓይኑን አንስቶ ተመለከተ፤ እነሆም የተመዘዘ ሰይፍ በእጁ የያዘ ሰው በፊቱ ቆሞ ነበር። እያሱም ወደ እርሱ ቀርቦ ከእኛ ወገን ወይስ ከጠላቶቻችን ወገን ነህን? አለው" (መጽሐፈ ኢያሱ 5፡13)

ይህ ከኢያሱ ጋር የተገናኘው ሰው እንደኛ ሰብአዊ ፍጡር ቢሆን ኖሮ የሚሰጠው መልስ— "የእናንተ ወገን ነኝ "ወይም" ከጠላቶቻችሁ ወገን ነኝ" ከማለት ባላለፈም ነበር። ሰዎች ይህን ለመሰለ ጥያቄ የሚሰጡት መልስ ከዚህ አያልፍም። ኢያሱ ያገኘው ይህ ሰው ግን የሌላ ዓለም ፍጡር በመሆኑ "አይደለህም" የሚል መልስ ነበር የሰጠው። ለምንድን ነው በደፈናው "አይደለሁም" ያለው።

ይህ ፍጡር የመጣው ሰዎች በሰውነታቸው ከሚታዩበት ዓለም እንጂ፤ በማንነታቸው ወይም በሚያራምዱት የፖለቲካ ርዕዮት ከሚገመገሙበት ክልል አይደለም። ስለዚህም ኢያሱ "ከእኛ ወይስ ከጠላቶቻችን ወገን ነህ?" በማለት በጠየቀው ጊዜ ከማንኛቸውም ወገን እንዳልሆነ ነገረው።

እንደ ሰው መለኪያ ወይም ሚዛን ቢሆን ኖሮ ኮሚኒዝምን ልንጠላ ይገባን ነበር። የዚህ ጨካኝ ፍልስፍና አራማጆች በመሆናቸውም ኮሚኒስ ቶችን ከምድረ ገጽ ማጥፋት ባስፈለገ ነበር።

ክርስቲያኖች ግን በሰው ሚዛን ወይም መለኪያ ብቻ መመልከት የለባቸውም። የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው። የመለኮታዊው ባሕርይ ተካፋዮች ናቸው፣ በመሆኑም በኮሚኒስቶች እሥር ቤት መማቀቄ እንድጠላቸው አላደረገኝም። የእግዚአብሔር ፍጡሮች ናቸው፤ ታድያ፣ ለምን እጠላቸዋለሁ? በሌላ በኩል ደግሞ ባልንጀራቸው ልሆን አልች ልም፤ ባልጀርነት ማለት በአንድ ነፍስ የተጠቃለሉ ሁለት ሰዎች ማለት ነው። ከኮሚኒስቶች ጋር አንድ ነፍስ የለኝም፤ እነርሱ እግዚአብሔርንም ሆነ ስለ እግዚአብሔር የሚሰነዘረውን ማንኛውንም ሃሣብ ይጠላሉ፣ እኔ ደግሞ እግዚአብሔርን እወዳለሁ፣ የኮሚኒስቶች ደጋፊ ነህ ወይስ ተቃ ዋሚ? የሚል ጥያቄ ቢቀርብልኝ የምሰጠው መልስ ውስብስብ ሊሆን ይችላል። እንደሚታወቀው ኮሚኒዝም ለዓለም ሕዝብ መበጣበጥ ዋነኛ ምክንያት ነው። ከዚህ የተነሣ እጠላዋለሁ፣ ሙሉ በሙሉ እስኪደመሰስ ድረስ መዋጋቴን አላቋርጥም። በመንፈስ ግን ከክርስቶስ ጋር በሰማያዊ ስፍራ ተቀምጬአለሁ። በሰማይ የሚኖር እግዚአብሔር በትክክለኛ ማንታቸውና ምንነታቸው ያውቃቸዋል፤ በሰማይ ያሉ መላእክት የማንኛ ውም ፍልስፍና ርዕዮት ደጋፊ ወይም ነቃፊ አይደሉም። ሰዎች ደኅንነትን አግኝተው ክርስቶስን ወደ መምሰል ደረጃ ማደግ አለባቸው። ስለዚህም የእኔ ዋነኛው ዓላማ ወንጌልን ማስፋፋትና እኔ የማምነው ጌታ እነርሱንም እንደሚወድድ ለኮሚኒስቶች ማብሰር ነው። እርሱ ራሱም ሰዎችን ሁሉ እንደሚወድ ተናግሮአል። ከዘጠና ዘጠኝ ፃድቃን ይልቅ የጠፋችው አንዷት ሃጢአተኛ ነፍስ ወደ እርሱ እንድትመለስ ይፈልጋል። ሐዋርያ ቱና በዘመናት የተነሱት የክርስትና መምሕራን ይህን ፍቅር ሲያውጁ ኖረዋል። ቅዱስ ማካሪ የተባለ የቤተ ክርስቲያን አባት—"አንድ ሰው ሰዎችን ሁሉ ቢወድ፣ አንድ ሰው ግን ቢጠላ ያ ሰው ክርስቲያን አይደለም፣ ምክንያቱም ፍቅሩ ሁሉን አቀፍ አይደለምና" ብሎአል። ቅዱስ አውጉስ ጢኖስ ደግሞ "ሰዎች በሙሉ ፃድቅ ቢሆኑ በመካከላቸው ግን አንድ ሃጢአተኛ ብቻ ቢኖር ክርስቶስ ለዚያ ሰው ወደዚህ ምድር መምጣቱንና መሰቀሉን አይተውም ነበር፤ እርሱ እያንዳንዱን ግለሰብ ይወዳል"

ብሎአል። የክርስትና ትምህርት ግልጽ ነው፤ ኮሚኒስቶች ሰዎች እንደመሆናቸው መጠን ክርስቶስ ይወዳቸዋል፤ የክርስቶስ ልብ ያለው ማንኛውም ሰው ሌላውን አይጠላም። ኃጢአትን ብንጠላም እንኳ ኃጢአተኛውን እንወዳለን።

ክርስቶስ ኮሚኒስቶችን እንዴት እንደሚወዳቸው የምናውቀው እኛ በምንወዳቸው መጠን ነው።

በእሥር ቤት በነበርኩበት ጊዜ እግራቸውን 50 ፓውንድ በሚመዝን እግር ብረት የታሠሩ፣ በጋለ ብረት የተተኮሱ፣ ጨው እንዲውጡ ከተገደዱ በኋላ—ውሃ ተከልክለው በጥም እንዲቃጠሉ የተደረጉ፣ ሰውነታቸው እስኪገዘል ድረስ በረሃብ የተቀጡ፣ የሚገረፉና ሊቋቋሙት በማይችሉት ሁኔታ ውርጭ ላይ የተጣሉ ክርስቲያኖች ለኮሚኒስቶች ሲፀልዩ ተመልክቼአለሁ። ይህ የክርስቶስ ፍቅር ነው። የክርስቶስ ፍቅር በልባችን ፈስሶአል፤ ይህን ፍቅር ሰብአዊ አእምሮ ሊረዳው አይችልም።

ብዙ ጊዜ እኛን ያሰቃዩ ኮሚኒስቶች እነርሱም በተራቸው እሥረኛ ሆነው ወደነበርንበት እሥር ቤት ሲመጡ ተመልክተናል። ኮሚኒዝም ተቃዋሚዎቹን በሚበቀልበት ሁኔታ ነው ራሳቸውን ኮሚኒስቶቹን ወይም የኮሚኒስት መሪዎችን የሚቀጣቸው። የሚሰቃዩትና ሲያሰቃዩ የነበሩት ራሳቸው ሲታሠሩ በእነርሱ ምክንያት የታሠሩትና ብዙ ግፍ የደረሰባቸው እሥረኞች ተራቸውን ይበቀሉአቸዋል። በዚህ ጊዜ ለኮሚኒስቶች የሚከራከሩላቸው ክርስቲያኖች ናቸው። የኮሚኒዝም ደጋፊዎች ናችሁ ተብለው ራሳቸው ክርስቲያኖቹ ይንገላታሉ። ክርስቲያኖች የሚሰጣቸውን ቁራጭ ዳቦ እንዲሁም ለሕመም ማስታገሻ የሚሰጣቸውን መድሃኒት ሲያሰቃዩዋቸው ለነበሩ ኮሚኒስት እሥረኞች ሲያካፍሉ ተመልክቻለሁ።

ክርስቲያንና የቀድሞው የሩማንያ ሚኒስቴር የነበረው ሉሉ ማኒዮ የተባለው ሰው በእሥር ቤት ሲሞት የተናገራቸው የመጨረሻዎቹ ቃላት— "ኮሚኒዝም ሲደመሰስ ሕዝቡ ሁሉ ኮሚኒስቶችን ለመበቀል መነሣቱ አይቀርም፤ ታድያ በዚያን ጊዜ ቅን ፍርድ እንዲደረግላቸው መታገል በእነርሱ ሲሰቃዩ የነበሩት ክርስቲያኖች ተግባር መሆን አለበት" የሚሉ ነበሩ።

ጌታን በተቀበልኩበት ዘመን በሕይወት ብዙ የምቆይ አይመስለኝም ነበር። ምክንያቱም የእያንዳንዱ ሰው ዘላለማዊ ፍጻሜ በጣም

ያሳስበኛል። ይህ ሰው የዘላለምን ሕይወት አግኝቶአል? የሚለው ጥያቄ ልክ እንደተሳለ ቢላ ልቤን ይወጋኛል። ከቤተክርስቲያኔ አባሎች አንዱ በኃጢአት ቢወድቅ ለሰዓታት ያህል አለቅስለታለሁ። ሰዎች ደኅንነትን እንዲያገኙ አሁንም ቢሆን የጋለ ፍላጎት አለኝ፤ ይህ ፍላጎቴም ኮሚኒስቶችንም ይጨምራል።

በጠባቧ የእሥር ክፍል ለየብቻችን ታስረን በነበረበት ወቅት በፊት እንደምንፀልየው መፀለይ አንችልም። ሰውነታችን እስኪዝለፈለፍ ድረስ እንራባለን፤ ደደብ እስክንሆን ድረስ አእምሮአችን ደንዝዞአል፤ ሥጋችን አልቆ በአጥንታችን ቀርተናል፤ የጌታን ፀሎት እንኳ ለመውጣት ረጅም ይሆንብናል፤ ፀሎቱን እንደበታችን ቢያነበንበውም የተበታተነ አእምሮአችንን መሰብሰብ በጣም አስቸጋሪ ነበር። ደጋግመን የምንናገረው ወይም የምናደርገው ፀሎት — "ኢየሱስ ሆይ እንወድሃለን" ማለት ብቻ ነበር።

አንድ ቀን ደጋግሜ "ኢየሱስ ሆይ እወድሃለሁ" በማለት ላይ እያለሁ "በእርግጥ ትወደኛለህ?" እኔ ደግሞ እንዴት እንደምወድህ አሳይሃለሁ" በማለት ኢየሱስ ክርስቶስ በመንፈሱ አማካይነት በግልጽ ተናገረኝ። በድንገት የእሳት ወንዝ የሚመስል መለኮታዊ ፍቅር ልቤንና ሁለንተናዬን አጥለቀለቀው፤ በቃላት መግለጽ ግን ያዳግተኛል፤ በኤማሁስ መንገድ ይጓዙ የነበሩት ደቀ መዛሙርት ኢየሱስ በተናገራቸው ጊዜ "ልባችን ይቃጠልብን ነበር" ሲሉ ምን ማለታቸው እንደሆነ የገባኝ ያን ጊዜ ነው። ይህንን ሁኔታ እኔም ተለማምጄዋለሁ፤ ለእኛ ሲል ሕይወቱን የሰጠ ጌታ ፍቅሩ ምን ያህል እንደሆነ በሕይወቴ አይቼዋለሁ። በደላቸው ምን ያህል የከፋ ቢሆንም፡ ይህ ፍቅር ኮሚኒስቶችንም ያቅፋል። ኮሚኒስቶች ብዙ በድለዋል። አሁንም እየበደሉ ነው ሆኖም።— "ብዙ ፈሳሾች ነበልባላዊውን የፍቅር እሣት ሊያጠፉት አይችሉም። ፍቅር ከሞት ኃይል ይልቅ የበረታ ነው። ቅንዓት ግን የመቃብርን ያህል ጨካኝ ነው" መቃብር— ሀብታሙንና ድሃውን፤ ወጣቱንና ሽማግሌውን፤ ፃድቁንና ወንጀለኛውን፤ ዘር፤ ጎሣ፤ የትምህርት ደረጃ፤ የተለያየ ፖለቲካዊ አመለካከት ያላቸውን ሳይመርጥ ሁሉን እንደሚውጥ ሁሉ ፍቅርም ሁሉንም ያቅፋል። ኮሚኒስቶችንም ወደ እርሱ ካላመጣ በቀር ይህ ነበልባላዊ ፍቅር አያርፍም።

አንድ ጊዜ የነበርኩበት እሥርክፍል በድንገት ተበረገደና አንድን

ወንጌላዊ ወለሉ ላይ ዘረሩት። ይህ ሰው ግማሽ በድን ነበር። ክፉኛ በመደብደቡ ከፊቱና ከሰውነቱ ደም እየጎረፈ ነው። ቁስሎቹን አጠብንለት። ይህንን የተመለከቱ አንዳንድ እሥረኞች ኮሚኒስቶችን ይሳደቡና ይራገሙ ጀመር፡ እርሱ ግን "እባካችሁን አትራገሙ ይልቅስ እንፀልይላቸው" በማለት ጣዕር በሚተናነቀው ቃሉ ተናገረ።

አንዳንድ ጊዜ በእሥርቤት ያሳለፍኳቸውን አሥራ አራት ዓመታት ሳስባቸው ደስ ያሰኙኛል። ምንም እንኳ በጣም በሚያስከፋ ሁኔታ ቢያልፉም ክርስቲያኖች ደስተኛ ሆነው መገኘታቸው ሌሎች እሥረኞችንና የእሥር ቤቱን ዘበኞች እንኳ ሳይቀር ያስደንቃቸዋል። ብዙ ጊዜ ቢደበደቡም ሲዘምሩ ነው የሚታዩት። እንዴት ነው በዚህ ሁኔታ ወስጥ ደስተኛ ሊሆኑ የቻሉት?

በእሥር ቤት በነበርኩ ጊዜ ኢየሱስ—"እናንተ የምታዩትን የሚያዩ ዓይኖች የተባረኩ ናቸው" በማለት ለደቀመዛሙርቱ መናገሩ ምን ማለት ነው? እያልኩ አሰላስል ነበር፡በጊዜው በፖለስቲና ግፍና ጭቆና ነበር የተንሰራፋው። በየቦታው የሚታዩት ከሰውነት ተራ የወጡ ሰዎች ናቸው። ረሃብ፡ ሕመም፡ ደዌና ትካዜ የዕለት ተዕለት ዕይታዎች ናቸው። ዓይንን የሚማርክ ነገር አልነበረም የሚታየው።

ታድያ ይህ አስከፊ ሥርዓት በተንሰራፋበት አገር ወስጥ እያሉ "እናንተ የምታዩትን የሚያዩ ዓይኖች የተባረኩ" ናቸው ሲል ምን ማለቱ ነው? ደቀ መዛሙርቱ ጭቆናውንና ግፉን ብቻ አልነበረም ይመለከቱ የነበረው። የሁሉ አዳኝ፡ የውበት ሁሉ መደምደሚያ፡ የሰው ልጆች ሁሉ ናፍቆትና ግብ የሆነውንም ጌታ ተመልክተዋል። በቅጠላ ቅጠል ላይ ሲርመሰመሱ የሚታዩት አስቀያሚ ትላትሎች በዚያ ሁኔታ ካለፉ በኋላ ከአበቦች ወደ አበቦች የሚበሩ ባለ ብዙ ኅብረ ቀለማት ቢራቢሮ ይሆናሉ። ይህ ነው የደስታችን ምንጭ።

በዙሪያችን ከኢዮብ ያላነሰ መከራ የደረሰባቸው ሰዎች ይታያሉ። ይሁን እንጂ፡ የኢዮብ ታሪክ እንዴት እንዳከተመ አውቃለሁ። በፊት ከነበረው ይልቅ እግዚአብሔር ሁለት እጥፍ መልሶለታል። በዙሪያዬ እንደ አልዓዛር የሚራቡና በቁስል የተወረሱ ሰዎችን አያለሁ። ይሁን እንጂ፡ በአብርሃም እቅፍ እንዲያርፍ መላእክት አልዓዛርን ወስደውታል። አሁን ካሉበት ይልቅ ወደፊት የሚሆኑትን ነው የማየው፡ አጠገቤ ያለውን

ደካማውን፣ ረሀብተኛውንና ቡቱቷሙን ስማዕት የድል አክሊል የጫኑ ቅዱስ ሆኖ ነው የማየው።

ሁኔታዎችን አሁን ባሉበት ብቻ ሳይሆን ወደፊት የሚሆኑትን ስመለከት ፣ ዛሬ ክርስቲያኖችን የሚያሣድዱ ሰዎች አንድ ቀን እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ ታላቅ የወንጌል አርበኞች ሆነው አያቸዋለሁ ፡ እኛን ሲያሰቃዩ የነበሩ ባለሥልጣናት በእኛ ስብከት አምነው እነርሱም እንደ እኛው የመከራችን ተካፋዮች ሆነዋል። ሐዋርያትን ሲያሰቃይ የነበረው የፊሊጵስዮስ ወህኒ ጠባቂ ራሱ ክርስቲያን ሆኖአል። ዛሬም በሚያሰቃዩን ሰዎች ውስጥ ሕይወታቸው የተለወጠ ሰዎችን እናያለን። እንደ ፊሊጵስ ዩሱ የወህኒ ዘበኛ ሁሉ፣ እነዚህም አንድ ቀን “እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል?” በማለት የሚጠይቁበትን ዕለት እንጠብቃለን። ዛሬ በክርስቲያኖች የሚያፌዙና የሚዘባበቱ ሁሉ በኃጢአታቸው ደረታቸውን የሚደቁበትን ቀን እንጠብቃለን።

እንደማንኛውም ሰው ሁሉ ኮሚኒስቶችም በጌታ አምነው እንዲሚድኑ ተስፋ ማድረግ የጀመርነው ከታሠርን በኋላ ነበር። ለእነርሱ ወንጌልን የመስበክ ሃላፊነት እንዳለብን የተገነዘብነው በእሥር ቤት ውስጥ ነው። እነርሱን ማፍቀር የጀመርነው በእነርሱ ከተደበደብን በኋላ ነበር።

አብዛኞቹ ቤተሰቦቼ ተገድለዋል፤ ይሁን እንጂ፣ ነፍሰ ገዳዮቹ በጌታ ያመኑት በእኔ ቤት ውስጥ ነበር። ለኮሚኒስት አገሮች ወንጌልን በስፋት የማዳረስም ሃሣብ የተጠነሰሰው በራሳቸው በኮሚኒስቶቹ እሥር ቤት ውስጥ ነበር።

የእኛ አመለካከት ከጉንዳን አመለካከት በጣም የተለየ እንደሆነ ሁሉ እግዚአብሔር ነገሮችን የሚመለከታቸውም ከእኛ በጣም በተለየ ሁኔታ ነው። በሰው ደረጃ ቢሆን ኖሮ ኮሚኒስቶች ያደረሱብን ስቃይ ከይቅርታ በላይ በሆነ ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ ሰማዕታት የሚጠብቃቸውን ክብር በዚህ ምድር ከተቀበሉት መከራ ጋር ሲያነፃጽረው “ቀላል የሆነ የጊዜው መከራ” ብሎታል። አሥራ አራት ዓመት በእሥር መማቀቅ ቀላል አይደለም። ይህ ግን በእኛ ዓይን ነው፤ በእግዚአብሔር ዓይን ግን እጅግ ቀላል ነው። በእግዚአብሔር ፊት አንድ ሺህ ዓመት እንደቅጽበት ነው። ኮሚኒዝም በዚህ ዓለም ላይ ከግማሽ ምዕተ ዓመት በላይ ሆኖታል። ይሁን እንጂ፡ አሁንም ቢሆን ተከታዮቹ የመዳን ተስፋ አላቸው።

ሰማያዊት ኢየሩሳሌም እንደ እናት ሁሉ ማንኛችንንም ትወደናለች፣ ለኮሚኒስቶችም ቢሆን የመንግሥተ ሰማያት በሮች አልተዘጉባቸውም። መርቶ ወደ ደኅንነት የሚያደርሳቸውም መብራት አሁንም በሙሉ ኃይሉ እያበራ ነው። እንደማንም ሁሉ ንስሐ መግባት ይችላሉ። ንስሐ እንዲያደርጉም ወንጌል እንሰበክላቸዋለን።

ኮሚኒስቶችን ሊለውጣቸው የሚችለው የፍቅር ኃይል ብቻ ነው። (ፍቅር ስል ግን ከኮሚኒዝም ትምህርት ጋር መደራደር ወይም መቻቻል ማለቴ አይደለም) ጥላቻ የሰዎችን ዓይን ያሳውራል። ሒትለር በፀረ—ኮሚኒዝም አቋሙ የታወቀ ሰው ነበር። ይሁን እንጂ ሊያጠፋቸው አልቻለም። እንዲያውም የዓለም አንድ ስስተኛው ክፍል ኮሚኒስቶች እንዲሆኑ አደረጋቸው፣ በእሥር ቤት ሆነን ለኮሚኒስቶች የፍቅር ወንጌልን የምንሰብክበት ዕቅድ ነደፍን። ትኩረት የሰጠነውም መሪዎቻቸውን ነው። አንዳንድ የሚሲዮን ዳይሬክተሮች የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ያጠኑት በጥቂቱ እንደሆነ አስባለሁ። ኖርዌይ ክርስትናን የተቀበለችው እንዴት ነበር? አስቀድሞ ንጉሥ አላፍ ጌታን በመቀበሉ ነበር። ሩሲያ ወንጌልን የተቀበለችው ንጉሥ ቭላድሚር ወንጌልን ስለሰማ ነበር። ፖላንድም እንዲሁ። በአፍሪካ ደግሞ የአንድ ጎሣ መሪ ጌታን ከተቀበለ ከተታዮቹም

ክርስቲያን ሊሆን ይችላል ። ስለሆነም መሪዎች ያላቸው ድርሻ ቀላል አይደለም ።

ግን – የኮሚኒስት መሪ በጌታ ሊያምን ይችላል ? ኮሚኒስታዊ መሪ እንደሚጨፈጭፏቸው ሕዝብ ሁሉ እርሱም ደስተኛ አይደለም ። ውስጣዊ ዋስትናም የለውም ። እንደምናውቀው አብዛኞቹ ኮሚኒስት መሪዎች ራሣቸው ታስረዋል ። ወይም ተገድለዋል ፤ ወይም ደግሞ አገር ጥለው ሸሽተዋል ። ለጊዜው ማንም ሊነካቸው ወይም ሊነቀንቃቸው መስለው ያልታዩ እንደ አጐዳ ፣ ዮዜፍ ፣ እና ቤሪያ የመሳሰሉ ባለሥልጣኖች እንደማንኛውም ፀረ—አብዮተኛ ሁሉ በጥይት ተደብድበዋል ። የሶቪየት የሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር ሽልፒን፡ የዩጎዝላቪያው የሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር ራንኰቪክ ፍፃሜ እንደ አሮጌ ዕቃ መጣል ሆኖአል ።

## ኮሚኒዝምን በመንፈሳዊ ደረጃ እንዴት መዋጋት ይቻላል?

ኮሚኒስታዊ አስተዳደር ማንንም ደስተኛ አያደርግም ። ሌላው ቀርቶ ራሣቸው በሥርዓቱ የተጠቀሙ ሁሉ ደስተኞች አይደሉም ። ትንሽ ኰሽ ባለ ቁጥር ከአሁን አሁን አፈና ተደረገብን በማለት ተሳቅቀው ነው የሚኖሩት ።

ብዙ የኮሚኒስት መሪዎችን በግል አውቃለሁ ። የውጥረትና የጭንቀት ኑሮ ነው የሚኖሩት ። እረፍት ሊሰጣቸው የሚችል ኢየሱስ ብቻ ነው ።

ኮሚኒስት መሪዎችን መለወጥ ማለት ዓለምን ካንዣበባት የጦርነት ሥጋት ማዳን ሊሆን ይችላል ። ከመጠን በላይ የሀገሪቱ ገንዘብ የጦር መሣሪያ ላይ ስለሚውል ሕዝቡ ከጊዜ ወደ ጊዜ በችግር እየማቀቀ ነው ። ኮሚኒስት መሪዎችን መለወጥ ማለት ዓለም⁻አቀፍ ውጥረትን ማርገብ ሊሆን ይችላል ። ኮሚኒስት መሪዎች ክርስቲያን እንዲሆኑ ማድረግ ማለት ክርስቶስንና መላእክትን ማስደሰት ሊሆን ይችላል ። የኮሚኒዝምን መለወጥ የቤተ ክርስቲያን ድል ነው ። ሚስዮናውያን በኒውጉኒያ ፣ በማዳጋስካር ወንጌልን በማስፋፋት ረገድ ከፍተኛ ተግባር እያከናወኑ ነው። ኮሚኒስት መሪዎች በክርስቶስ ካመኑ ግን እነዚህን አገሮች ወደ ጌታ ማምጣት አያዳግትም ። ለክርስትና አዲስ መንደርደሪያ ሊሆነው ይችላል።

ወደ ጌታ የመጡ ኮሚኒስቶችን አውቃለሁ ። እኔ ራሴም ሽንጤን ገትሬ እግዚአብሔር የለም በማለት የምከራከር ነበርሁ ። ወደ እምነት የሚመጡ እግዚአብሔር የለሾችና ኮሚኒስቶች እግዚአብሔርን በጣም ነው የሚወዱት ፤ ምክንያቱም ብዙ ኀጢአተኞች ናቸውና ።

ሚስዮናውያን አሠራራቸውን እንደሚገባ ሊያስቡበት ይገባል ። ደኅንነትን በሚመለከት አንፃር ሰዎች ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት እኩል ናቸው ። ከሚስዮናዊ አሠራር አንፃር ግን ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባውን ወገን ለይተን ማወቅ አለብን ። መሪዎች በጌታ ቢያምኑ ፥ ሕዝቡም በጌታ ያምናል ። ብቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ሕዝቡ መሪዎችን የመከተል አዝማሚያ አለው ። ኢየሱስ አገልግሎቱን የፈጸመው በመንደሮች ሳይሆን የመንፈሳዊ ነገር መዲና በሆነችው በኢየሩሳሌም ነበር ። ጳውሎስ ደግሞ በጊዜው ዓለምን አንቀጥቅጣ ትገዛ ወደነበረችው ሮም ለመድረስ ይቸኩል ነበር ።

መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቶስ የእባቡን ራስ እንደሚቀጠቅጥ ይናገ ራል። እኛ ግን ሆድ ሆዱን እየረገጥን የበለጠ እንዲያላግጥብን አድርገ ዋል። የእባቡ ራስ ያለው ኮሚኒዝም በሰፈነበት ስፍራ ነው ። እያንዳንዱ ክርስቲያንን ጨምሮ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና የሚስዮን ዳይሬክተ ሮች ትኩረት ኮሚኒዝም ላይ መሆን አለበት ። “የጌታን ሥራ በቸልታ የሚሠራ የተረገመ ይሁን” ተብሎ ተጽፎአል ፤ ስለዚህም ሥራችን የግብር ይውጣ መሆን የለበትም ። ቤተ ክርስቲያን በመንፈሳዊ ኃይል ኮሚኒዝምን መዋጋት አለባት ። ድል የሚገኘው በተከላካይነት ብቻ ሳይሆን በአጥቂነትም ጭምር ነው ። እስካሁን ቤተክርስቲያን ኮሚኒዝ ምን የተዋጋችው በተከላካይነት ብቻ ነበር ፤ ስለዚህም በተደጋጋሚ ተጠቅታለች ።

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር የብረት መዝጊያን ይሰብራል ይላል ፤ ኮሚኒዝምን ማድቀቅ ለእርሱ በጣም ቀላል ነው።

የመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን ወንጌልን የምታስፋፋው በኅቡዕ ወይም “ሕገወጥ” በሆነ መንገድ ነበር ። ስለዚህም አሸንፋለች ፤ ዛሬም የአሠራር ዘዴያችንን መለወጥ አለብን ።

ኮሚኒዝም እስከመጣበት ጊዜ ድረስ በአዲስ ኪዳን ስማቸው የተጠቀሰው አንዳንድ ሰዎች ለምን በቅጽል ስም እንደተጠሩ አይገባኝም ነበር ። ዛሬም በኮሚኒስት ዓለም ወንጌልን የምንሰብከው ሰዎች ጥቂቶች

ብቻ የሚያውቁት ስም አለን ።

የመጨረሻውን የፋሲካ እራት ለመብላት በፈለገበት ጊዜ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን "ወደ ከተማ ስትገቡ ማድጋ ውኃ የተሸከመ ሰው ይገናኛችኋል" አለ እንጂ ትክክለኛ ስፍራውን አለመናገሩ ለምን እንደሆነ አይገባኝም ነበር ። አሁንግን ገብቶኛል ። በኮሚኒስት አገሮች ወንጌልን በኅቡዕ የምናስፋፋ ሰዎች እርስ በርሳችን የምንግባባት የሚስጢር ቋንቋ አለን ።

አሠራራችንን ከለወጥን ፡ የጥንት ክርስቲያኖችን ምሣሌነት ከተከተልን ውጤት ማግኘት ይቻላል ።

በምዕራቡ ዓለም ያገኘኋቸው አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ግን ኮሚኒስቶችን አይወዱዋቸውም ። ለጠፉት የካርል ማርክስ ቤተሰቦች የመልካሙ ሳምራዊ ርኅራኄም ሆነ ፍቅር የላቸውም ። የአንድ ሰው እምነት የሚለካው ጥዋት ማታ በሚያነበንበው ቃል ሳይሆን ለእምነቱ ለመሞት ሲዘጋጅ ነው ።

በኅቡዕ የምትሠራው ቤተ ክርስቲያን አባሎች ግን ለእምነታቸው ለመሞት ዝግጁ መሆናቸውን በተለያየ መንገድ አስመስክረዋል ። ዛሬ ወደ ኮሚኒስት አገሮች በመሄድ ወንጌልን የሚያስፋፋ ቡድን መሪ ነኝ ፤ ምናልባትም እንደገና እሥራትና ስቃይ ይደርስብኝ ይሆናል ፤ ግን የምናገረውንም ሆነ የምጽፈውን አምንበታለሁ ።

በተለያየ መልኩ ከኮሚኒዝም ጋር የተወዳጁ አንዳንድ የሃይማኖት መሪዎች ስለ እምነታቸው ለመሞት ዝግጁ ናቸው ? ይህን ለመጠየቅ መብት አለኝ ።

ሰዎች ለመግባባት ካላቸው ፍላጐት የተነሣ ቋንቋ ሊዳብር ችሎ አል። በቋንቋ በመጠቀም ለሕይወት አስፈላጊ ስለሆኑ ነገሮች ይወያያሉ ፤ ስሜታቸውንም ይገልፃሉ ። የእግዚአብሔርን ሚስጢራዊ አሠራር ፤ የመንፈሳዊ ሕይወትንም ጥልቀትና ምጥቀት ግን የሰው ቋንቋ እንደሚገባ ሊገልፀው አይችልም ።

አንዳንድ ጊዜ የሰዎችን ጭካኔ ብዛት መግለጽም ያስቸግራል ። በናዚዎች እቶን—እሣት እንዲጣል የተፈረደበት ሰው ምን እንደሚሰማው እሱን ሆናችሁ ልትረዱለት ትችላላችሁ ? ልጅዋ ወደ እቶን—እሣት ሲጣል የምትመለከት እናትስ ምን እንደሚሰማት በእርስዋ ስፍራ ሆናችሁ ልታውቁላት ትችላላችሁ ?

እንደ እውነቱ ከሆነ ክርስቲያኖች በኮሚኒዝም የተቀበሉትንና አሁንም የሚቀበሉትን ስቃይ እንደሚገባ ልገልጽላችሁ አልችልም ።

ሉክሬቱ ፓትራስካኑ ከሚባል ሰው ጋር አብሬ ታስሬአለሁ ፡ ይህ ሰው ኮሚኒዝም በሩማንያ ውስጥ ሥር እንዲሰድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረገ ነው ። የተከፈለው ክፍያ ግን በራሳቸው በኮሚኒስቶቹ ወህኒ እንዲማቅቅ ነበር ። አእምሮው በትክክል የሚሠራ ጤነኛ ቢሆንም እብዶች ሆስፒታል አስገቡት ፡ በመጨረሻም እርሱ ራሱ አበደ ።

የሩማንያ መንግሥት ዋና ፀሐፊ የነበረችው አና ፑከርም ተመሣሣይ ዕጣ ደርሶባታል ። ክርስቲያኖችም በኤሌክትሪክ ሾክ እየተጠበሱ ይሰቃያሉ ፡ ሳያብዱ እንዳበደ ሁሉ በእግር ብረት ይጠፈራሉ ።

በቻይና አውራ ጐዳናዎች የተደረገውን የዓለም ሕዝብ ሲያስብ ይዘገንነዋል ። ለመቀጣጫ እንዲሆኑ እየተባለ ሰዎች በየመንገዱ በሬድ ጋርድ (ቀዩ ሠራዊት) ይሰቃያሉ ፡ እስቲ ማንም በማያይበት ሁኔታ በቻይና የሚሰቃዩ ክርስቲያኖችን ሁኔታ ለአንድ አፍታ አስቡት ።

የታወቁ ቻይናውያን የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት አባሎች እምነታቸውን ክደው ኮሚኒስት ለመሆን ባለመፍቀዳቸው ጆሮአቸው ምላሣቸውና እግራቸው ተቆርጦአል ። ይህ መጽሐፍ እስከተዘጋጀበት ድረስ ስለ ቻይና ክርስቲያኖች ስቃይ ያለን መረጃ በዚህ ያቆማል ።

የኮሚኒስቶች መጥፎነታቸው ሰዎችን ማሰቃየታቸውና መግደላ ቸው ብቻ አይደለም ፤ በሐሰተኛ ወሬ የሰዎችን ሕሊና ያቆሽሻሉ ። ሕፃናትንና ወጣቶችንም ይበክላሉ ። ኮሚኒስት መሪዎችን በየቤተ ክርስቲያኑ አስርገዋል ። ዓላማቸውም ቤተ ክርስቲያንንም ሆነ ክርስቲያኖ ችን ወደ ጥፋት መምራት ነው ። ወጣቶችን በእግዚአብሔርና በክርስቶስ እንዳያምኑ ያስተምሯቸዋል ። ሕፃናት እግዚአብሔር ወይም ኢየሱስ ክርስቶስ የሚሉትን ስሞች እንዲጠሉ ይነግሯቸዋል ።

ክርስቲያን ሰማዕታት ብዙ ዓመታት ከታሠሩ በኋላ ወደ ቤታቸው ሲመለሱ ልጆቻቸው በእምነታቸው ያላግጡባቸዋል ። እነርሱ ወህኒ በነበሩበት ወቅት ልጆቻቸው እግዚአብሔርን ክደዋል ። ታድያ ፡ እነዚህ ሰዎች የሚሰማቸውን ሐዘንና የልብ ስብራት በቃላት ልትገልጹት ትችላላችሁ ?

ይህ መጽሐፍ የተፃፈው በቀለም ብቻ ሳይሆን በሐዘን ከተወጋ ልብ

በሚፈሰዉ ደም ጭምር ነው ማለት እችላለሁ።

በዳንኤል ዘመን ስለ እምነታቸው ሲሉ በእቶን—እሣት የተጣሉት ሶስት እስራኤላውያን ወጣቶች ምንም ጉዳት ሳይደርስባቸው ወጥተዋል። የእሣቱ ወላፈን የልብሳቸውን ሽታ እንኳ አልለወጠውም ። ዛሬ ከኮሚኒስት እሥር ቤት የሚወጡ ክርስቲያኖች የጥላቻ ሽታ ወይም ጠረን የላቸውም ።

አንድን አበባ ብትደፈጥጡት ውስጡ ያለው መልካም መዓዛ ይወጣል ። ክርስቲያኖችም ለሚያሰቃዩዋቸው ኮሚኒስቶች ፍቅርን መግበዋል ። ያሰቃዩን ከነበሩት ብዙዎቹ የእምነታችን ተከታዮች ሆነዋል፣ ሲያሰቃዩን ለነበሩ ኰሚኒስቶች ከኢየሱስ ክርስቶስ የሚገኘውን የደኅንነትን የምሥራች ልንሰጣቸው ቆርጠው ተነስተናል ። ከዚህ የበለጠ ክቡር ስጦታ የለንም ።

እንደ እምነት ወንድሞቼና እህቶቹ በሰማዕትነት አልሞትኩም ፤ ለመፈታት እና ሩማንያን ለቅቄ ወደ ምዕራብ ዓለም ለመሰደድ በቅቻለሁ።

በምዕራቡ ዓለም ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ያየሁት ሁኔታ ግን በምሥራቁ ማለትም በኮሚኒስቱ ዓለም በኅቡዕ ወንጌልን ከሚያሠራጩ ክርስቲያኖች በጣም የተለየ ነው ። በምዕራቡ ዓለም ያሉ ክርስቲያኖች ኮሚኒስቶችን በጣም ነው የሚጠሉዋቸው ። ለአይሁዳውያን የተቋቋመ የሚስዮን ድርጅቶች አሏቸው ። ለእስላሞች የተቋቋመ የሚስዮን ድርጅቶች አሏቸው ፤ ለቡዲስት እምነት ተከታዮች የተቋቋሙ የሚስዮን ድርጅቶች አላቸው ፤ በአንድ ቤተክርስቲያን ያሉትን ወደሌላው ቤተ ክርስቲያን የሚያስኰበልሉ— የሚስዮን ድርጅት አሏቸው ። የዘላለምን ሕይወት ሳያገኙ ለሚጠፉት ኮሚኒስቶች ግን አንድም የሚስዮን ድርጅት እንኳ የላቸውም ። አይወዷቸውም ማለት ነው ፤ ቢወዷቸው ኖሮ ገና ድሮ ወንጌልን የሚያስፋፉ ድርጅት ባቋቋሙላቸው ነበር ። ኬሪ ለሕንዶች፣ ሀድሰን ቴለር ደግሞ ለቻይናዎች ከማሰባቸው የተነሣ ስመጥር የሚስዮን ድርጅቶችን አቋቁመውላቸዋል ።

አንዳንድ ቤተ ክርስቲያኖች ደግሞ ታማኝ ባለመሆናቸው ወይም ተባባሪ በመሆናቸው ኮሚኒስቶችን አጠናክረዋቸዋል ። ክርስቲያን ሣይሆኑ ክርስቲያን ነን የሚሉትን ኮሚኒስቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የመሪነት ስፍራ ሰጥተዋቸዋል ። ኮሚኒዝም ስለሚያስከትለው ችግር

ምዕመናንን አያስጠነቅቁዋቸውም ።

አንዳንድ የቤተ ክርስተያን መሪዎች ደግሞ ለኮሚኒስቶች ወንጌልን የማይሰብኩት ስላልተፈቀደላቸው እንደሆነ ይናገራሉ ። ለመሆኑ የጥንት ክርስቲያኖች በሮም ውስጥ ወንጌል እንዲያስፋፉ ኔሮ ቄሣር ፈቅዶላቸው ነበር? ኮሚኒስቶችን ካልወደዱ የገዛ ምዕመኖቻቸውንም አይወዱም ፡ ምክንያቱም ኮሚኒስቶችን ክርስቲያን ካላደረግናቸው እነርሱ ቤተ ክርስ ቲያንን ኮሚኒስት ያደርጓታል ። ከታሪክ እንማር !

በመጀመሪያዎቹ ጥቂት ምዕተ—ዓመታት ክርስትና በሰሜን አፍ ሪካ እየተስፋፋ ነበር ። እንደ አነ ቅዱስ አውግስጢኖስ ፤ እንደነ ቅዱስ ሣይፕሪያን እንደ እነ ቅዱስ አትናቴዎስ ፣ እንደ እነ ቴርቱሊያን ፡ የመሳሰሉ መምሕራን የተገኙት ከዚያ ነው ። በጊዜው የነበሩ ክርስቲያ ኖች ግን ቸልተኛ ሆኑ ፣ እስልምና እየተስፋፋ ነበር ፤ እስላሞችን በጌታ ከማሳመን ይልቅ ዳር ቆመው ሁኔታውን መታዘብ ያዙ ፤ ስለዚህም በእስልምና የክርስትና ሥር ተነቀለ ። እስከ ዛሬ ድረስ በዚያ አካባቢ ወንጌልን መስበክ አልተቻለም ።

እባካችሁ ከታሪክ እንማር ፤

የዘመነ ተሐድሶ እንቅስቃሴ መሪዎች የነበሩት ሐስ ፣ ሉተርና ካልቪን የጳጳሱ ተቃዋሚዎች ነበሩ ። ሕዝቡም እንዲሁ ከጳጳሣዊ ቀንበር ነፃ የመውጣት ፍላጐት ነበራቸው ። ይህ ጉዳይ በጊዜው ሃይማኖታዊ ብቻ ሣይሆን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ይዘትም ነበረው። ስለሆነም የእንቅስ ቃሴው መሪዎችና የሕዝቡ ፍላጐት ሊጣጣም ችሎአል ። ዛሬ ቢሆን በኅቡዕ ለኮሚኒስት ዓለም ወንጌልን የሚያስፋፉ መሪዎች ፍላጐትና በነፃው ዓለም በነፃነት የሚኖሩት ሰዎች ፍላጐት ተመሣሣይነት አለው ።

ኮሚኒዝም መጣል የሚችል ፖለቲካዊ ኃይል ያለ አይመስለኝም ። ኮሚኒስቶች የኒውክሌር ባለቤቶች ናቸው ። እነርሱን በወታደራዊ ኃይል ለመጣል መሞከር ለአዲስ ጦርነት መጀመር ምክንያት ሊሆን ይችላል ። ከዚህም በተረፈ ብዙ የምዕራባውያን አገር መሪዎች ብሬንዎሽድ ስለተደረጉ ኮሚኒዝምን ለመገርሰስ ፍላጐቱም የላቸውም ። ይህንንም ራሳቸውም ብዙ ጊዜ ተናግረውታል ። የዕፅ ሱሰኝነትን ፣ ውንብድናን ፡ ካንሰርንና የሳምባ በሽታን ለማጥፋት ብዙ ቢጥሩም ኮሚኒዝምን ግን የመንካት ፍላጐት የላቸውም ። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ከዕፅ ሱሰኝነት ፡ ከውንብድና ፤ ከካንሰርና ከሳምባ በሽታ ባላነሰ ሁኔታ ኮሚኒዝም

ለብዙዎች እልቂት ምክንያት ሆኖአል ።

ኢልያ ኤኽረንበርግ የተባለ የሶቪየት ፀሐፊ— "ስታሊን ሥራውን ሁሉ ትቶ የገደላቸውን ንፁሐን ሰዎች ስም መዘርዘር ቢጀምር ዕድሜ ልኩን ጽፎ የሚጨርሰው አይመስለኝም" ብሎአል ። ክርስቾቭ ደግሞ በሃያኛው የኮሚኒስት ፓርቲ ኮንግረስ ላይ ባሰሙት ንግግር "ስታሊን በሺህ የሚቆጠሩ ንፁሐን ኮሚኒስቶችን በግፍ ጨፍጭፎአል ፤ አሥራ ሰባተኛው ኮንግረስ ከመረጣቸው መቶ ሠላሣ ዘጠኝ አባሎችና ዕጩዎች ዘጠና ስምንቱ ማለትም ሰባው እጅ ታስረዋል በጥይት ተደብድበዋል" ብለው ነበር ።

እስቲ በክርስቲያኖች ላይ የተደረገውን እንገምት —

ክርስቾቭ ስታሊንን ቢያወግዙም እሳቸውም ከእርሱ የተሻለ አላደረጉም ። እስከ 1959 ድረስ በሶቪየት ሕብረት አገልግሎት ሲሰጡ ከነበሩት አብያተ ክርስቲያናት ግማሾቹ ተዘግተዋል ።

በቻይና ደግሞ በስታሊን ዘመን ከታየው የሚብስ ጭፍጨፋ እየተደረገ ነው ። ምንም አይነት በግልጽ የሚሠራ ቤተ ክርስቲያን አይገኝም ። በሩማንያም ሆነ በሩሲያ አዲስ ክርስቲያኖችን የማሰር ዘመቻ እየተካሄደ ነው ።

ከምዕራባውያን ጋር የተያያዘ ማንኛውንም ነገር በተለይም ደግሞ ክርስትናን እንዲፀየፉ ለወጣቱ ትውልድ የማይነገረው ውሸት የለም ።

በሩስያ ፣ ፖሊስ ቤተ ክርስቲያን በር ላይ ቆሞ ልጆች እንዳይገቡ ሲከላከል መመልከት አዲስ ነገር አይደለም ። ወደ ቤተ ክርስቲያን ሊገቡ የሚሞክሩ በጥፊ እየተመቱ ይባረራሉ ። ምዕራባውያኖችና ክርስትና ይጠፋሉ ብለው ስለሚያስቡ የእነዚህን ወጣቶች አእምሮ በጥላቻ መሙላት አለባቸው ።

ኮሚኒዝምን የሚቋቋም አንድ ኃይል ብቻ ነው ፣ ይህ ኃይል አረማዊ መንግሥት የነበረችውን ሮም የለወጠ ነው ። ቲቶንስ እና ቫይኪንግን የለወጠ ኃይል ነው ። ይህም ኃይል የወንጌል ኃይል ነው ። ይኸው ወንጌል ደግሞ በመላው ኮሚኒስት አገሮች ባስደናቂ ፍጥነት እየተስፋፋ ነው ።

እነዚህ ክርስቲያኖች መርዳት ለነፃው ዓለምም ሆነ ለቤተ ክርስቲያን ሞት ወይም ሽረት ማለት ነው ፣ ይህ ደግሞ የነፃው ዓለም ሕዝብን ብቻ ሳይሆን የማንኛውን የዴሞክራሲያዊ መንግሥትንም ተሣትፎ ይፈልጋል።

በኅቡዕ ወንጌልን የምታስፋፋው ቤተ ክርስቲያን ብዙ ኮሚኒስት መሪዎችን ወደ ክርስቶስ እያመጣች ነው ። የሩማንያ ጠ/ሚኒስትር ጆርጅሁ ደጅ የሞተው ኃጢአቱን ተናዝዞ ጌታን ከተቀበለ በኋላ ነበር ። አንዳንድ በኮሚኒስት አገሮች ያሉ መሪዎች ደግሞ እነርሱ ቢደብቁትም አማኞች ናቸው ። ይህ ሁኔታ ሊስፋፋ ይችላል ። ቲቶ እና ጐሙላካ ለውጥ አድርገናል ብለዋል ፤ ይሁን እንጂ በምትኩ አምላክ የለሽና በጭከና የሚያምን ፓርቲ ነው የተመሠረተው ። እኛ የምንፈልገው ሕዝቡን ወደ ክርስትናና ወደ ተሟላ ነፃነት የሚያመጣ ለውጥ ነው ።

ክርስቲያኖች እምነታቸውን በቅንነት እንደተቀበሉ ሁሉ ፤ አንዳንዶች ኮሚኒዝምን የተቀበሉት በፍጹም ቅንነት ነው ።

ኮሚኒዝም ዓለምን ይለውጣል ። በሰዎች መካከልም ወንድማማችነትን ያሰፍናል ፤ የሚል ልባዊ እምነት ነበራቸው ። አሁን ደግሞ ራሳቸው ኮሚኒስቶቹ እርስ በርስ ሲበላሉ እያዩ ነው ።

ኮሚኒዝም ምድርን ገነት ያደርጋል የሚል እምነት ነበራቸው አሁን ግን የራሳቸውን ሕዝብ መመገብ አቅቷቸዋል ። ስለዚህም ከካፒታሊስት አገሮች ስንዴ ወደ ሀገራቸው እየገባ ነው ።

ኮሚኒስቶች በመሪዎቻቸው ላይ ፍጹም እምነት አላቸው ። አሁን ግን ስታሊን ነፍሰ ገዳይ ፤ ክሩስቶቭ ደግሞ የማይረባ ተብለው በራሳቸው ጋዜጦች ሲወገዙ እያነበቡ ነው ። በሀገር አቀፍ ደረጃ ሲወደሱ የነበሩ እንደ ራኮሲ–ጌሮ–እና ፑከር ራንኮቪቺ ወዘተ. የመሳሰሉ ሰዎችም ዛሬ ስማቸው እየጠፋ ነው ፤ ከዚህም የተነሣ ሕዝቡ በመሪዎቹ ላይ እምነት የለውም ። ጳጳስ የሌላቸው ካቶሊኮች ሆነዋል ።

በኮሚኒስቶች ልብ ውስጥ ያለውን ባዶነት መሙላት የሚችል ክርስቶስ ብቻነው ። የሰው ልብ በተፈጥሮው እግዚአብሔርን ይፈልጋል ። ክርስቶስ ባዶውንስፍራ እስኪልሞላው ድረስ ፤ በእያንዳንዳችን ልብ ባዶነት አለ ። በወንጌል ውስጥ ራሳቸው ኮሚኒስቶችን መለወጥ የሚችል ኃይል አለ ፤ ለዚህ ምስክር ነኝ ።

ክርስቲያናዊ ፍቅር ወገናዊነት የለበትም ። ኢየሱስ “ፀሐይ ለኃጢአተኞችም ለፃድቃንም ታበራለች” አለ ። ክርስቲያናዊ ፍቅርም እንዲሁ ነው። ። በምዕራቡ ዓለም ያሉ ክርስቲያን መሪዎች ከኮሚኒስቶች ጋር ወዳጅነት መፍጠራቸው ደስ ያሰኛል ። ይሁን እንጂ ፤ ጠላቶቻችንን

ስንወድ ወዳጆቻችንን ወይም ወንድሞቻንን በመዘንጋት መሆን የለበትም።

ለኮሚኒስቶች ወዳጅነታቸውን የሚያሣዩት በደም በታጠቡበት እጅ አብሮ በመብላት እንጂ ፡ የክርስቶስን ወንጌል በመንገር አይደለም ። በኮሚኒስቶች የሚረገጡትን ዘንግተዋቸዋል ።

በአንድ ወቅት በጀርመን ያሉ የፕሮቴስታንትና የካቶሊክ ክርስቲያኖች 125 ሚሊዮን ዶላር ለረሃብተኞች ረድተዋል ። የአሜሪካ ክርስቲያኖች ደግሞ የበለጠ ሰጥተዋል ።

በዓለም ላይ ብዙ ረሃብተኞች አሉ ። ይሁን እንጂ ፡ በኮሚኒስት አገሮች ለእምነታቸው በመሰቃየት ላይ ካሉት ክርስቲያኖች የበለጠ ረሃብተኛ የለም ።

እኔ ራሴ ከሩማንያ መውጣት የቻልኩት ክርስቲያን ድርጅቶች በከፈሉልኝ ቤዛ ነው ። ከኮሚኒስት አገሮች በቤዛ ክፍያ ነፃነቱን ያገኘ ክርስቲያን እኔ ብቻ አይደለሁም ፤ ሌሎችም ሞልተዋል ።

በመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች መካከል—"የቤት ክርስቲያን የአይሁዳውያን ብቻ ናት ወይስ የአሕዛብም ጭምር ?" የሚል ጥያቄ ተነስቶ ነበር። ጥያቄው በጊዜው ትክክለኛ መልስ አግኝቶአል ። ዛሬ ደግሞ ይኸው ጥያቄ መልኩን ለውጦ መጥቶአል ፤ ክርስትና የዚህኛው ወይም የዚያኛው አገር ሕዝብ ሃይማኖት ብቻ አይደለም ። ኢየሱስ የተሰቀለው አንድ እጁን ወደ ምሥራቅ ፥ ሌላውን ደግሞ ወደ ምዕራብ ዘርግቶ ነበር ። ከኮሚኒስቶችም ሆነ ካፒታሊስቶች ጌትነቱን እንዲቀበሉ ይፈልጋል። "ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱና ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ" በማለት ለደቀመዛሙርቱ የነገራቸው ።

ደሙን ያፈሰሰው ለሁሉም ነው ፤ ሁሉም ወንጌልን ሰምተው ማመን አለባቸው

ለክርስቶስ ካላቸው ፍቅርና ቅንዓት የተነሣ ለኮሚኒስቶች ወንጌልን መስበክ ያስደስተኛል ። አንድም ለብ ያለ ሕይወት ያለው ሩሲያዊ ክርስቲያን አልገጠመኝም ። የዱሮ ኮሚኒስት ወጣቶች ታላላቅ የወንጌል አገልጋዮች ሊወጣቸው ይችላል ።

ክርስቶስ ማንኛውንም ሰው ከኃጢአት ነፃ ለማውጣት የሚፈልገውን ያህል ኮሚኒስቶችንም ከኮሚኒዝም ቀንበር ነፃ ማውጣት ይፈልጋል።

# ከተፈታሁ በኋላ

ከእሥር ከተፈታሁ በኋላ ባለቤቴ የወደፊት እቅዴ ምን እንደሆነ ጠየቀችኝ እኔም – የወደፊት እቅዴ አብዛኛውን ጊዜዬን ስለ መንፈሳዊ ነገሮች በማሰብና በማሰላሰል በብህትውና ለማሳለፍ እንደምፈልግ ነገርኳት ። የእርሷም ሃሣብ ከእኔ ጋር ተመሣሣይ ነበር ።

በወጣትነቴ በጣም ቀበጥባጣ ነበርሁ ፡ ነገር ግን እሥራት በተለይም ደግሞ ለብቻዬ ተዘግቶብኝ ያሳለፍኳቸው የእሥር ዓመታት ብዙ ለውጦኛል ፣ ረጋ ማለትን ስለ መንፈሳዊ ነገሮች በጥልቀት ማሰብና ማሰላሰልን አስተምሮኛል ። ዱሮ አእምሮዬን ይበታትንና ሃሣቤን ይከፋፍሉ የነበሩ ነገሮች አሁን ፀጥ ብለዋል ። ለብቻዬ ታስሬ በነበርኩበት ጊዜ ስለ ኮሚኒዝም ግድ አልነበረኝም ፤ እንዲያውም ኮሚኒዝም የሚባል ነገር እንኳ መኖሩን ዘንግቻለሁ ። ልክ በሰማያዊ ሙሽራ እቅፍ ውስጥ እንዳለሁ ሆኖ ነበር የሚሰማኝ ። ለሚያሰቃዩኝ ሰዎች እፀልያለሁ። ያለ አንዳች ችግር ከሙሉ ልቤ እንድወዳቸው ምንም የሚያውከኝ ነገር አልነበረም ።

እፈታለሁ የሚል ሃሣብ አልነበረኝም ፤ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ – "ምናልባት ብፈታ ቀሪውን የሕይወት ዘመኔን እንዴትና የት አሣልፋለሁ?" እያልኩ አስባለሁ ። እቅዴ በፀጥተኛ ቦታ ሁኜ ስለ እግዚአብሔር እና መንፈሳዊ ሚስጢራት ማሰብና ማሰላሰል ነበር ። በእሥር ቤት ከተለማመድሁት ጣፋጭ መንፈሳዊ እርካታና ሠላም ለመውጣት በመንፈሴ ካወቅሁት ሰማያዊ ሙሽራ ውበትና ሕብረት መለየት አልፈለግሁም።

እግዚአብሔር "እውነት" ነው መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እውነት የሚናገር "እውነት" ነው–ሥነ መለኮት (ቲዎሎጂ) ስለ "እውነት" የሚመራመር "እውነት" ክርስትና የእውነተኛ ሃይማኖት እውነት ነው ። እኛ ክርስቲያኖች ስለዚህ እውነት በተገለፀ ብዙ እውነቶች እናምናለን ፤ በዚህ ምክንያት አንድና ብቸኛ የሆነውን – "እውነት" እንደሚገባ አውቀነዋል ለማለት አንደፍርም ። በእሥር ቤት ከደረሰብን ረሃብ – ድብደባና ስቃይ የተነሣ ሥነ መለኮትን ወይም ስለ እውነት የሚመራመረውን እውነት ዘንግተነዋል ። ስለዚህም ያለን እድል "በእውነት" መኖር ብቻ ነው ። "የሰው ልጅ ባላሰባችሁት ጊዜና ሰዓት ይመጣል" ተብሎ

ተጽፎአል ። ልናስብ ባልቻልንባት ወቅት የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ የእሥር ቤታችን ክፍል እንደ እንቁ እስኪያበራ ድረስ ባላሰብነውና ባልጠበቅነው ወቅት ጐብኝቶናል ፤ የሚያሰቃዩን በሥጋ ክልል ውስጥ ናቸው ፤ መንፈሳችን ግን በጌታ ሐሴት ያደርጋል ። እንዲህ አይነቱን ደስታ ደግሞ ከምንም ጋር ማወዳደር ወይም በምንም መተካት ያስቸግራል።

ትክክል ነው ተብሎ በሚገመት ውጊያ ውስጥ እንኳ የመሳተፍ ዓላማ የለኝም ። ዓላማዬ ለክርስቶስ ሕያው ቤተ መቅደስ መገንባት ነው ። ይህንን ዓላማ ይዤ ነው ከእሥር ቤት የወጣሁት ።

ከተፈታሁ በኋላ ግን ከእሥር ቤቱ ስቃይ በበለጠ ሁኔታ የኮሚኒዝም አስቀያሚነት ማየት ችዬአለሁ ። ብዙ ሰባኪዎች ፤ ፖስተሮች ከዚያም በላይ ጳጳሳት እንኳ ሣይቀሩ በመጸጸት የኮሚኒስቶች ጠቋሚ እንደሆኑ ሲነግሩኝ ልቤ ክፉኛ ተወጋ ። እነዚህ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለኮሚኒስት ባለሥልጣኖች በመሰለል ባያገለግሉ ደግሞ ቤተ ክርስቲና ቸው ይዘጋና ጠቅላላ ምዕመናኑ ይበተናሉ ።

በእያንዳንዱ አካባቢ የሃይማኖት ጉዳዮችን የሚከታተል ተወካይ ይኖራል ። ይህ ሰው ራሱ የሚስጢር ፖሊሶች አባል ነው ። አስፈላጊ ሆኖ ባገኘው ጊዜ ማንኛውንም ቄስ ወይም ፖስተር አስጠርቶ ማን ወደ ቤተ ክርስቲያን እንደሚመጣ ፤ ማን ለእምነቱ ፍጹም ቅንዓት እንዳለው ፤ ማን ብዙ ነፍሣትን ወደ እምነት እንደሚያመጣ ፤ የመመርመር መብት አለው። ለመናገር ፈቃደኛ ካልሆነ ግን ይባረርና በምትኩ ሌላ "ካህን" ይተካል ። ወይም ከነጭራሹ ቤተ ክርስቲያኑ ይዘጋል ።

አብዛኞቹ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለኮሚኒስት ባለሥልጣኖች የሚጠቁሙ ናቸው ። ልዩነቱ አንዳንዶቹ በጣም አስፈላጊ ሚስጢሮችን ሲደብቁ ፤ ሌሎች ደግሞ በሥራው ብዙ ጊዜ ከመለማመዳቸው የተነሣ ሕሊናቸው ስለደነዘዘ ያዩትንና የሰሙትን ሁሉ የሚዘከዝኩ ናቸው ። አንዳንዶቹ ደግሞ በገዛ ፈቃዳቸው ወደው ጠቋሚ ሆነዋል ።

እናትና አባቶቻቸው በእምነት ምክንያት የታሠሩባቸው ወይም የተገደሉባቸው ሕፃናት አስጠግተው በሚያሣድጉዋቸው ሰዎች ላይ ጥቆማ እንዳደረጉ በጣም እያዘኑ አውግተውኛል ይህን ባያደርጉ ግን የመማር መብታቸው እንደሚነፈጋቸው ይዛትባቸዋል ።

አንድ ጊዜ የባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን ወዳዘጋጀችው ኮንፈረንስ

ሄጄ ነበር ። የስብሰባው ዓርማ ቀይ ባንዲራ ነበር ፤ የስብሰባው ዓላማ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን "መሪዎችን" ለመምረጥ ነበር ።

በግልጽ ሥራቸውን እንዲያካሂዱ ፈቃድ ያላቸው ቤተ ክርስቲያኖችን የሚመሩት የኮሚኒስት ፓርቲው ባስቀመጠው ሰው እንደሆነ አውቃለሁ ። ልክ ኢየሱስ እንደተናገረው የጥፋትን ርኩሰት በተቀደሰው ስፍራ ውስጥ አየሁት ።

ምን ጊዜም ቢሆን መልካምና መልካም ያልሆኑ ፓስተሮች ወይም ሰባኪዎች ይኖራሉ ። ሁሉም መልካም ወይም ክፉ ሊሆኑ አይችሉም ። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ግን ለመጀመሪያ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር የለም በሚሉና እስከ መጨረሻው ሃይማኖትን በሚቃወሙ ሰዎች እየተመራች ነው ። እነዚህን ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሠርገው እንዲገቡና የመሪነቱን ስልጣን እንዲይዙ ሁኔታዎችን የሚያመቻችላቸው ራሱ የኮሚኒስቱ ፓርቲ ማዕከላዊ ኮሚቴ ነው ።

ሌኒን– "ስለ እግዚአብሔር ወይም ስለ መንፈሳዊ ነገር የሚኖረን ሃሣብ ወይም ግምት ሁሉ ከማንኛውም ደዌና ተላላፊ በሽታ ይልቅ እጅግ አስከፊ ነው" ብሏል ።

በሶቪየት ያለው ኮሚኒስት ፓርቲ ደግሞ የተመሠረተው በሌኒን ስም ነው ። ለእነዚህ ሰዎች ሃይማኖት–ከካንሰር ፣ ከሳምባ በሽታና ፣ ከአባለ–ዘር ሕመም የከፋ ነው ። ታድያ ፣ እንደዚህ ያሉት ናቸው ለቤተ ክርስቲያን የሚበጃትን መሪ የሚመርጡላት…? በግልጽ እንዲሠሩ ፈቃድ የተሰጣቸው ቤተ ክርስቲያኖች እነሰም በዛም ከኮሚኒስት ባለሥልጣኖች

ከተለያዩ የገጠር አካባቢ የመጡ ሰዎች "የሕብረት እርሻ" በሚል ሰበብ እንዴት ርስታቸውን እንደተነጠቁ አጫውተውኛል ። ስለዚህም በገዛ መሬታቸው ቤተሰባቸውን እንኳ መመገብ የማይችሉ አገልጋዮች ሆነዋል ። ለራሳቸው ዳቦ ፣ ለሕፃናቶቻቸው ወተት ወይም በቂ ፍራፍሬ የላቸውም ። ይህ ሁሉ የሚሆነው ደግሞ በተፈጥሮ ሀብቷ ለሌሎች ለመትረፍ በምትችል አገር ውስጥ ነው ። ከችግራቸው የተነሣ ቀድሞ የግላቸው ከነበረው እርሻ ይሠርቃሉ ፣ የሠረቁትን ለመሸፈን ደግሞ መዋሸት አለባቸው ።

በየፋብሪካው የሚታየው ብዝበዛ ከካፒታሊስቱ ሥርአት እንኳ የከፋ እንደሆነ ሠራተኞች አጫውተውኛል ። የሚደረግባቸውን ብዝበዛ እንዳይቃወሙ ደግሞ መብት የላቸውም ።

ምሑራን ደግሞ ምንም እንኳ ባያምኑባትም እግዚአብሔር የለም የሚል አቋም እንዲኖራቸው ይጠበቅባቸዋል ። በከፍተኛ የትምህርት ተቋሞች ይህንኑ ማስተማር አለባቸው ።

የዓለም አንድ ሶስተኛው በዚህ ትምህርት ተበክሎአል ። ሐሰት ነግሶአል ፣ ነገሮች ውበታቸውን አጥተዋል ።

ብዙ በኀቡዕ ወንጌልን የሚያስፋፉ ወገኖችን አግኝቻለሁ ። አንዳንዶቹ እስከ አሁን አልታሰሩም ፤ አንዳንዶቹ ደግሞ ታስረው ከተፈቱ በኋላ ያንኑ አገልግሎት በመስጠት ላይ ያሉ ናቸው ። በሚስጢር በሚያደርጉት የወንጌል ስብሰባ ተካፍዬአለሁ ፣ የሚዘምሩት በእጅ ከተፃፉ የመዝሙር መፃሕፍት ነው ።

ታላቁ የእግዚአብሔር ሰው ቅዱስ አንቶኒ ትዝ ይለኛል ። ከዓለማዊ ነገሮች ተለይቶ ለሰላሣ ዓመታት ያህል በበረሃ ውስጥ በጾምና በጸሎት አሣልፎአል ። የክርስቶን መለኮታዊነት አስመልክቶ በአርዮስና በአትና ትያስ መካከል የተደረገውን ክርክር ሲሰማ ግን እውነት እንድታሸንፍ ለመርዳት ከነበረበት በረሃ ወደ እስክንድርያ መጥቶአል ። ቅዱስ ቤርናርድ ደግሞ ከዓለም ተለይቶ በተራራማዎቹ አካባቢ የሚኖር መንፈሳዊ ሰው ነበር ። የእየሱስን ባዶ መቃብር ላለማስነካት በሚደረገው የመስቀል ጦርነት ክርስቲያኖች አረቦችንና አይሁዶችን እየጨፈጨፉ መሆኑ ሲሰማ በሞኝነታቸው በጣም አዘነ ። የመስቀል ጦረኞችን ለመቃወም ከነበረበት ተራራ ወርዶ ከሕብረተሰቡ ጋር ተቀላቅሎአል ።

ማንኛውም እውነተኛ ክርስቲያን ለማድረግ እንደሚፈልገው ሁሉ የእየሱስን ፣ የሐዋርያው ጳውሎስና በየዘመናቱ የተነሱትን ታላላቅ ቅዱሣን ፈለግ ለመከተል ስል ለብቻዬ በጾምና በጸሎት ከመታቀብ ይልቅ በክርስቲያናዊ ውጊያ ለመሳተፍ ወስኜአለሁ ።

ታድያ ምን አይነት ውጊያ መሆን አለበት…?

በእሥር ቤት ውስጥ ክርስቲያኖች ለጠላቶቻቸው ፀልየዋል ። ስለ እምነታቸውም መስክረዋል ፤ ዋናው ዓላማችን ደኅንነትን እንዲያገኙ ነው ፤ ደኅንነት ሲያገኙ ደግሞ ደስ ይለናል ።

በኅቡዕ ወንጌልን የምታስፋፋውን ቤተ ክርስቲያን ለማጠናከር የወሰንኩት ኮሚኒስታዊ ሥርዓትን በመጥላቴ ነው ፣ ይህ ቀንበር በወንጌል ኃይል ሊሰበር እንደሚችል እርግጠኛ ነኝ ። ትኩረቴ የትውልድ አገሬ ሩማንያ ላይ ብቻ ሣይሆን መላው የኮሚኒስት ዓለም ላይ ነው ።

ነፃው ዓለም ግን በጣም ቸልተኛ ሆኖ ነው ያገኘሁት ። እንደ ሲኒያቭስኪ እና ዳንዔልን የመሳሰሉ ኮሚኒስት ፀሐፊዎች በመታዛቸው ዓለም ተቃውሞውን አሰምቶአል ። ክርስቲያኖች ስለ እምነታቸው ሲገላሉና ሲሰቃዩ ግን ክርስቲያኑ ሕብረተሰብ ድምፁን አላሰማም ።

ለመሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችንና አንዳንድ መንፈሳዊ ጽሁፎችን በማሰራጨቱ "መርዛማ" ጽሁፎችን በትነሃል ተብሎ እሥራት ስለተፈረደበት ስለ ወንድማችን ኩዝይክ የገደደው ማንን ነው…? በጽሁፍ የታተመ ስብከቶችን በማሰራጨቱ ስለ ተፈረደበት ስለ ወንድማችንን ፕሮኮቪብ የገደደው ማንን ነው? ክርስቲያን ጽሁፎችን ሲያሠራጭ በመገኘቱ እንደ ወንጀለኛ ስለ ተቆጠረውና ልጁን ስለ ተነጠቀው አይሁዳዊ ክርስቲያን ጕረንቫልድ የደረሰበትን የሚያውቅ ማነው? ለመጀመሪያ ጊዜ ከልጁ ከሚኻይ ነጥለው ሲወስዱኝ ምን እንደተሰማኝ አውቃለሁ ። ስማቸውን ዘርዝሬ ማቅረብ የማልችላቸው የሃያኛው ክፍለ ዘመን ሰማዕታት የተሰማቸው ሁሉ ይሰማኛል ።

የጥንት ክርስቲያኖች በሰንሰለት ታስረው ወደ አራዊት ይጣሉ የነበሩ ክርስቲያን ወገኖቻቸውን ሰንሰለት ይሳለሙ እንደነበር ሁሉ ፣ ዛሬም እኔ የክርስቲያን ሰማዕታትን ሰንሰለት እሣለማለሁ ።

በነፃው ዓለም ያሉ ክርስቲያኖች ግን እነዚህን ሰማዕታት አያስቡአቸውም ። በእነዚህ ክርስቲያኖች ላይ የጠቆሙት የሩሲያ ባፕቲስትና

ኦርቶዶክስ መሪዎች ለስብሰባ ወደ ኒውደልሒ ወይም ጄኔቫ በሚመጡበት ጊዜ ግን ሞቅ ያለ አቀባበል ይደረግላቸዋል ። እንደ እነዚህ አይነት ሰዎች በሩስያ ውስጥ የተሟላ የሃይማኖት ነፃነት እንዳለ ይናገራሉ ።

ሊቀ ጳጳስ ኒቆዲሞስ በሩስያ ውስጥ የሃይማኖት ነፃነት እንዳለ በተናገሩበት ወቅት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት መሪ በትልቅ አክብሮት ነበር የተቀበሉዋቸው ። ሁኔታዎቹ ግን በዚህ መልክ መቀጠል የለባቸውም ። ከሩማንያ እንድወጣና በክርስቲያኖች ላይ የሚደረገውን ተቃውሞ ለዓለም ሕብረተሰብ እንዳሰማ የተወሰነውም በዚህ ምክንያት ነው ።

ኮሚኒስቶችን ብወዳቸውም እንኳ ፣ ኮሚኒዝምን ግን ከማውገዝ ወደ ኋላ አልልም ። ኮሚኒዝምን ሳላወግዝ ወንጌልን መስበክ ትክክል መስሎ አይታየኝም ።

አንዳንድ ሰዎች –"ለምን ንፁሑን ወንጌል ብቻ አትሰብክም?" ይሉኛል ። ራሣቸው ኮሚኒስቶችም "ስለ ክርስቶስ ብቻ ስበክ ፤ ስለ ኮሚኒዝም ግን አትናገር" ብለውኝ ነበር ። ይህም የሚያሣየው "ንፁሑን ወንጌል ብቻ መስበክ" የሚሉ ወገኖችና ኮሚኒስቶቹን ይህን ለማለት ያነሣሣቸው ምክንያት ተመሣሣይ መሆኑን ነው ።

"ንፁህ ወንጌል" የሚሉት ምን አይነት ወንጌል እንደሆነ አይገባኝም ። ለመሆኑ መጥምቁ ዮሐንስ ሲሰብክ የነበረው ንፁህ ወንጌል አልነበረም እንዴ? መጥምቁ ዮሐንስ – "የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ" በማለት ከመስበኩም ሌላ በዘመኑ የነበረውን ንጉሥ ሄሮድስን በክፉ ሥራው ተቃውሞታል ፤ ስለዚህም ተሰይፎአል ። ለመሆኑ ጌታ እየሱስ ራሱስ ቢሆን "ወዮላችሁ እናንተ ግብዞች ፃፎችና ፈሪሣውያን … የእፉኝት ልጆች" በማለት በዘመኑ የነበሩትን የሃይማኖት መሪዎች ግብዝነት አልተቃወመም? ታድያ ስህተትን ስለተቃወመ ንፁህ ወንጌል አልሰበከም ሊባል ነው? እየሱስ የተራራው ስብከት በመባል የሚታወቀውን ስብከቱን ብቻ አልነበረም ያሰማው ፤ እንደዚያ ቢሆንማ ኖሮ አይሰቀልም ነበር ።

ኃጢአት በስሙ ነው መጠራት ያለበት ። ኮሚኒዝም ደግሞ እጅግ አደገኛ ሃጢአት ነው ። ከኮሚኒዝም ጋር የሚስማማ ወንጌል እውነተኛ ወንጌል ሊሆን አይችልም ። እውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን ስደትና መከራ የሚደርስባትም ከኮሚኒዝም ጋር ለመጣጣም ባለመቻልዋ ነው ።

እኔ ኮሚኒዝምን የማወግዘው "ፀረ—ኮሚኒዝም" አቋም እንዳላቸው ሰዎች አይደለም ። ሒትለር ፀረ–ኮሚኒስት ነበር ፤ ይሁን እንጂ ይህ አቋሙ ትክክለኛ ሊያደርገው አይችልም ። የብዙ ሚሊዮን ሰዎችን ነፍስ ያጠፋ ነፍሰ–ገዳይ ነው ። ኃጢአትን ብንጠላም ሃጢአተኛውን ግን እንወደዋለን ።

በኮሚኒስት አገር ብቻ ሣይሆን በምዕራቡ ዓለምም ተሰቃይቻለሁ ። እንዱ ያሰቃየኝ በኀቡዕ ወንጌልን የምታስፋፋው ቤተ ክርስቲያን ናፍቆት ነው ። አንድ ጥንታዊ የላቲን አባባል (Nudis nudum Christi sequi) ይላል ። የተራቆቱ ክርስቲያኖች የተራቆተውን ክርስቶስን ይከተላሉ ማለት ነው ።

በኮሚኒስት አገሮች መጠጊያ ያጡ ክርስቲየኖችን አውቃለሁ ። ቤት መሥራት አይችሉም ። ለምን ሊረባቸው? እነርሱ ሲታሠሩ ቤቱ እንደሚወረስ ያውቁታል ። አዲስና ያማረ ቤት ስትሠሩ በሰበብ አስባቡ ቤቱን የግላቸው ለማድረግ በሚፈልጉ ኮሚኒስት መሪዎች ልትታሠሩ ትችላላችሁ ። ሽማግሌ ወላጆቻችሁን ለመቅበር ፤ ቤተሰቦቻችሁን ለመሰናበት እንኳ ላይፈቀድላችሁ ይችላል ። ለመሆኑ እናታችሁ ማናት? ወንድማችሁ፡—እህታችሁስ? ይህን በመሰለ መንገድ ነው የኮሚኒስት አገር ክርስቲያኖች ከክርስቶስ ጋር ይመሳሰላሉ የምንለው ። እናትም ሆነ ወንድማችሁ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚፈጽም ሰው ነው ። ሰው ከሥጋ ዘመዶቹ ሊቆራረጥ ይችላል ፤ በመንፈሳዊ ሁኔታ ከተሳሰራቸው የእምነት ወገኖቹ ግን መቆራረጥ አይችልም ።

ወንጌልን በኀቡዕ የምታስፋፋው ቤተ ክርስቲያን መከራ የበዛባትና ድሃ ብትሆንም ፣ ስመ–ክርስቲያን ወይም ደግሞ ለስስተኛ አባሎች ግን የሉባትም ። በዚህች ቤተ ክርስቲያን ያለው አምልኮ ሥርአት ልክ ፤ እንደመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ክርስቲያኖች አምልኮ ልባዊ ነው ። ሰባኪዎቹ እንደ ዘመናችን ሰባኪዎች ከታላላቅ የቲዎሎጂ ትምህርት ቤት የተመረቁ አይደሉም ። ወይም ደግሞ ሆሚሊቲክ ማለትም የአሰባበክ ስልት የተማሩ አይደሉም ። ጴጥሮስ በጰንጠቆስጤ ዕለት ያሰማውን ስብከት የዘመናችን የቲዎሎጂ ፕሮፌሰሮች ምናልባት ዝቅተኛ ውጤት ሊሰጡት ይችሉ ይሆናል ፣ በኮሚኒስት አገሮች ያሉ ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስ እንደፈለጉት ስለማያገኙ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ

ችን በቃላቸው አላጠኑም ። በዚህ ላይ ደግሞ በእሥር ቤት በሚያሳልፉዋ ቸው ብዙ ዓመታት መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ቀርቶ በዓይናቸው አይተውም አያውቁም ። ብዙ መከራ ቢደርስባቸውም እግዚአብሔር ሰዎችን የሚወድድ አምላክ ለመሆኑ ግን ጥርጥር የላቸውም ። "ቢገድለ ኝም እንኳ እርሱን አመልካለሁ" እንዳለው ኢዮብ በእግዚአብሔር ላይ ያላቸው እምነት የሚያወላውል አይደለም ። እየሱስ በመስቀል ላይ ተቸንክሮ በነበረበት ወቅት እንኳ እግዚአብሔርን "አባት" ብሎ ጠርቶታል ።

የእምነት ነፃነት በተገፈፈባቸው ኮሚኒስት አገሮች ወንጌልን በኀቡዕ የምታስፋፋውን ቤተ ክርስቲያን ውበት የሚያውቅ ሁሉ "ነፃ ነት" አለን በምትለው ቤተ ክርስቲያን አምልኮ መርካት አይችልም ። እኔ እንደምረዳው በነፃው ዓለም ያለችው ቤተ ክርስቲያን ለመሞት እያጣጠ ረች ነው ። አዝዋልድ ስፒንግለር የተባለ ፀሐፊ "ዘ፡ዲክላይን አፍ ዘ፡ ዌስት" በሚለው መጽሐፉ ፦

"ለመሞት እያጣጣራችሁ ነው ። የሞት ባሕርይ ታይቶባችኋል ፤ የሞት ጥላ አጥልቶባችኋል ። እጅግ የበዛው ብልጽግናችሁ ፤ በጣም የተባባሰው ድኅነታችሁ ፤ — ካፒታሊስነታችሁና ሶሻሊስትነታችሁ ፣ ጦርነቶችና አብዮታችሁ ፣ እግዚአብሔርን መካዳችሁና ጽልመተኝነታ ችሁ ፣ (ፒሲሚዝም) አመፃችሁና የፍቺ ብዛታችሁ ፣ የመከሰም ፣ ከዚያም አልፎ የሞት ምልክቶች ናቸው ። እነዚህ ሁኔታዎች በእስክንድርያ ፣ በግሪክና ሮምን በመሳሰሉ የጥንት ሥልጣኔያቸው የከሰመ አገሮች ታይተው ነበር ፤ ዛሬም በእናንተ ላይ እያታዩ ናቸው ።" ብሎአል ።

ይሁ መጽሐፍ የተፃፈው በ1926 ቢሆንም ፣ ከዚያን ጊዜ ወዲህ በግማሹ የአውሮፓ ክፍል ዲሞክራሲ እየደከመ ፣ ሥልጣኔም እየከሰመ ነው ። የተቀረው የአውሮፓ ክፍል ደግሞ ገና እንቅልፍ ላይ ነው ፤ ኮሚኒስቶች ግን ዛሬም ቢሆን አልተኙም ። በምሥራቅ አውሮፓ ኮሚኒዝም ቢደክምም በምዕራቡ ግን እያቆጠቆጠ ነው ። በምዕራቡ ዓለም ያሉ ኮሚኒስቶች በምሥራቁ ዓለም ያሉ ኮሚኒስቶችን ጭካኔ መቀበል ይከብዳቸዋል ። በሚቻላቸው ሁሉ እምነታቸውን እያስፋፉ ነው ። እኛ ክርስቲያኖች ግን እውነትን የያዝነው በግማሹ ልባችን ነው ። እነርሱ ግን ውሸቱን በሙሉ ልባቸው ይዘውታል ።

በነፃው ዓለም ያሉ የሥነ መለኮት ሊቃውንት በማይረባ ነገር ሲጨቃጨቁ ጊዜያቸውን ያሳልፋሉ ።

በ1493 የዳግማዊ ማሐሜት ሠራዊት ኮኒስታንቲኖ ፕልን ከተማ ከቦአት ነበር ። የባልካን አገሮች በማን እጅ እንደሚሆኑ ወሣኝ የትግል ወቅት ቢሆንም ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ግን በዚያችው በጠላት በተከበበች ከተማ ውስጥ ሆነው — "ለመሆኑ የእምዬ ማርያም ዓይን ምን ይመስል ይሆን? የመላክትስ ጾታቸው ምንይሆን? ቅበዓ-ቅዱስ ውስጥ ዝንብ ብትገባ ታረክሰዋለች ወይስ ቅብዓ-ቅዱሱ ይቀድሳታል?" በሚሉ የማይረቡ ጉዳዮች ላይ ይከራከሩ ነበር ። ዛሬም ቢሆን ክርስቲያኖች በጣም ጥቃቅን በሆኑ ጉዳዮች እርስ በርሣቸው እየተነታረኩ ነው ። የኮሚኒዝምን ከፋት ፣ የክርስቲያኖችን ስቃይ ፣ ሲያነሱት ግን አይሰማም።

መፍትሔ ስለማናገኝላቸው ብዙ የቲዎሎጂ ጥያቄዎች እንወያየ ለን። ስለ አምልኮ ሥርአት ፣ የቱ አስፈላጊ ፣ የቱ አላስፈላጊ እንደሆነም እንነታረካለን ።

አንድ ጊዜ ሰዎች ተሰብስበው ሲወያዩ አንዱ "ለመሆኑ በመርከብ እየተጓዛችሁ ባለበት ወቅት መርከቡ የመስጠም አደጋ ቢያጋጥመው እና መርከቡ ውስጥ ካሉት መፃሕፍት ውስጥ አንድ መጽሐፍ ብቻ እንድትወ ስዱ ቢፈቀድላችሁ የትኛውን መጽሐፍ ትወስዱ ነበር? በማለት ጠየቃ ቸው ። አንደኛው ሰው "መጽሐፍ ቅዱስን" አለ ። ሌላው ደግሞ "ሼክስፒርን" አለ ። በዚህ ጊዜ ግን የጥያቄው አቅራቢ የሁሉንም መልስ ካዳመጠ በኋላ —"እኔ የምመርጠው ግን እንዴት ጀልባ መሥራት እንደሚቻል የሚረዳኝን መጽሐፍ ነው ፤ ጀልባውን ሠርቼ ወደምፈልገው ስፍራ ከደረስሁ በኋላ የፈለግሁትን መጽሐፍ ለማግኘት ሰፊ ዕድል ይኖረ ኛል ።" አለ ። እኛም ብንሆን ባለን ነፃነት ለመኖር የተነጠቅነውን መብት ለማስከበር ቅድሚያ መስጠት አለብን ።

እየሱስ — "እውነት ነፃ ታወጣችኋለች" አለ ። እውነትን ለመስ ማት ደግሞ ነፃነት ያስፈልጋል ። በማይረቡ ነገሮች ከመጨቃጨቅ ይልቅ፣ በአንድነት ሆነን የእምነታችን ተፃራሪ የሆነውን ሐሰተኛ ትምህርት መቋቋም አለብን ።

በ1966 እ·ኤ·አ· የታተመ ኢስቪስታ እና ደርቤንስካይስ የተባሉት የሶቪየት ጋዜጦች "በእርሱ ሞት የኃጢአት ስርየት ይገኛል" በማለት የሶቪየት ባፕቲስቶች ሕፃናትን እንደገደሉ ጽፎ ነበር ። የዚህ ዓይነት

ከአምልኮ ጋር የተያያዘ ግድያ ወንጀል በአይሁዳውያንም ላይ ሲሰነዘር ነበር ።

በ1959 እ·ኤ·አ· በሩማንያ ውስጥ ክሎጅ በሚባል ወህኒ ቤት ላዛሮብስኪ ከሚባል ወጣት ጋር ታስሬ ነበር ። ይህ ወጣት የታሠረው አንዲት ልጃገረድ ገድለሃል ተብሎ ነበር ፤ ምንም እንኳ ገና የሠላሣ ዓመት ወጣት ቢሆንም ያለ ጊዜው ሸብቶአል ፤ ያልሠራውን ወንጀል እንዲያወጣ በማለትም ጥፍሮቹን ነቃቅለዋቸዋል ። በዚህ ሁኔታ አንድ ዓመት ከተሰቃየ በኋላ ግን ወንጀለኛ አለመሆኑ ታውቆ በነፃ ተለቆአል ። ግን ዕድሜ ልኩን ከሰውነት ተራ ወጥቶ ነው የኖረው ።

ሌላ ጊዜ ደግሞ የሶቪየት ፕሬስ በባፕቲስቶች ላይ ሊታመን የማይቻል ነገር ጽፎባቸው ነበር ። ጽሁፉ ሕብረተሰቡን አስቆጥቷል ። ያለስማቸው ስም ለተሰጣቸው ክርስቲያኖች ግን ከፍተኛ የልብ ስብራት ሆኖአቸዋል ።

ሊቀ ጳጳስ አሌክሲ እና ሊቀ ጳጳስ ኒቆዲሞስ የኮሚኒስት መጠቀሚያ መሆናቸውን በመቃወም ሊቀ ጳጳስ የርሞጊን እና የተቀሩት ሰባት ጳጳሳት (ሶቪየት ሕብረት) የደረሱበትን የሚያውቅ ማነው? የኮሚኒዝም መጠቀሚያ ለመሆን ባለመፈለጋቸው በሩማንያ እሥር ቤት የሞቱ ጳጳሳት አውቃለሁ ። ይህን ባላውቅ ኖሮ ስለ እነዚህ ጳጳሳት አይገደኝም ነበር ።

እንደ ኒኮላይ ኤሽሊማን እና ጊለብ ያኩኒን የመሳሰሉ አገልጋዮች ደግሞ ለቤተክርስቲያን የእምነት ነፃነት እንዲሰጣት መጠየቃቸው እንደ ወንጀል ተቆጥሮባቸው የቤተክርስቲያኑ መሪ ራሱ ለተወሰነ ጊዜ ከአገልግሎት አግዶአቸዋል ። “ለተወሰነ ጊዜ” ከአገልግሎት የታገዱ ሰዎችን አውቃለሁ ። ይህንንም “የቤተክርስቲያን የውስጥ አሠራር” በሚል ሽፋን የሚያቀነባብሩት ኮሚኒስት መሪዎች መሆናቸውን አውቃለሁ ። ይሁን እንጂ ፤ በመንግሥታዊ አካላት የታቀፉት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከሚስጢር ፖሊሲች ጋር እጅና ጓንት ሆነው እንደሚሠሩ የታወቀ ነው። እነርሱ የሚያገልሉዋቸውን አገልጋዮች ፡ የሚስጢር ፖሊሲች ደግሞ ስቃይ ድብደባና ሌላም ወንጀል ያደርሱባቸዋል ።

በኮሚኒስቶች ካምፕ ስደት ስለሚደርስባቸው ሰዎች ሳስብ ይሰቀጥጠኛል። ስለሚያሰቃዩዋቸው ሰዎች ዘላለማዊ ዕጣ ማሰቡም ያሣዝነኛል። ከዚያም ባላነሰ ሁኔታ ደግሞ በነፃው ዓለም ተቀምጠው ወገኖቻቸውን የማይረዱት ክርስቲየኖች ያበሣጩኛል ።

በብቸኛና ገለልተኛ ስፍራ ሆኜ ቀሪውን ሕይወቴን ባሳልፈው እወዳለሁ ፤ ይህ ግን የሚቻል አልመሰለኝም ። ኮሚኒዝም በፀረ–እምነት አቋሙ እየሰፋ ነው ። ኮሚኒስቶች ቲቤትን ከወረሩ በኋላ ለመንፈሳዊ ነገሮች ከፍተኛ ትኩረት ይሰጡ የነበሩትን ሁሉ አስወግደዋቸዋል ። በእኛም አገር ቢሆን ተመሣሣይ ነገር ተደርጐአል ። አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ለሌላ አገልግሎት ውለዋል ። ያሉት ጥቂቶቹ የሃይማኖት ነፃነት ያለ ለማስመሰል የውጪ ጐብኚዎችን ለመሸንገል የሚጠቀሙባቸው ናቸው ። ስለዚህም ሕይወቴን በፀጥታና በገለልተኛ ስፍራ ለማሳለፍ ያለኝን ዓላማ ለመሸሽ እንዳደረግሁት ሙከራ ነው የሚቆጠርብኝ ።

የግል ሕይወቴን ችግር ላይ እንደሚጥል ባውቅም የዚህ ውጊያ ተካፋይ መሆንን መርጫለሁ ። ምናልባት አንድ ቀን ብሰወር ፤ ኮሚኒስቶች አፍነው እንደወሰዱኝ እርግጠኛ መሆን አለባችሁ ።

በ1948 ዓ·ም ከአደባባይ ላይ አፍነው ከወሰዱኝ በኋላ የውሸት ስም ሰጥተው አስረውኛል ፡ በዚያ ዘመን የመንግሥቱ ዋና ፀሐፊ የነበሩት ሐና ኮከር "በአሁኑ ሰዓት ውምብራንድ የሚገኘው በኮፐንሐገን ከተማ ነው" በማለት ነበር በጊዜው የስዊዲን አምባሰደር ለነበሩት ለሰር ፓትሪክ ቮን የነገሩዋቸው ። አብረዋቸው የነበሩት ስዊዲናዊ ቄስ ከእሥር ቤቱ በሚስጢር የላኩላቸው ደብዳቤ እጂማቸው ስለነበር የተነገራቸው ውሸት መሆኑን ተረድተዋል ። ከተገደልኩም ገዳዬ ሌላ ሣይሆን የኮሚኒስቶቹ ቅጥረኛ መሆን አለበት ። ሌባ ነው ፤ ግብረ ሰዶማዊ ነው ፤ ዘማዊ ነው ፡ ወይም ደግሞ ሌላ ሥነ-ምግባራዊ ጉድለት ብትሰሙብኝ ከዚህ ቀደም የኮሚኒስት መሪዎች "እርፊህ ካልተቀመጥህ ስምህን እናጠፋዋለን" በማለት የተሰነዘሩብኝን ዛቻ አትዘንጉ ።

በአሜሪካ ሴኔት ፊት ቀርቤ ምስክርነቴን ከሰጠሁ ወዲህ የሩማንያ ኮሚኒስት መሪዎች እኔን ለማጥፋት ስላደረጉት ውሣኔ ከታመነ ምንጭ ሰምቻለሁ ። ምናልባት አካሌን ይገድሉ ይሆናል ፤ ወይም ደግሞ መልካሙን ስሜን ያጠፉ ይሆናል ። በወዳጆቼ ላይም ዛቻና ማስፈራራት ሊካሄድባቸው ይችላል ፡ ይህን የሚያደርጉበትም ብዙ ዘዴ አላቸው ።

የሆነው ቢሆንም ዝም አልልም ። የእናንተ ድርሻ ደግሞ የምለውን በጽሞና መመርመር ይሆናል ። እኔ ከሞትሁ በኋላ ምናልባት የደረሰብኝ ችግር ሥነ ልቦናዊ ውጥረት ወይም መቃወስ እንደሆነ ብታስቡም እንኳ በዜጐቼ ላይ የዚህ አይነት ስቃይ የሚያደርሰው ኮሚኒዝም ምን አይነት

አስተዳደር ቢሆን ነው? በማለት መጠየቅ ይኖርባችኋል ። ሰዎች ከምሥራቅ ጀርመን ወደ ምዕራቡ ቤተሰቦቻቸውን ይዘው የሚሰደዱት ምን ቢደርስባቸው ነው ..? ከተገኙ እንደሚረሸኑ እያወቁ ለምንድን ነው በሕይወታቸው ተወራርደው ከኮሚኒስቱ ምድር የሚሸሹት ..?

ወደ ምዕራቡ ዓለም ከወጣሁ ወዲህ የተለያዩ የሥነ መለኮት ሰሚናሪዎችን ጐብኝቻለሁ ። ስለ ደወል ፣ ስለ ቅዳሴ ፣ እንዲሁም ዛሬ ስለማንጠቀምባቸው የቤተ ክርስቲያናት የሚሰጠውን ሌክቸር አድምጬ አለሁ ። የሥነ ፍጥረት ፣ የአዳምና የሔዋን ፣ የኖህ ጥፋት ውሃ ፣ የሙሴ ተአምራትና ኢየሱስ ከድንግል መወለዱ ትንሣኤው ፣ ውሸት እንደሆነና የኢየሱስ አጽምም አሁንም በአንድ ያልታወቀ ስፍራ ሊገኝ እንደሚችል የቴዎሎጂ ተማሪዎችን ሲያስተምሩ ሰምቻለሁ ። እንደ እነዚህ መምህራን ከሆነ ትንቢቶቹ የተፃፉት ከተፈጸሙ በኋላ ነው ። የሐዋርያቱ መልእክቶችም ትክክል አይደሉም ። የዩሐንስ ራዕይን የፃፈው የአእምሮ ችግር ያለበት ሰው ነው ። ይሁን እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ ፣ ቅዱስ መጽሐፍ ነው ይላሉ ። እንደ እነርሱ ከሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ከኮሚኒስቶች ጋዜጦች የሚልቅ የተቀነባበረ ውሸት ያለበት መጽሐፍ መሆኑ ነው ።

ይህንን ነው እንግዲህ ዛሬ ቤተ ክርስቲያንን በመምራት ላይ ያሉት ሰዎች በሰሚናሪ በነበሩበት ጊዜ የተማሩት ። የሚኖሩትም ይህ አስተሳሰብ በሰፈነበት ማኅበረሰብ ነው ። ታድያ እንዲህ ያለ የተሣሣተ ነገር ለሚወራበት ጌታ እንዴት ታማኝ ሊሆኑ ይችላሉ ?

ሰዎችን ስለ አንድ የሕይወት ገጽታቸው ብቻ መውቀሱ ትክክል አይደለም ። እንደዚህ ካደረግን በኢየሱስ ዘመን እንደነበሩት ፈሪሣውያን መሆናችን ነው ። ፈሪሣውያን ስለሰንበት የነበራቸውን ወግ ባለማክበሩ ብቻ ነበር ኢየሱስን የጠሉት ፤ ውበቱንና መልካምነቱን እንዳያዩ ግን ዓይኖቻቸውን ጨፈኑ ፤

ስለ ኮሚኒዝም የተሣሣተ አመለካከት ያላቸው የቤተክርስቲያን መሪዎች በሌላ በብዙ መልክ ትክክል ሊሆኑ ይችላሉ ። ምናልባትም ቅንነት ሊኖራቸው ይችላል ፤ ከስህተታቸው ለመመለስም ዝግጁ ሊሆኑ ይችላሉ ።

አንድ ጊዜ ከአንድ በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከፍተኛ ሹመት ከነበረው ሰው ጋር ነበርኩ ። ይህ ሰው በሃላፊነት የሚመራውን

ምዕመን በመዘንጋት ለኮሚኒስቶች ያደረ ሰው ነው ። አንድ ምሽት በግቢው ውስጥ ባለ አትክልት ስፍራ ውስጥ ሆነን ስንጫወት ፣ ስለ ኮብላዩ ልጅ ታሪክ ነገርኩት ። አንዳንድ ክርስቲያናዊ መዝሙሮችንም ዘመርኩ ለት ። ይህ ሰው በዚያችው ቅጽበት በስህተቱ ተጸጽቶ ተመለሰ ።

ሌላ ጊዜ ደግሞ አብሮኝ ታስሮ የነበረ ቄስ ምናልባት ይፈቱኝ ይሆናል በማለት ኮሚኒስታዊ ሥርአትን የሚደግፍ የክህደት ጽሁፍ አዘጋጅቶ ነበር ። ስህተቱን ስነግረው ወዲያውኑ ያዘጋጀውን ጽሁፍ ቀደደው ።

ሌላው ችግሬ ደግሞ ዓላማዬን የቅርብ ወዳጆቼ እንኳ አለመረዳታ ቸው ነው ፤ በኮሚኒስቶች ላይ ጥላቻና ቂም እንደማናፍስ አድርገው ነው የሚገምቱኝ ።

ክላውዲ ምንቴፊዮሬ የተባለ ፀሐፊ ኢየሱስ ጸፎችና ፈሪሣውያንን ማውገዙ "ጠላትህን ውደድ" "ለሚቃወሙዋችሁም ፀልዩ" የሚለውን የራሱን ትምህርት ይፃረርባታል ብሏል ። ሌላው ፀሐፊ ደግሞ ኢየሱስ ይህን ያደረገው በትምህርት ባለመግፋቱ ነው ብሏል ።

ሞንቴፊዮሬ ክርስቶስ ላይ የሰነዘረው ነቀፋ ትክክል አይደለም ። ምንም እንኳ ክፉ ሥራቸውን በአደባባይ ቢያወግዝም ኢየሱስ ፈሪሣውያ ንን ይወዳቸው ነበር ። እኔም ብሆን ኮሚኒስቶችንና አገልጋዮቻቸውን ባወግዝም እነርሱን ግን እወዳቸዋለሁ ።

የተለያዩ ሰዎች "ኮሚኒስቶችን ተዋቸው፣ መንፈሳዊ ትምህርት ላይ ግን አትኩር" ይሉኛል ። አንድ ጊዜ በናዚዎች ወህኒ ቤት የተለያየ መከራ ከደረሰበት ክርስቲያን ጋር እነጋገር ነበር ። ስለክርስቶስ የማሰማውን ስብከት ቢደግፍም ኮሚኒዝምን በመቃወም በማሰማው ንግግር ግን እንደማይስማማ ነገረኝ ። እኔም በናዚ ዘመን የነበሩ ክርስቲያኖች ናዝዝምን ማይቃወሙ ዝም ብለው ከመጽሐፍ ቅዱስ ቢያስተምሩ ምን ይሰማህ ነበር ? አልኩት ። የሰጠኝ መልስ – "ናዚዝም እኮ የስድስት ሚሊዮን አይሁዳውያን ገዳይ ነው ፤ ስለዚህም በዘመኑ የነበሩ ክርስቲያን መሪዎች ማውገዛቸው ትክክል ነው" የሚል ነበር ። እኔም "ኮሚኒዝም ደግሞ የሠላሣ ሚሊዮን ሩሲያውያን ፣ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ቻይናውያን፣ እና አይሁዳውያንን ጨፍጭፎአል ፤ ታድያ ፣ መቃወም ያለብን አይሁዳ ውያን ሲገደሉ ብቻ ነው? አልኩት "ይህን እንኳ አላውቅም ነበር" ከማለት በቀር ሌላ መልስ ሊሰጠኝ አልቻለም ።

የናዚም ሆነ የኮሚኒስት ፖሊሶች ደበድበውኛል ፤ የሁለቱም በትር ያምማል ፤ ምንም ልዩነት አላየሁም ።

ክርስትና ኮሚኒዝምን ብቻ ሳይሆን ማንኛውንም ክፉ ነገር መቃወም አለባት ፤ ኮሚኒዝምን በመቃወም ላይ ብቻ ማትኩር የለብንም ።

ኮሚኒዝም በአሁኑ ጊዜ በመንቀሳቀስ ላይ ያለ አደገኛ የቤተ ክርስቲያን ተቃዋሚ ነው ። ኮሚኒዝምን ለመቃወም መተባበር አለብን ።

የሰው ሕይወት ግብ ክርስቶስን ወደመምሰል ደረጃ ማደግ ነው ። ይህን መቃወም ደግሞ ዋነኛ የኮሚኒስቶች ዓላማ ሆኖአል ። ኮሚኒስቶች የሃይማኖት ተቋዋሚ ናቸው ፤ ከሞት በኋላ ሰው ወደ ማዕድንነት ይመለሳል ፤ ብለው ስለሚያምኑ ፤ ከዚህ ወድያ ሕይወት መኖሩን መስማትእንኳ አይፈልጉም ።

የሚናገሩት ስለ ብዙኀኑ ብቻ ነው ። ኢየሱስ ከአንድ ሰው ያስወጣቸው አጋንንት "ብዙኀን" ነን ብለው እንደነገሩት ከአዲስ ኪዳን መመልከት ይቻላል።

"ግላዊ ሣይኮሎጂ" የሚለውን የአልፍሬድ አድለርን መጽሐፍ ሲያነብ በመገኘቱ ብቻ የታሠረ ሰው አውቃለሁ ። ሁል ጊዜ ስለ ግል፡ ስለ ግል፡ ስለ ግል፡ ብቻ ለምን ስለ ብዙኀኑስ አናስብም። በማለት ባለሥልጣኑ አምባረቁበት።

ኢየሱስ ግን ግላዊ ባሕርይ እንዳለንም ነው ያስተማረው ። ግላዊነታችንን እንድንጥል ከሚያስተምር ኮሚኒዝም ጋር ምንም ሕብረት ሊኖረን አይችልም ። ኮሚኒስቶቹ ራሣቸውም ይህንን አሳምረው ያውቃሉ። "ሣይንስና ሃይማኖት" በተሰኘው የራሣቸው መጽሔት "ሃይማኖት ከኮሚኒዝም አይስማማም ጠላቱ ነው፤ የኮሚኒስት ፓርቲው ዓላም ሃይማኖትን መደምሰስ ነው ፤ የኮሚኒዝም ፕሮግራም ሰዎች ከሃይማኖት ባርነት ነፃ የሚወጡበት ሕብረተ ሰብ መፍጠር ነው" ብሏል ።

ክርስትና ከኮሚኒዝም ጋር አብሮ መኖር ይችላልን? ኮሚኒስቶች ለዚህ ጥያቄ መልስ ሲሰጡ "የኮሚኒስት ፓርቲው ዓላማ ሃይማኖትን መደምሰስ ነው" ይሉናል ።

በኮሚኒስት አገሮች ወስጥ ወጣቶች ማንኛውንም ዓይነት ሃይማኖት እንዲከተሉ አይፈቀድም ። አረጋውያንና በዕድሜ የገፉ ሰዎች ግን የማንኛውም ሃይማኖት ተከታይ መሆን ይችላሉ የሬዲዮ ፣ የቴሌቪዢን ፣

የትያትሩና የጋዜጦች ዓላማም የክህደትን ትምህርት ማስፋፋት ነው ።

በኮሚኒስት አገሮች ውስጥ በኅቡዕ የወንጌልን እውነት የምታስፋፋው ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችዋን የምታሰለጥንባት የሥነ–መለኮት ትምህርት ቤት የላትም ። እንዲያውም አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን ፖስተሮች ጠቅላላውን መጽሐፍ ቅዱስ አንብበው የማያውቁ ናቸው ።

ምን ያህሉ የክህነት ሥልጣን እንዳላቸው እነግራችኋለሁ ። አንድ ጊዜ ከአንድ ሩሲያዊ አገልጋይ ጋር ተገናኘሁና ሥልጣነ–ክህነት የሰጠው ማን እንደሆነ ላቀረብኩለት ጥያቄ ሲመልስ – "ሥልጣነ ክህነት ለመስጠት የሚታመን ጳጳስ የለንም ፤ መንግሥታዊ ዕውቅና ያላቸው ቤተ ክርስቲያኖች ደግሞ የኮሚኒስት ፓርቲውን ድጋፍ ላላገኘ ለማንም ቢሆን ክህነትን አይሰጡም ፤ ። ስለዚህም አሥር ወጣት ክርስቲያኖች በቅርቡ በሰማዕትነት ወደሞተ ጳጳስ መቃብር ሄድን ። ሁለት ወጣቶች እጃቸውን መቃብሩ ላይ አደረጉ ። ሌሎች ደግሞ በዙሪያችን ሆነው መንፈስ ቅዱስ የአገልግሎት ኃይልን እንዲሰጠን ፀለዩልን ። ሥልጣነ ክህነትን ያገኘነው በቆሰሉት የኢየሱስ እጆች እንደሆነ እርግጠኞች ነን" አለኝ ። እንደእኔ እምነት ከሆነ የዚህ ሰው ክህነት በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት ያለው ነው ።

እንግዲህ ይህን በመሰለ ሁኔታ ራሣቸውን ለአገልግሎት በሰጡና ምንም ዓይነት ሥነ መለኮታዊ ትምህርት በሌላቸው ሰዎች ነው ቤተ ክርስቲያናችን ትመራ የነበረችው ።

በብዙ መልክ የመጀመሪያውን ክፍለ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ትመስላለች ። ለመሆኑ በወንጌል ኃይል ዓለምን የገለባበጡት እነዚያ የጥንት ክርስቲያኖች ከየትኛው የሥነ መለኮት ሰሚናር ነበር የተመረቁ? ማንበብ እንኳ የሚችሉ ነበሩ? መጽሐፍ ቅዱስስ ነበራቸው"? ይሁን እንጂ በእነርሱ አማካይነት እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ተናግሮአል ።

መሰብሰቢያ ካቴድራል የለንም ፣ ስለዚህም የምንሰበሰበው በጫካ ውስጥ ነው ፤ በሙዚቃ መሣሪያዎች ፈንታ በወፎች ጫጫታ ነው ዝማሬያችን የሚታጀበው ፤ በዕጣን ፈንታ የዱር አበባዎች መዓዛ ነው አምልኮአችንን መልካም መዓዛ የሚሰጠው፤ በጌጥ የተንቆጠቆጠ ልብሰ ተክህኖ ባይኖረንም ዘወትር በምንለብሰው ልብስ ጌታን እናመልከዋለን ፤ የሻማና የጧፍ ብርሃን በጨረቃና በከዋክብት ብርሃን ተተክቶአል ።

የዚህችን ቤተ ክርስቲያን ውበት ለመግለጽ ቃላት ያጥሩኛል ። ።

ብዙ ጊዜ አምልኮአችንን ከጨረስን በኋላ እንታሠራለን ፤ ልክ ሙሽራ በወርቅ ካቴና እንደምታጌጥ ሁሉ እነዚያ ክርስቲያኖችም የእጃቸው መታሠሪያ ሰንሰለትን የሚቀበሉት በደስታ ነው ። እውነተኛ ክርስቲያኖችን ያየሁት በመጽሐፍ ቅዱስና በዚህች በኅቡዕ ወንጌልን በምታስፋፋ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ነው ። በቅርቡ አንድ የራሽያ ጋዜጣ በተለያዩ ሃላፊነት ላይ ያሉ ሰዎች እንኳ ከአማኞች ጋር ስላላቸው ሕብረት እያማረረ ጽፎአል ። ጋዜጣው ስለ አንዲት ቅስቀሣ ድርጅት ውስጥ ስለምትሠራ ወጣት ሴት ጽፎ ነበር ። ከሥራ እንደወጣች በቀጥታ ወደቤትዋ ትሄድና ባልዋ እስኪመጣ ድረስ ትጠብቃዋለች ፤ ከራት በኋላም ከሌሎች ጋር መጽሐፍ ቅዱስን ወደሚያጠኑበትና ወደሚፀልዩ በት ስብሰባ ተያይዘው ይሄዳሉ ። እንዲህ ያሉ ሰዎች ደግሞ በመላው ኮሚኒስት አገር ይገኛሉ ። መንግሥታዊ ዕውቅና ወዳላቸው አብያተ ክርስቲያናት ቢሄዱ ሰዎች ያዩዋቸዋል ። የሚሰሙት የተበራረዘ ስብከ ትም የልባቸውን ጥማት አያረካም ። ስለዚህም በኅቡዕ ከሚያመልኩ እውነተኛ ክርስቲያኖች ጋር ማምለክን መርጠዋል ። የእምነታችን ተካፋዮችና ደጋፊዎች የሆኑ በተለያየ ድርጅት ውስጥ በከፍተኛ ሃላፊነት ላይ ያሉ ሰዎች አሉን ።

በኮሚኒስት ሩሲያ "ሕፃናትን ማጥመቅ ፤ ትክክል ነው አይደለም?" የሚል ክርክር የለም ። ጳጳሱ ሊኖራቸው ስለሚገባው የሥልጣን ገደብም ደንታ የላቸውም ። ስለ ቅዱሳት መፃሕፍት አተረጓጎምም እርስ በርሳቸው አይጋጩም ስለእግዚአብሔር ሕልውና የሚያቀርቡትም ሃሣብ በጣም ያስደንቀኛል ።

እግዚአብሔር የለም በማለት ለሚከራከሩዋቸው ሰዎች የሚያቀር ቡት መልስ ቀላል እና ተራ ይመስላል ። ግን ብዙውን ጊዜ የተከራካሪዎች አፍ ያስይዛል ። "ለምሳሌ የምሣ ግብዣ ላይ ተገኝተሃል እንበል የቀረቡትን የተለያዩ ምግቦች ማንም ሳያዘጋጃቸው እንዲሁ በአጋጣሚ ተገኙ ማለት ይቻላል ? እንደምናየው ተፈጥሮ የተለያዩ ምግብ አይነቶች የቀረቡባት ሰፊ ማዕድ ትመስላለች ፤ ለመሆኑ ለሰው ልጅ ጠቃሚ የሆኑትን የተለያዩ የምግብ ዓይነቶችን ያቀነባበረው ማነው? በአጋጣሚ ማለት አይቻልም። አጋጣሚ እውር ነው። በእግዚአብሔር ካላመንህ

ስለዚህ ጉዳይ የምትሰጠው ምን ገለፃ ይኖርሃል …?

አንድ ጊዜ ደግሞ ከዚህ በኋላ ሕይወት የለም ለሚል ሰው ስለሰጡት መልስ ሰምቼ በጣም ነው የተገረምኩት "ለምሣሌ ማሕፀን ውስጥ ካለ ፅንስ ጋር ለመነጋገር ቢቻል ኖሮ ከዚያው ካለበት ከጠባቡ የእናቱ ማሕፀን ውጪ ሕልውና መኖሩን አይቀበልም ፡፡ እየዋለ እያደረ ግን እጅና እግር ሲያወጣ ይህ ለምን አስፈለገ…? እዚህ ውስጥ በእጆቼ የምሠራው ሥራ የለኝም ። ሌላው ቀርቶ እጆቼን የምዘረጋበት ስፍራ እንኳ የለኝም ። ይህ እግርስ ለምን አስፈለገ? እዚህ ውስጥ እንደሆነ የምሄድበት ስፍራ የለም ። — ምናልባት ከዚህ ውጪ ሕልውና ይኖር ይሆን እንዴ? ይህ እግር ከዚህ ውጪ ባለው ሰፊ ዓለም ውስጥ የምረማመድበት ይሆን እንዴ? ይህ እጅስ የምሠራበት ይሆን? ማለቱ አይቀርም ። ስለዚህም ምንም እንኳ ባያየውም ከእናቱ ማሕፀን ውጪ ሕልውና ሊኖር እንደሚችል ይገነዘባል ። የእኛም ሁኔታ ይህን ይመስላል ። በእውቀትና በጥበብ እያደግን በሄድን መጠን ከዚህ ከአሁኑ ዓለም ውጪ ስላለው ሕልውና እንረዳለን ። በጥበብ ፣ በእውቀትና በማስተዋል ማደጋችን ለአሁኑ ብቻ ሣይሆን ለሚቀጥለውም ዓለም ሊያዘጋጀን ነው ። ከሞት ባሻገር ላለው እውነታ እንዘጋጃለን።

ኢየሱስን በተመለከተ ደግሞ ኮሚኒስቶች ኢየሱስ የሚባል ሰው በዓለም ታሪክ አልነበረም የሚል አቋም ነው ያላቸው ። ክርስቲያኖች ግን ለዚህ የሚሰጡዋቸው መልስ በጣም ቀላል ነው "የእኔ ወንድም ፣ የያዝከው ጋዜጣ (ፕራቭዳ) የዛሬ ነው ወይስ የትናንት? እስቲ እባክህን እንዴ ልመልከተው ። አሃ! የጥር 4 ፣ 1983 ነው ለካ! ለመሆኑ ካሌንደሩ ከየት ተነስቶ ነው መቁጠር የሚጀምረው? መቼም በታሪክ ውስጥ ካልነበረ ሰው ልደት ሊሆን እንደማይችል የታወቀ ነው ። እናንተ ኮሚኒስቶች ኢየሱስ የሚባል ሰው አልነበረም ትላላችሁ ፣ ዓመታትን የምትቆጥሩት ግን ከእርሱ ልደት ተነስታችሁ ነው ። በእርግጥ ኢየሱስ በሥጋ ከመወለዱ በፊትም ነበር ፣ ይሁን እንጂ ከእርሱ በፊት የነበረው ጊዜ የባከነ እንደሆነ ስለተገነዘበ ፣ የሰው ልጅ ከእርሱ ልደት በመነሣት ነው ዓመታትን የሚቆጥረው ። ስለዚህም ኢየሱስ በዚህ ዓለም ለመኖሩ የእናንተ በኮሚኒስቶቹ ጋዜጣ እንኳ ይመሰክርለታል ማለት ነው ።

ከብዙ አገሮች ታሪክ እንደምንመለከተው ኮሚኒስቶች ወደ ሥልጣን የወጡት አንዳንድ የሃይማኖት መሪዎችን መስላል በማድረግ ነው ።

ለምሣሌ ሩሲያን የተመለከትን — እንደሆነ ሠርጊስ የተባለ ጳጳስ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጐአል ። ከቅርብ የሥራ ባልደረቦቹ አንዱ — ማርክሲዝም በክህደት (ኤቲዝም) ቃላት የተፃፈ ወንጌል ነው” ማለቱ ይታወሣል። እንዲህ አድርጐም ቲዎሎጂ የለ!

በሐንጋሪ ደግሞ ፋዘር ባሎግ የሚባል ጳጳስና የተለያዩ ፕሮቴስታንት አገልጋዮች ኮሚኒስቶች ሙሉ በሙሉ ሀገሪቱን እንዲቆጣጠሩ መሰላል ሆነውላቸዋል ።

ሩማንያ ውስጥ ኮሚኒስቶች ሥልጣን የጨበጡት ቡርዱሲያ በሚባል የኦርቶዶክስ ቄስ ረዳትነት ነው ። ከዚያ አስቀድሞ ይህ ሰው ፋሽስት ነበር ። ያለፈ በደሉን ያስተካከለ ይመስል ጊዜ ሲያመቸው ደግሞ የኮሚኒስቶች መጠቀሚያ ሆነ ። የኮሚኒስት መንግሥት በተመሠረተበት ወቅት “ይህ መንግሥት ምድራዊ ገነትን ይሰጠናል ፤ ስለዚህም ሰማያዊ ገነት አያስፈልገንም” በማለት የተናገረው ይኸው ቄስ ነበር ።

ኮሚኒስቶች መጠቀሚያ የሚሆናቸውን ሰው ለቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ይሾማሉ ። እውነተኛ ክርስቲያኖችን ግን ያገልሉዋቸዋል ። አብያተ ክርስቲያናትን ሙሉ በሙሉ ከመዝጋት ይልቅ ጥቂቶቹን ብቻ መደበኛ ተግባራቸውን እንዲያከናውኑ ፈቅደውላቸዋል ። አስተዳዳሪዎቹ ግን የራሳቸው ሰላዮች ናቸው ። ይህም ክርስቲያኑን ሕብረተሰብ ለማጥመድና ለምዕራቡ ዓለም ደግሞ ፡ የሃይማኖት ነፃነት እንዳለ ለማስመሰል የሚጠቀመበት ዘዴ ነው ። ምዕራባውያን በጽሁፍ የሰፈረ ነገርን በሙሉ የማመን ዝንባሌ አላቸው ። ኮሚኒስቶች አንዳንድ ቤተ ክርስቲያኖችን በማሳየት የሃይማኖት ነፃነት እንዳለ ያሳምኑዋቸዋል ።” ‘ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ’ በማለት ጌታ በሰጠን መመሪያ መሠረት የወንጌልን እውነት እንሰብካለን “ለጥፍረት ሁሉ...” የሚለው ቃል ወጣቶችንም እንደሚጨምር መዘንጋት የለብንም ።

ምንም እንኳ ሰብከቱ የኮሚኒስት መሪዎችን የሚያቆላምጥ ቢሆንም፡ ጥንታዊው የኦርቶዶክስ ቅዳሴ ይዜማል ። የተለያዩ ፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናትም ጥንታዊና ውብ መዝሙሮች አልተለወጡም።

መንግሥታዊ እውቅና ያላቸው አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች በሙሉ ለኮሚኒስቶች ያደሩ ናቸው ማለት አግባብ አይሆንም ። ክርስትና የውጊያ ሃይማኖት ነው ። በኅቡዕ ወንጌልን የሚያስፋፉ አብያተ

ክርስቲያን መሪዎችም በጣም የሚፈለት ካልሆኑ በቀር እውቅና ካላቸው ቤተ ክርስቲያኖች ጋር አብረው ይሠራሉ ። በሩማንያና በሩስያ ያሉ አንዳንድ ታዋቂ ገዳማትን ለራሳቸው ፍላጐት መጠቀሚያ ለማድረግ ባደረጉት ሙከራ ኮሚኒስቶች ከፍተኛ ተቃውሞ እንደደረሰባቸው ይታወቃል ። በጠቅላላ ሶቭየት ሕብረት መንግሥታዊ እውቅና ያላቸው አብያተ ክርስቲያናት ከአምስት እስከ ስድስት ሺህ የሚገመቱ ሲሆኑ ፣ ተመጣጣኝ ሕዝብ ብዛት ባላት በአሜሪካ ውስጥ ወደ ሶስት መቶ ሺህ የሚቆጠሩ አብያተ ክርስቲያናት አሉ ። በሶቭየት ውስጥ መንግሥታዊ እውቅና ያላቸው አብያተ ክርስቲያናት ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሱ ናቸው ። ቤተ ክርስቲያን የሚባሉትም አነስተኛ ክፍሎች ያላቸው ቤቶች ናቸው ። የውጪ ጐብኚዎችም የሰውን ግርግር ሲያዩ በኮሚኒስት አገሮች የሃይማኖት ነፃነት አለ ብለው ያስባሉ ። ለሰባት ሚሊዮን ፕሮቴስታንቶች አንድ መጠነኛ ክፍሎች ያለው "ቤተ ክርስቲያን" እንደሆነ አያውቁም ። ለእነዚህ ሰዎች መንፈሳዊ አገልግሎት ለመስጠት ደግሞ በኅቡዕ መሥራት አለብን ። በአንድ ሀገር ውስጥ ኮሚኒዝም እየተስፋፋ በመጣ መጠን በኅቡዕ ከመሥራት በቀር ቤተ ክርስቲያን ሌላ ምርጫ ሊኖራት አይችልም ።

ኮሚኒስቶች የክርስትና እምነትን ያዋረዱና ያጥላሉ እየመሰላቸው የተለያዩ ጥቅሶች ያሉባቸውን የነቀፋ ጽሁፎችን በብዛት ያሰራጫሉ ። ኤልያስ በቁራዎች እንደተመገበ ሁሉ እኛም እግዚአብሔር የለም የሚሉ ሰዎች በሚያሠራጩዋቸው የቅዱሣት መፃሕፍት ጥቅሶች መንፈሳችንን እንመግባለን ።

አንድ ጊዜ ኮሚኒስቶች – "አስቂኙ መጽሐፍ ቅዱስ–ለሚያምኑትና ለማያምኑት" በሚል ርዕስ አንድ መጽሐፍ አዘጋጅተው ነበር ። ዓላማቸው መጽሐፍ ቅዱስ ምን ያህል የማይረባ መሆኑን ለማሣየት ስለሆነ ፣ በተደጋጋሚ ከመጽሐፍ ቅዱስ ይጠቅሣሉ ። ይህን መጽሐፍ ስናገኝ የተሰማን ደስታ ከፍተኛ ነበር ። ነቀፋው ደካማ ስለነበር የፈለጉትን ዓላማ ሊመታላቸው አልቻለም ። ምንም እንኳ ኮሚኒስቶች ይህን ጽሁፍ ያዘጋጁት በእምነት ላይ ለመዘባበት ቢሆንም ፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱ በጣም ብዙ ክፍሎች ስለነበሩት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ቅጂዎች እንዲታተሙ ተደረገ ። የቅዱሣት መፃሕፍት ቃላት በራሱ

በዲያብሎስ እንደበት ቢነገርም – እውነተኝነታቸው አያቋርጥም ።

ጽሁፉ እንዲታተም ብዙ ደብዳቤዎችን ለአሳታሚው ድርጅት ጻፍን ፣ አሣታሚው ድርጅትም ገበያ በማግኘቱ ደስ እያለው ብዙ ቅጂዎችን ያትም ጀመር ። እነዚህን እያሌ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ያለበትን መጽሐፍ እንዲያትም ደብዳቤ የሚጽፉለት ግን ክርስቲያኖች እንደሆኑ አያውቅም ። ቅዱሣት መፃሕፍትን የሚያገኙበት ምንም መንገድ ስላልነበር ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስን ሐሰተኛነት ለማሣየት ብዙ ጥቅሶችን በማካተት የቀረበውን መጽሐፍ ክርስቲያኖች በታላቅ ናፍቆት ነበር የተቀበሉት ።

አንድ ጊዜ ደግሞ አንድ ፕሮፌሰር በአንድ ስብሰባ ላይ ኢየሱስ ውሃውን ወደ ወይን ጠጅ የለወጠው በምትሐት ነበር በማለት ንግግር እያደረገ ነበር ። እፊት ለፊቱ ውሃ ያለበት ጠርሙስ ተቀምጦ ነበር "እያችሁ ኢየሱስ ውሃውን ወይን ጠጅ አድርጌአለሁ" ያለው ይህን የመሰለ ኬሚካል ሰዎች ሳያዩት ውሃ ውስጥ በመጨመር ነበር ፤ አለና ፣ አንድ ኬሚካል ውሃው ውስጥ ጨመረ ። እውነትም ውሃው የወይን ጠጅን መልክ ያዘ ። ፕሮፌሰሩም በመኩራራት – "ኢየሱስ ያደረገው ውሃውን ወደ ወይን ጠጅ መለወጥ ብቻ ነበር ። እኔ ግን ይህን የምታዩትን ወይን ጠጅ እንደገና ወደውሃነት ልለውጠው እችላለሁ" – ካለ በኋላ አንድ ሌላ ኬሚካል ጨመረበት ። ወይን ጠጁ እንደገና ወደ ውኃነት ተለወጠ ። ሕዝቡ በከፍተኛ መገረም ውስጥ በነበረበት ወቅት ግን አንድ ክርስቲያን በስብሰባው መካከል ቆመና – "ጓድ ፕሮፌሰር – ባደረጉት አስደናቂ ነገር ሁላችንም በጣም ነው የተገረምነው ፤ ግን ጓድ ፕሮፌሰር አንድ ነገር ብቻ እንድጠይቅ ይፈቀድልኝ እስቲ እፊትዎ ያለውን ውኃ ይቅመሱት" አለው ፕሮፌሰሩም – "በፍጹም የማይቻል ነው ፤ ምክንያቱም ውሃው ተመርዞ አል" የሚል መልስ ነበር የሰጠው ። ክርስቲያኑም – "አዎ በእርስዎ እና በክርስቶስ መካከል ያለው ልዩነትም እዚህ ላይ ነው ። እርስዎ መርዝነት ያለው ወይን ጠጅ አቀረቡልን ፣ ክርስቶስ ግን ለሰው ልጅ ሕይወት ጣዕም የሚሰጥ ወይን ጠጅን ነበር ያቀረበልን ። ከሁለት ሺህ ዓመታት በኋላ እንኳ ጣዕሙ አልተቀነሰም" አለው። ምንም እንኳ ክርስቲያኑ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ቢታሠርም ሁኔታው ተስፋፍቶ በመወራቱ የብዙዎች እምነት ጠነከረ ።

እንደ ዳዊት ታናሾችና ደካሞች ነን ፤ ይሁን እንጂ ፣ እግዚአብሔር

ከእኛ ጋር በመሆኑ እንደ ጐልያድ ግዙፍ የሆነው የሐሰት ትምህርት ሊቋቋመን አልቻለም ። እውነት የእኛ ናት ።

አንድ ጊዜ ደግሞ አንድ ካድሬ ለአንድ ፋብሪካ ሠራተኞች “እግዚአብሔር የለም” በሚል ርዕስ ንግግር እያደረገ ነበር ። ማንኛውም የፋብሪካው ሠራተኛ በስብሰባው ላይ የመገኘት ግዴታ ነበረበት ። ብዙ ክርስቲያን ሠራተኞችም ስብሰባው ላይ ነበሩ ። “እግዚአብሔር ወይም ክርስቶስ የሚባል ነገር የለም ፤ ከዚህ ዓለም ውጪ ምንም መንፈሳዊ ዓለም የለም ፤ ማንኛውም ነገር ቁስ አካል ብቻ ነው” በሰውና በቁስ–አካል መካከል ምንም ልዩነት የለም ። በማለት ካድሬው ይናገር ነበር ።

አንድ ክርስቲያን ግን ጥያቄ እንዲጠይቅ ካስፈቀደ አንድ ወንበር አነሣና ጣለው ወደፊት በመሄድም ካድሬውን በጥፊ አጮለው ፡ በዚህም ምክንያት በስብሰባው ውስጥ አምቧጓሮ ተፈጠረ ። ክርስቲያኑ ግን “–በሰውና በቁስ አካል መካከል ምንም ልዩነት የለም ብለኸን ነበር። ወንበሩን እንስቼ ስጥለው ስሜት ስለሌለው ምንም አልተቃወመኝም ፡ ወይም አልተቆጣም፤ አንተን በጥፊ ስለመታሁህ ግን ይኸውና ተቃውሞህን እየገለጽህ ነው ። ይህ ከሆነ ደግሞ የምታስተምረን ሁሉ ሐሰት ነው ። ሰው ከቁስ አካል በላይ ነው ። ሰው መንፈሳዊ ፍጡር ነው አለው ። ያው እንደተለመደው ክርስቲያኑ ወደ ወህኒ ቤት ተወሰደ ።

ይህን በመሰለ ተራና ቀላል አቀራረብ ነው ክርስቲያኖች በከፍተኛ ጥናትና ምርምር የተዘጋጀ የክህደት ትምህርትን እያሳፈሩ ያሉት ። በእሥር ቤት በነበርኩበት ጊዜ አንድ ባለሥልጣን ፡ “ይህን የማይረባ ሃይማኖታዊ አስተሳሰብህን ከአእምሮህ አውጥተህ የማትጥለው እስከ መቼ ነው?” በማለት እያንጓጠጠ ጠየቀኝ ። እኔም – “ብዙ እግዚአብሔር የለም ሲሉ የነበሩ ሰዎች በሚሞቱበት ጊዜ ሲፀፁና የክርስቶስን ስም ሲጣሩ አይቼአለሁ ። ክርስቲያን በመሆኑ ግን በመሞታቸው ሰዓት ስለተፀፀተ ሰው ሰምተህ ታውቃለህን? ከሞት እንዲያድኑት ማርክስን ወይም ሌኒንን የተማፀነ ሰው ሊኖር ይችላልን? በማለት መለስኩለት ። እርሱ ግን ጮሌነት ያዘለ መልስ በመስጠት ሣቀብኝ ። እኔም ንግግሬን በመቀጠል – “በአንድ ድልድይ ላይ ድመት ስላለፈችበት ብቻ ለድልድዩ ጥንካሬ ማስረጃ ሊሆን አይችልም ። ሁሉም ነገር በተሟላበት ጊዜ እግዚአብሔር የለም ማለት ይችላል ፤ በችግር ጊዜ ግን ክህደት የሚያዋጣ

ሆኖ አልተገኘም ። ሌኒን ራሱ አስከፊ ሁኔታዎች በገጠሙት ጊዜ እንደፀለየ መጻሕፍትን ጠቅሼ ነገርኩት ።

እኛ በያዝነው እምነት እርካታን አግኝተንበታል ። ኮሚኒስቶች ግን ባለማቋረጥ እግዚአብሔር የለም የሚል ዘመቻቸውን ተያይዘውታል ። እረፍት – የለሾችና ቅብጥብጦች ናቸው ። ይህም ቅዱስ አውጉስጢኖስ የተባለ የቤተ ክርስቲያን አባት – "ጌታ ሆይ ፡ – ለራስህ ፈጥረኸናል ፡ በአንተ እርፍትን እስከታገኝ ድረስ ልባችንም ምንኛ የተቅበዘበዘ ነው" በማለት የተናገረውን ያስታውሰኛል ።

ኮሚኒስቶች ሊድኑ ይችላሉ ፤

ኮሚኒስቶችን በወንጌል ቃል መለወጥ ማለት – የዓለምን ገጽታ መለወጥ ማለት ነው ። ኮሚኒስታዊ ትምህርት ከሰው ባሕርይ ጋር የሚሄድ አይደለም ። ኮሚኒስቶች ሰው ከተለያዩ ኬሚካሎች የተገነባ ቁስ–አካላዊ ፍጡር ነው በሞት ጊዜም ሕልውናው ያከትማል ይሉናል ። ስለ ዓላማቸው ብዙ ራሣቸውን የሰው ኮሚኒስቶች ግን እናውቃለን ። ታድያ ፡ ቁስ–አካላዊ ፍጡር ለዓላማው ራሱን መሰዋት ይችላል?

ናዚስቶች ብዙ ሰዎችን ይህ ነው በማይባል ጭካኔ ጨፍጭፈዋል ። በመጨረሻ ግን ብዙዎቹ የሰው ደም እያባነናቸው ከመኖር ይልቅ ሕይወታቸውን ማጥፋትን መርጠዋል ። አንዳንዶቹም ባደረጉት ግፍ ተፀጽተው ንስሐ ገብተዋል ። ግፍና ጭከና ከሰው መሠረታዊ ነገሮች ጋር የሚሄዱ አይደሉም ። ኮሚኒስቶች ለሕይወት ትርጉምና ዓላማ ይፈልጋሉ፤ ይህን ደግሞ ኮሚኒዝም ሊያሟላላቸው አይችልም ። ኮሚኒዝም በጣም ጠባብ ነው ፡ ጥልቀት የለውም ። ለሕይወታቸው ትርጉም ወይም ዓላማ የሚሆናቸው ነገር ከአልክሆል ለማግኘት ይሞክራሉ ፤ ለጥቂት ጊዜ አልኮሆል ፋታ ይሰጣቸው ይሆናል ፤ እውነትን ቢያውቁ ኖሮ ለዘላለም ነፃ በሆኑ ነበር ።

ሩሲያኖች ዋና ከተማችንን ቡካሬስትን በተቆጣጠሩበት ዘመን ይህ ነው በማለት ልገልፀው በማልችለው ስሜት ተገፋፍቼ ወደ አንድ መጠጥ ቤት ገባሁ ። ባለቤቱም አብራኝ ነበረች ፣ ወደ ውስጥ ስገባ አንድ በጣም የሰከረ ሩሲያዊ ካፒቴን ሌላ ተጨማሪ መጠጥ እንዲሰጠው በያዘው ሽጉጥ አስተናጋጆችን እያስፈራራ ነበር ። ከመጠን በላይ ሰክሮ ስለነበር ግን ተጨማሪ መጠጥ ሊሰጡት አልፈለጉም ። ሰዎች ሁሉ በጣም ተደናግጠ

ዋል ። እኔም ወደ መጠጥ ቤቱ ባለቤት ሄድሁና ተጨማሪ መጠጥ ቢሰጠው ዝም እንደማሰኘው ነገርኩት — ከመጠጥ ቤቱ ባለቤት ጋር እንተዋወቅ ነበር ። የወይን ጠጅ በተደጋጋሚ ቀረበለት ፤ እፊታችን በነበሩት ሶስት ብርጭቆዎች ሙሉ ወይን ጠጅ እያከታተለ ጠጣ ፡ እኔ እና ባለቤቱ ግን አንጠጣም ። ምንም እንኳ ብዙ ቢጠጣም አእምሮው በትክክል በመሥራት ላይ ነበር ። ለዚያ አልኮሊስትነት ለተጠናወተው ሰው ስለ ክርስቶስ ነገርኩት እርሱም በተመስጦ ነበር የሚያዳምጠኝ ።

በመጨረሻም — "እስከአሁን ድረስ ስለማንነትህ ነገረኸኛል አሁን ደግሞ ስለማንነቴ ልንገርህ ፡ ስታሊን በአማኞች ላይ ከፍተኛ ስደት ባስነሣበት ወቅት እምነታቸውን ከካዱ ቀሣውስት አንዱ ነኝ ። ከአገር ወደ አገር እየተዘዋወርኩ "እግዚአብሔር የሚባል ነገር እንደሌለና በቅስናዩ ዘመን ሰዎችን ሣታልል እንደኖርሁ አስተምሬአለሁ ። እኔ አታላይ እንደነበርሁ ሁሉ ሌሎች ካህናትም አጭበርባሪዎች ናቸው በማለት ተናገርሁ ። ይህ አባባሌም የመንግሥት ባለሥልጣኖችን ደስ ስላሰኘ በሕዝብ ደኅንነት መሥሪያ ቤት ውስጥ እልቅና ተሰጠኝ ። በእነዚህ እጆቼ ብዙ ክርስቲያኖችን ካሰቃየሁ በኋላ ገድዬአለሁ ። ያደረግሁትን ግፍ ያስረሣኝ እንደሆነ በማለት መጠጥን አዘወተርሁ ። ሆኖም መጠጡም ቢሆን ሊረዳኝ አልቻለም ። ለበደሌ እግዚአብሔር እየቀጣኝ እንደሆነ አውቃለሁ" አለኝ ።

ብዙ ኮሚኒስቶች ራሣቸውን አጥፍተዋል። ኢሴኒን እና ማያኮቭስ ኪን የመሳሰሉ ታላላቅ ባለቅኔዎች በገዛ እጃቸው ነበር ሕይወታቸውን ያጠፉት ። ፌዴቭ የተባለ ተደናቂ ዐሐፊም ሕይወቱን አጥፍቶአል ። "ደስታ" በሚል ርዕስ ባዘጋጀው መጽሐፍ (ኖቭል) ደስታ የሚገኘው ለኮሚኒዝም ጠንክሮ በመሥራትና ኮሚኒዝምን በማስፋፋት እንደሆነ ገልጾ ነበር ፡ መጽሐፉን ከጨረሰ በኋላ ግን በገዛ ሽጉጡ ራሱን አጠፋ ። ነፍሱ ያን የሚያህል ውሸት መቋቋም አልቻለችም ። ጋፍኒን እና ቶምኪን የተባሉ በዛር ዘመን ለኮሚኒዝም ልዕልና የታገሉ ኮሚኒስት መሪዎች ከብዙ የትግል ዓመታት በኋላ ዓላማቸው ግቡን ቢመታም የኮሚኒዝምን እውነተኛ ገጽታ ግን መታገስ አልቻሉም ። ሁለቱም ራሣቸውን ገድለዋል።

ተራ ኮሚኒስቶችም ሆኑ አምባገነን መሪዎቻቸው ደስታ የሌለበት ሕይወትን ነው የሚመሩት ። ስታሊን ደስታ የሌለው ሰው ነበር የቅርብ

ጓዶችን ጨምሮ ብዙ ሕዝብ ጨፍጭፎአል ። ሰዎች መርዝ አብልተው ይገድሉኛል ወይም ደግሞ አንድ ቀን ራሴን አጠፋ ይሆናል በሚል ስጋት ነበር የኖረው ። እንደ ባንክ ካዝና በጥንቃቄ የሚጠበቁ ስምንት መኝታ ክፍሎች ነበሩ ። የትኛው ክፍል ውስጥ እንደተኛ እንዳይታወቅ ልዩ ጥንቃቄ ያደርግ ነበር ። ወጥ ቤቱ እፊቱ ምግቡን ሲቀምስ ካላየ በቀር አይበላም ። ኮሚኒዝም ማንንም ደስተኛ አያደርግም ። አምባገነን መሪዎቻቸው እንኳ ደስተኞች አይደሉም ። ክርስቶስ ያስፈልጋቸዋል ።

የኮሚኒዝም መፈራረስ ጥቅሙ የባርነት ቀንበሩን ለሚነባቸው ዜጐች ብቻ ሳይሆን ለራሳቸው የሥርዓቱ ተጠቃሚዎች ጭምር ነው ።

እኔ እስከማውቀው ድረስ በባርነት ጭቆና ሥር ያሉትን ሕዝቦች የልብ ትርታን የምታዳምጥና በዓለም አቀፍ ደረጃ ብሶታቸውን የምታሰ ማላቸው ይህቺ በኅቡዕ የወንጌልን እውነት የምታስፋፋው ቤተ ክርስቲ ያን ብቻ ናት ።

ይህች ቤተ ክርስቲያን ከሌሎች የምትለይበት ምክንያት ደግሞ የእምነት ጽናትዋና ትጋቷ ነው ።

ራሱን "ጆርጅ" በተሰኘ ድብቅ ስም ያቀረበ አንድ አገልጋይ ስለዚህች ቤተ ክርስቲያን የሚከተለውን አጋጣሚ ጽፎ ነበር።

አንድ ጊዜ በሐንጋሪ የነበረ ሩሲያዊ መኰንን ወደ አንድ አገልጋይ መጣና በግል ሊያናግረው እንደሚፈልግ ነገረው ፤ ወታደሩ ገና በአፍላ ወጣትነት የሚገኝ ሲሆን ፣ የአሸናፊነት የበላይነቱንም በግልጽ መረዳት ይቻል ነበር ። አገልጋዩም ወደ አንድ ክፍል ይዞት ገባ። ወጣቱ መኰንን ግድግዳው ላይ የነበረውን መስቀል እየና በቅሬታ ራሱን ነቀነቀ ።

"ይህ ሁሉ'ኮ ውሸት ነው" አለው ለአገልጋዩ ።

"አዎን ፣ እናንተ ቄሶች የሕዝቡ ንቃተ ሕሊና እንዳይዳብርና እድሚ ልኩን ለከበርቴዎች ተገዢ ሆኖ እንዲቀር የምትጠቀሙበት ውሸት ነው ። እንደምታየው እዚህ ያለነው እኔና አንተ ብቻ ነን ። እስቲ እውነቱን ንገረኝ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን በእርግጥ ታምናለህ?"

አገልጋዩ ግን ፈገግ እያለ—"የእኔ ልጅ ፣ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑንና ቅዱሳት መጻፍሕትም ስለ እርሱ የሚናገሩት ሁሉ እውነት እንደሆነ በፍጹም ልቤ ነው የማምነው" በማለት መለሰለት ።

"እንድታታልለኝ አልፈልግም ፤ እንድትስቅብኝም አልፈልግም ፤

ይልቅስ እውነቱን ንገረኝ" አለ ወጣቱ ከረር ባለ አነጋገር ። ሽጉጥ አውጥቶ አገልጋዩ ላይ ደቀነበትና ።— "የምታምነውና የምትሰብከው ሁሉ ውሸት መሆኑን ካልነገርከኝ የመጨረሻህ ይሆናል" በማለት ዛተበት ።

የእግዚአብሔር ሰው ግን— "እውነቱን ውሸት ነው ማለት አልችልም ፤ ጌታ በእርግጥ የእግዚአብሔር ልጅ ነው" አለው ምንም የመደናገጥ ምልክት ሳያሳይ ።

መኮንኑ ሽጉጡን ከመለሰ በኋላ አገልጋዩን አቀፈው ፤ ዓይኖቹም እንባ አቅርረው ነበር— "አዎን፡ እውነት ነው! እውነት ነው! እኔም እውነትነቱን አምናለሁ ፤ ይሁን እንጂ እኔ ራሴ በሕይወቴ እስካረጋግጠው ድረስ ሰዎች ለዚህ እውነት ለሙሞት እንኳ የመዘጋጀታቸው ሚስጢር ሙሉ በሙሉ ሊገባኝ አልቻለም" አለ ።

ይህን የመሳሰሉ ብዙ ታሪኮችን ማቅረብ ይቻላል ። ሩሲያዎች ሩማንያ በተቆጣጠሩበት ዘመን ሁለት ወታደሮች መሣሪያቸውን እንደ ያዙ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ገቡ ። እግዚአብሔርን ለማምለክ ተሰብስበው የነበሩትም ክርስቲያኖች "እምነታችሁን አንቀበልም ፤ ይህን እምነት ለመተው የማትፈልጉትን አሁኑኑ እንረሽናችኋለን ፤ እምነታችሁን ለመተው ፈቃደኛ የሆናችሁ ግንበዚህ በኩል ተከማቹ! አሉዋቸው ። አንዳንዶቹ በታዘዙት መሠረት በስተቀኝ በኩል ተከማቹ ፡" ስለዚህም በሰላም ወደ ቤታች እንዲሄዱ ተነገራቸው እና ሄዱ ። የተቀሩት ግን ለእምነታቸው ለመሞት የወሰኑ ክርስቲያኖች ብቻ ነበሩ፤ ሁለቱ ወታደሮችም — "እኛ ራሳቸውን ክርስቲያኖች ነን ሕብረት ለማድረግ የምንፈልገውም ከወላዋዮችና መንታ አስተሳሰብ ካለቸው ጋር ሳይሆን እንደእናንተ ለሚያምኑበት እምነት ለመሞት ዝግጁ ከሆኑት ጋር ብቻ ነው" አሉዋቸው ጌታንም በአንድነት አመለኩ ።

በሀገሬ እነዚህን የመሳሰሉ ክርስቲያኖች ለወንጌል እየተዋጉ ነው። የሚዋጉት ለወንጌል ብቻ ሳይሆን ለነፃነትም ጭምር ነው ። ይህም ጽሁፍ የሚያቀርብላችሁ ተራና እዚህ ግባ የማይባል ሰው ነው። ይሁን እንጂ ድምፅ ለሌላቸው ድምፅ ነኝ ፤ አፋቸው ለተሸበበ ክርስቲያኖች አንደበት ነኝ ። በእነርሱ ስም ሆኜ እምነታችሁን አጥብቃችሁ እንድትይዙና ክርስትና በእንዴት አይነት አሣሣቢ ሁኔታ ላይ እንዳለ ላሳውቃችሁ

አፈልጋለሁ ። በእነርሱ ስም ሆኜ የእምነት ነፃነት በሌለባቸው አገሮች ሁሉ በተለያየ ስቃይ ያሉትን ክርስቲያኖች በፀሎት እንድታስቡዋቸው እለምናችኋለሁ ።

ኮሚኒስቶችን እናሸንፋቸዋለን ፤ የምናሸንፋቸውም በመጀመሪያ ደረጃ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር በመሆኑ ነው።

በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ፣ የወንጌል መልእክታችን የሰውን ልብ ጥልቅ ጥማትና ፍላጐት የሚነካ በመሆኑ ነው ።

በናዚዎች ዘመን እሥር ቤት የነበሩ ኮሚኒስቶች በመከራቸው ጊዜ ይፀልዩ እንደነበር አጫውተውኛል። የኮሚኒስት ባለሥልጣኖችም ለሞት በሚያጣጥሩበት ጊዜ— "ኢየሱስ—ኢየሱስ" በማለት የጌታን ስም ሲጠሩ ሰምቻለሁ ።

ሌላው የምናሸንፍበት ምክንያት ደግሞ ክቡርና ውድ የሆኑት ባሕላዊ ቅርሶች ደጋፊዎቻችን በመሆናቸው ነው ። ኮሚኒስቶች የዘመኑ ክርስቲያኖች ፀሐፊዎችን መፃፍሕት ያግዱ ይሆናል ። ይሁን እንጂ ፣ የቶልስቶይንና የዶስተየቨስኪን ሥራዎች ማጥፋት አይቻላቸውም ። ጽሑፎቻቸው ዛሬም ቢሆን የክርስቶስን ብርሃን የሚፈነጥቁ ናቸው ። ጐቴ በምሥራቅ ጀርመን ፣ ሴንክዊች ፣ በፖላንድ እና ሌሎችም ከጥንት ክርስቲያን ፀሐፊዎች ጥቂቶቹ ናቸው ። ሌላው ታላቅ ሩማንያዊ ፀሐፊ ደግሞ ሣዱቪያኑ ነው "የቅዱሳን ሕይወት" የተሰኘውን መጽሐፉን "የቅዱሳን ተረት" በሚል ርዕስ ኮሚኒስቶች እያተሙት ነው ። ይሁን እንጂ ፣ ምንም አይነት ርዕስ ቢሰጡትም በውስጡ የተጠቀሱት ቅዱሣን ሕይወት ዛሬም ቢሆን ለብዙዎች መንፈሳዊ እውነታን እያንፀባረቁ ናቸው።

ኮሚኒስቶች ከዓለም ኪነ—ጥበባት መድረክ ላይ የራፋኤልን ፣ የሚካኤል ኤንጀሎን ፣ የሊዮናርዶ ዳቬንቼን ቅርሶች ማጥፋት አይቻላቸውም ። ስዕሎቹና ቅርሶቹ ሳይቀሩ ስለ ክርስቶስ ይናገራሉ ።

ከኮሚኒስቶች ጋር ስለ ክርስቶስ ስነጋገር በልባቸው ያለው መንፈሳዊ ጥማትና ባዶነታቸው ቁልጭ ብሎ ይታየኛል ። ኮሚኒስቶች በክርክር አፍን ማስያዝ ችግራቸው ላይሆን ይችላል ። ይሁን እንጂ ለውስጣዊው ረሃብና ጥማቱ እርካታን ማግኘት አይችልም ። የሕሊናን ድምፅ ፀጥ ሊያሰኘው አይችልም ።

"እግዚአብሔር የለም" የሚል ሌክቸር ከማሰማታቸው በፊት የሚፀልዩ ማርክሲስት ፕሮፌሰሮችን በግሌ አውቃለሁ ። በሚስጢር ወንጌል ወደ ሚሰብክበት ሥፍራ የሚሄዱ ኮሚኒስት ባለሥልጣኖችንም አውቃለሁ ። በእምነታቸው ጠንካሮች ባለመሆናቸውም ይፀፀቱበታል ። ኮሚኒስቶችም እንደማንኛችንም ሰዎች መሆናቸውን እንዘንጋ ። ወንጌል ደጋግሞ ሲያሸንፍ ተመልክተናል ። ስለዚህም እንደምናሸንፍ እናውቃለን ። የአንድ ሰው እምነት ከጊዜ ወደ ጊዜ ያድጋል ፣ ይዳብራል ።

ክርስቶስ ኮሚኒስቶችንም ቢሆን ይወዳል ፤ በእርሱ ማመን የሚኖርባቸውም በዚህ ምክንያት ነው ። "ኢየሱስ ወንጌልን ለዓለም ሁሉ ስበኩ" አለ እንጂ "ከኮሚኒስት አገሮች በቀር ..." አላለም ። ወንጌል በኮሚኒስት አገሮች እንዲዳረስ ደግሞ የእናንተን ተሳትፎ እንፈልጋለን ። ለእግዚአብሔርና ለታላቁ ተልዕኮ ታማኝ ከሆንን በኮሚኒዝም ቀንበር ሥር ለሚማቅቁት ሰዎች ወንጌል ለማዳረስ እንነሳ ።

## ሦስት ጥምር ቡድኖችን ያቀፈች ቤተ ክርስቲያን

*የመጀመሪያዎቹ በኮሚኒስቶች የተባረሩ ፖስተሮች ፤*

በኮሚኒስት አገሮች ወንጌልን በኅቡዕ የምታስፋፋው ቤተ ክርስቲያን የሦሥት ወገኖች ጥምር ናት ። የመጀመሪያዎቹ በኮሚኒስት መሪዎች ግፊት ከአገልግሎታቸው የተባረሩ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ፖስተሮች ናቸው ። እነዚህ ወገኖች አስመስሎ መኖርን ባለመቀበላቸው ብዙ ዓመታት ታስረዋል ፤ ተሰቃይተዋል ። ምንም እንኳ ቀድሞ ሲያገለግሉባቸው የነበሩ ቤተ ክርስቲያኖች ኮሚኒስቶች "ታማኝ" አገልጋዮችን ቢያስቀምጡበትም እነዚህ ወገኖች ግን በኅቡዕ መንፈሳዊ ሥራ እየሠሩ ናቸው ።

ሁለተኛው ደግሞ ከተለያዩ ክርስቲያን ወገኖች የተውጣጡ ናቸው። በሩሲያ ወይም በቻይና መካከለኛና ፡ ለብ ያሉ ፡ ወይም አስመሳይ ክርስቲያኖችን ማግኘት አይቻልም ። ከፍተኛ መስዋዕትነትን ለመክፈል ዝግጁ ናቸው ። ምን ጊዜም ቢሆንስደት ክርስቲያኖችን እንደሚያበዛቸውና እንደሚያጠነክራቸው እርግጠኛ መሆን አለብን ። ለነፍሳት በመመስከርና ነፍሳትን ወደ ጌታ በማምጣት ረገድ በጣም ትጉ ናቸው ።

ሬድ ስታር የተሰኘ ወታደራዊ ጋዜጣ— "እነዚህ በክርስቶስ

የሚያመልኩ ክርስቲያኖች ማንኛውንም ሰው የእምነታቸው ተከታይ ለማድረግ በጣም ጉጉዎች ናቸው” በማለት መጻፉ ይታወሳል ። ክርስቲያኖች ከሕይወታቸው ምስክርነትና ከመልካም አኗኗራቸው የተነሣ የአካባቢው ሕዝብ ሁሉ ያከብራቸዋል ። ለምሳሌ አንዲት ሴት ከሕመምዋ የተነሣ ለልጆችዋ እንክብካቤ ማድረግ ቢሳናት ብዙ ጊዜ ይህን ኃላፊነት የሚወስዱ ክርስቲያኖች ናቸው ። አንድ ሰው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ለቤተሰቡ የሚያስፈልገውን ማሟላት ቢያቅተው ክርስቲያኖች የእርዳታ እጃቸውን ይዘረጉለታል። የሚናገሩትን በሕይወታቸው ስለሚያሳዩ ምስክርነታቸውን ሰዎች ሁሉ ይቀበሉላቸዋል ። አንድ ጊዜ የራሳቸው የኮሚኒስቶች ጋዜጣ ስለክርስቲያን ባለልኳንዳዎች ሲናገር “ከሚሰጡት ሥጋ መጠቅለያ ጋር መንፈሳዊ ጽሑፎችንም አብረው ያድላሉ” ብሏል ። ማተሚያ ቤት የሚሰሩ ክርስቲያኖች ደግሞ እዚያው በሚሠሩበት ማተሚያ ቤት በድብቅ እያደሩ ክርስቲያን ጽሑፎች ሲያትሙ ያድራሉ ። አንድ ጊዜ ደግሞ ሕፃናት “ለጊዜው ካልታወቀ ሥፍራ” መንፈሳዊ ጽሑፎችን እንደተቀበሉና እነዚያን መንፈሳዊ ጽሑፎች ደግሞ ሕፃናት በእጅ ጽሑፎቻቸው ካባዙ በኋላ እክፍላቸው ግድግዳ ላይ በሚሰቀሉት የአስተማሪዎቻቸው ኮቶች ወይም ካፖርቶች ኪስ ውስጥ እንደሚያስቀምጡ ተደርሶበታል ።

ሶስተኞቹ ደግሞ የመንግሥት ፈቃድ ባለው ቤተ ክርስቲያን ቢያገለግሉም እንኳ ፣ በዚያ አገልግሎት እርካታን ያጡ አገልጋዮችና ፓስተሮች ናቸው ። በብዙ ኮሚኒስት አገሮች የመንግሥት ፈቃድ ያላቸውና በኅቡዕ የሚሠሩት አብያተ ክርስቲያናት በሚስጢር አብረው ያገለግላሉ ። እነዚህ ፓስተሮች ከሚያገለግሉበት ቤተ ክርስቲያን ውጪ ስለክርስቶስ እንዲያስተምሩ አይፈቀድላቸውም ። የሕፃናት ወይም የወጣቶች ስብሰባ እንዲያደርጉ አይፈቀድላቸውም ። ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎችም ወደ ቤተ ክርስቲያን መምጣትን በጣም ነው የሚፈሩት ። ፓስተሮቹም ለታመሙ ምዕመናን እንኳ በየቤታቸው ተገኝተው መፀለይ አይፈቀድላቸውም ። ይህን በመሳሰሉ ኮሚኒስታዊ ሥርአትና ሕግ የተተበተቡ በመሆናቸው አምልኮአቸው ትርጉም የለሽ ነው ። ምንም እንኳ ከፍተኛ ችግርና ማሸሚጠዋ እንደሚጠበቅባቸው ቢያውቁም የሃይማኖት ነፃነታቸው እንዲከበርላቸው ጥያቄ ያቀርባሉ ። ለወጣቶችና

ለሕፃናት በሚሰጢር ወንጌልን ያስተምራሉ ። በየክርስቲያኑ ቤትና በሌላም አመቺ ሆኖ ባገኙት ስፍራ ወንጌልን ያስፋፋሉ ። ከውጪ ሲታዩ ለኮሚኒስቶች መመሪያ ታማኝ የሆኑ በመምሰልም ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ለተራበው ሕዝብ ከአገር ውጪ የሚመጡ መንፈሳዊ ጽሑፎችን ያሰራጫሉ ። ይህን የመሰለ አገልግሎት ያላቸው ሰዎች በቅርቡ ስለተደረ ሰባቸው ብዙዎቹ ታስረዋል ። ይሁን እንጂ ፣ ይህች ቤተ ክርስቲያን ኮሚኒዝም ሙሉ በሙሉ እስኪሸነፍ ድረስ በኅቡዕ ወንጌልን ማስፋፋቷን ትቀጥላለች።

ኮሚኒስት አገሮችን የጎበኙ አንዳንድ ክርስቲያን ፀሐፊዎች "የተለ ያዩ ኮሚኒስት አገሮች ጐብኝተናል ፤ ይሁን እንጂ ፣ አንድም እንኳ በኅቡዕ ወንጌልን የምታስፋፋ ቤተ ክርስቲያን አላየንም" ሲሉ ይሰማል ።

የመጀመሪያዎቹ አሥርተ ዓመታት ክርስቲያኖች ክርስቲያን መሆና ቸውን እንኳ አያውቁትም ነበር ። የምን ሃይማኖት ተከታዮች ናችሁ? በማለት ብንጠይቃቸው አይሁዳውያን ፣ እስራኤላውያን ፣ ወይም ደግሞ የኢየሱስ ተከታዮች መሆናቸውን ብቻ ነው የሚነግሩን ። "ክርስቲያን" የሚለውን ስም የተሰጣቸው በአንጾኪያ ከተማ ራሳቸው ክርስቲያን ባልሆኑ ሰዎች ነበር ።

በሉተር ተሃድሶ እንቅስቃሴ የተሳተፉ ሰዎች ሉተራውያን ነን ብለው አላሰቡም ነበር ። ሉተር ራሱም ቢሆን ተከታዮቹ "ሉተራውያን" ተብለው መጠራታቸውን በጥብቅ ነበር የሚቃወመው ።

"የኅቡዕ ቤተ ክርስቲያን" የሚለውን ስም የሰጡዋት ኮሚኒስቶቹ ወይም በኮሚኒስት አገሮች ያለውን የሃይማኖት ሁኔታ ምርምር ያደረጉ ምዕራባውያን ናቸው ። እነዚህ ወገኖች ራሳቸውን ክርስቲያን ነን በማለት ነው የሚያስተዋውቁት እንጂ "በኅቡዕ ወንጌልን የምታስፋፋ ቤተ ክርስቲያን አባላት ነን" ብለው አይደለም ።

አንድ ሰው ብዙ ዓመታት በምዕራብ አገሮች ቢዘዋወርም አንድም የሩሲያ ሰላጣ ወጥመድ መኖሩን ላይረዳ ይችላል ። ታድያ እንደዚያ ማለት የሩሲያ ሰላጣ ወጥመድ በምዕራብ አገሮች የለም ማለት ነው ወይ? እንዲህ በቀላሉ ከተገኘማ ምኑም ኅቡዕ ሆነው…! በሚቀጥለው ምዕራፍ ስለዚ ህች በኅቡዕ ወንጌልን ስለምታስፋፋው ቤተ ክርስቲያን የሶቪየት ዜና ብዙኃን ያስተላለፍውን አቀርባለሁ ።

# ምዕራፍ ስድስት

## ክርስትና ኮሚኒዝምን ሲያሸንፍ

እስከ አሁን ድረስ በሩሲያ ወታደሮች መካከልና በኮሚኒስት ሩማንያ ወንጌልን ለማስፋፋት ስላደረግነው ወይም አሁን እንኳ በማድረግ ላይ ስላለነው ጉዳይ ገልጬአለሁ ። ዛሬስ ቢሆንይህች በኅቡዕ ወንጌልን የምታስፋፋ ቤተ ክርስቲያን በሩሲያና በሌሎች ኮሚኒስት አገሮች ትኖር ይሆን··? ዛሬም እንደከዚህ ቀደሙ በኮሚኒስት አገሮች ወንጌልን ማስፋፋት ይቻል ይሆን···?

ኮሚኒዝም ከግማሽ ክፍለ ዘመን በላይ በዓለም ላይ ተንሰራፍቶአል። ይሁን እንጂ፣ የተቀዳጀው ድል የሽንፈት ድል ነው። እውነተኛው አሸናፊ ክርስትና እንጂ ኮሚኒዝም አይደለም። የራሳቸው ሕትመት እንኳ ከጊዜ ወደ ጊዜ የክርስትያኖች ቁጥር እያደገ መሆኑን ይመሰክራል። የክርስቲያኖች ቁጥር በማደጉ ኮሚኒስቶቹን እያሳሰባቸው ነው። ዛሬ የወንጌልን ተልዕኮ አገልግሎታችን በከፊልም ቢሆን በግልጽ እያካሄድን ነው። የኮሚኒስት ሕትመት ድርጅቶች ስለ ክርስትና መስፋፋት ያቀረቡትን ዘገባ ከሌሎቹ ምንጮች እንኳ አረጋግጠናል። በሚቀጥሉት ገጾች በጣም አስፈላጊ የሆኑትን ነጥቦች ብቻ አቀርባለሁ።

በኖቬምበር 7/1966 ሰሁሚ በሚባል ስፍራ ግልጽ የወንጌል ስብሰባ አድርገን ነበር። ከተለያዩ ከተሞች የመጡ ሰዎች በስብሰባው ላይ ተገኝተዋል። ብዙ ወጣቶች ጌታን ከመቀበላቸውም በላይ በጥቁር ባሕር ውስጥ የጥምቀትን ሥርአት ፈጽመዋል። መጽሐፍ ቅዱስ ወይም ሌሎች መንፈሳዊ መፃሕፍቶቻችንን ተነጥቀናል፤ አገልጋዮቻችንም በሥነ— መለኮታዊ ትምህርት የተካኑ አይደሉም ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ ያጠመቀው ከቀደምት ዲያቆናት አንዱ የነበረው ፊሊጶስም ከቴዎሎጂ ትምህርት ቤት የተመረቀ አልነበረም። ኢትዮጵያዊውና ፊሊጶስ አብረው ያሳለፉት ጊዜ ምናልባት ከአንድ ሰዓት አይበልጥም። የኢትዮጵያዊው ልብ በወንጌል ቃል በመነካቱ ግን "እነሆ እዚህ ውሃ አለ፣ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ነገር ምንድን ነው?" የሚል ጥያቄ አቀረበለት ፊሊጶስም—

"በሙሉ ልብህ ካመንህ መጠመቅ ትችላለህ" አለውና ወዲያውኑ አጠመቀው። (የሐዋ፡8፡36) እኛም አዲስ ወደ ጌታ የመጡትን አማኞች ያጠመቅነውም ይህንኑ ምሣሌ በማድረግ ነበር።

ኡቼትልስካያ ጋዜጣ (የመምሕራን መጽሔት) ደግሞ በአገስት 23—1966 ባወጣው እትሙ 'በኮሚኒስቶች በተሾሙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አንመራም' በማለት ሮስቶቭ በሚባል ስፍራ የባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን አባሎች የተቃውሞ ሰልፍ ማድረጋቸውን አመልክቷል።

ክርስቲያኖች ወንጌልን በአደባባይ የሚሰብኩት እንደ ሜይ ዴይ በመሳሰሉት (የወዛደር ቀን) የኮሚኒስት በዓላት ነው። ክርስቶስም የፈሪሳውያንን ግብዝነት ለማጋለጥ፣ በሰንበታትና በበዓላት ቀን የምሥራቹን ቃል ሰብኮአል፣ ታላላቅ ተአምራትንም አድርጎአል።

የወዛደር ቀን ኮሚኒስቶች በድምቀት የሚያከብሩት በዓል በመሆኑ፣ ክርስቲያኖችም እሥራትና ችግር እንደሚገጥማቸው ቢያውቁም እንደዚህ ዓይነቱን ቀን ወንጌልን ለመስበክ ይጠቀሙበታል።

ማንኛውም ሩሲያዊ አማኝ ወንጌላውያን አብያተ ክርስትያናት በኅቡዕ እያተሙ ስለሚያሠራጩት "ሴክሬት ማኒፌስቶ" ስለተሰኘው ጽሁፍ እንደሚያውቅ እርግጠኛ ነኝ። በዚህ ጽሁፍ ላይ ኩሉንዳ በሚባል ሰፈር ነዋሪ ስለነበረች ሐማራ ስለምትባል ሴት ተጽፎአል። ባለቤትዋ በእሥር ቤት እንደሞተ ተነገራት፣ ስለዚህም አራት ሕፃናትን ያለ አባት ማሳደግ ነበረባት። የባልዋን አስከሬን ስትመለከተው የእሥር ቤት ካቴና እጆቹ ላይ ያደረሱትን ጉዳት አስተዋለች፣ እጆቹ ጣቶቹና የውስጥ እግሮቹ ተቃጥለዋል፣ ሆዱን በስለት ተወግቶአል። ቀኝ እግሩ አብጦአል፣ ሁለት እግሮቹ ላይ የተደረገው ግርፋት ያስከተለው ቁስል በጉልህ ይታያል። በጠቅላላው ሰውነቱ በቁስል ተወርሮአል።

ይሁን እንጂ፣ እያንዳንዱ ክርስቲያን ይህ ዕጣ እንደሚጠብቀው ቢያውቅም፣ ወደ አንድ ሺህ አምስት መቶ የሚሆኑ ክርስቲያኖች በዚያች የሜይ ዴይ ቀን ሮስቶቭ አንዶን በሚባል አደባባይ ላይ ስለ ክርስቶስ እየመሰከሩ ነበር።

በዚህ ሰው የቀብር ሥነ ሥርዓት ላይ "ለእኔ ሕይወት ክርስቶስ ነው፣ ሞትም ጥቅሜ ነው፣ ሥጋን እንጂ ነፍስን መግደል የማይችሉትን አትፍሩአቸው"

"ከመሰዊያውም በታች ስለ እግዚአብሔር ቃል የሞቱትን ሰዎች አየሁ" የሚሉ በጉልህ የሚነበቡ ጽሁፎችን የያዙ ብዛት ያላቸው ክርስቲያኖች ተገኝተው ነበር።

የዚህ ሰው ሞት ክርስቲያኖችን የበለጠ አደፋፈራቸው። በዚያን ቀን በተደረገው ስብከት ወደ ሰማንያ የሚቆጠሩ ሰዎች ጌታን ሲቀበሉ፡ አብዛኞቹ ወጣቶች ነበሩ። ሃያ ሶስቱ ደግሞ የኮሚኒስት ወጣቶች ማኅበር አባላት ናቸው። ያመኑትንም ሰዎች ዶን በሚባለው ወንዝ በማጥመቅ ላይ እያሉ ወታደሮችን የያዙ ብዙ መኪናዎች ሲመጡ ታዩ፡ አማኞችን በወንዙ ዙሪያ ከበቡዋቸው፤ ሊያስርዋቸው ቢፈልጉም እንኳ አንድ ሺህ አምስት መቶ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎችን ማሰር እንደማይችሉ ሲያውቁት ተውት። ክርስቲያኖች ግን የዚያን ቀን አገልግሎት እስኪያከና ውኑ ድረስ እግዚአብሔር ጥበቃ እንዲያደርግላቸው ተንበርክከው ፀለዩ። ወንድሞች እና እህቶች የጥምቀቱን ሥርአት የሚፈጽሙትን ወገኖች ፖሊሶች እንዳያስሩዋቸው ለመከላከል ትከሻ ለትከሻ ተያያዙና ከበቡዋ ቸው።

አንድ የኮሚኒስት መምሕራን ጋዜጣ ስለ ሁኔታው ሲጽፍ "ሕገ ወጥ ባፕቲስቶች በኅቡዕ ጽሁፎችን ያትማሉ፤ ለወጣቶችም ሃይማኖትን ያስፋፋሉ"። ብሏል ሩሲያውያን (ባፕቲስት የሚሉዋቸው ሌሎች የወንጌ ላውያን አብያተ ክርስቲያናትንና ጴንጤቆስጤዎችን ጨምሮ ነው) አንድ ቢኅቡዕ የሚታተም ክርስቲያናዊ ጽሁፍ "ሕይወት ጊዜያዊ እንጂ ዘላለማዊ አለመሆኑን እንዲረዱ ልጆቻችሁን የቀብር ሥርዓት ላይ እንዲገኙ አድርጉ" በማለት ለወላጆች ጽፎአል፡ በኮሚኒስት ትምህርት ቤት ሕፃናት የሚማሩት ስለ እግዚአብሔር አለመኖር ነው፤ ክርስቲያኖች ደግሞ እንዲህ ዓይነቱን መርዝ የሚያረክሱት መንፈሳዊ ትምህርት በማስተማር ነው።

ይኸው የኮሚኒስቱ መምህራን ጋዜጣ— "ልጆች በሃይማኖታዊ ትምህርት እንዲጠመዱ አንዳንድ መምሕራን ያደረጉት ተግባር በጣም የሚያሣዝን ነው" ብሏል። በዚያን ቀን የጥምቀት ሥርዓት ስለፈጸሙት ሰዎች ሲገልጽም— "ለምስክርነት የቀረቡት ወጣት ክርስቲያኖች ሥርዓት የለሾች ነበሩ፤ የኮሚኒስት ፍርድ ቤትን ተዳፍረዋል..." በማለት ጽፏል። የእምነት ነፃነት እንዲሰጥ የኅቡዕ አብያተ ክርስቲያናት አባላት

በኮሚኒስት ፖርቲው ዋና ጽህፈት ቤት ፊት ለፊት በየጊዜው ሰላማዊ ሰልፍ ቢያደርጉም ለዚህ የሚሰጣቸው ምላሽ ግርፋትና እሥራት ነበር።

"የባፕቲስት ሕብረት" የምትባለዋ ቤተ ክርስቲያን በኮሚኒስት ባለሥልጣኖች ቁጥጥር ሥር ስትሆን የምትመራው በአንድ እምነቱን በሸጠ ካሬቭ በሚባል ካህን ነው። ይህ ሰው በ1963ዓ.ም በወጣው ቁጥር 6 "ሶቪየት ላይፍ ቱዴይ" ላይ እጅግ ብዛት ያላቸውን ክርስቲያኖችንና ሌሎች ተቃዋሚዎቻቸውን የጨፈጨፉትን ኮሚኒስቶች ተግባር በማድነቅ ጽፎ ነበር። እውነተኞቹ አማኞች ግን ለዚህ ከሃዲ ያቀረቡት ተቋውሞ በድብቅ ወደ ምዕራቡ ዓለም ወጥቶ ለመነበብ በቅቷል።

አንድ ጊዜ ደግሞ በሞስኮ ከተማ ታላቅ ሰላማዊ ሰልፍ ተካሂዶ ነበር፤ ስለዚህም ጉዳይ የሚያመለክተውን ከዚያው ከሞስኮ የደረሰንን ደብዳቤ እንደሚከተለው ተርጉሜዋለሁ።

"የተወደዳችሁ ወንድሞችና እህቶች ከእግዚአብሔር አብ እና ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ፀጋ ይብዛላችሁ"።

"ሜይ 16፣1966 ወደ አምስት መቶ የሚቆጠሩ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ተወካዮች የእምነት ነፃነትን በተመለከተ ጉዳይ አቤቱታ ለማሰማት ሞስኮ በሚገኘው የኮሚኒስቶች ማዕከላዊ ኮሚቴ ጽ/ቤት በመሄድ ጥያቄአቸውን ለዋና ፀሐፊው ብሬዥኔቭ አቅርበዋል"

ይህ ኮሚኒዝምን በመቃወም በሞስኮ ከተማ የተደረገ የመጀመሪያ ሰላማዊ ሰልፍ ነው። እነዚህ አምስት መቶ ክርስቲያኖች የአቤቱታቸውን ምላሽ እስኪያገኙ ድረስ ሙሉ ቀን በጽሕፈት ቤቱ ፊት ለፊት መዋል ብቻ ሳይሆን ሌሊቱንም እዚያው ማደር ነበረባቸው። በመኪና የሚያልፉ ሰዎች ይሰድቡዋቸዋል፤ ቆሻሻ ይጥሉባቸዋል፤ ዝናብ እየዘነበ ቢሆንም እስከሚቀጥለው ማለዳ ድረስ ከነበሩበት ንቅንቅ አላሉም።

በሚቀጥለው ማለዳ ወደፅሕፈት ቤቱ ግቢ እንዲገቡና አንዳንድ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ባለሥልጣኖች እንዲያናግሩ ተፈቀደላቸው። ክርስቲያኖቹ በዚህ ሁኔታ ወደ ግቢው ከገቡ በኋላ የተደበደቡ አማኞችን ያውቁ ስለነበር ራሣቸው ብሬዥኔቭ ወጥተው እንዲያናግሩዋቸው አቤቱታቸውን ቀጠሉ።

ቀትር ላይ ያልታሰበ ሁኔታ ተፈጠረ። ሃያ ስምንት ትልልቅ አውቶቡሶች መጡ። በወንድሞችም ላይ ብቀላ ተጀመረ። "እጅ ለእጅ

ቀያይዘን—"የሕይወታችን ታላቁ ቀን መስቀሉን የተሸከምንበት ዕለት ነው" የሚለውን መዝሙር መዘመር ጀመርን። ወጣት፡ ሽማግሌ ሳይለዩ ወታደሮቹ ይደበድቡን ያዙ። ዓይን ጥርስ ወይም አፍንጫን ሳይመርጡ ሕሊናችንን ስተን እስክንወድቅ ድረስ ደበደቡን፡ በዚህ ሁኔታ ካጎሳቆሉን በኋላ በአውቶቡሶቹ ሞልተው ወዳልታወቀ ስፍራ ይዘውን ሄዱ።

ከታጨቁበት አውቶቡሶች የሚወጣውም የወንድሞችና እህቶች ዝማሬ ግን በየአደባባዩ ሁሉ ተሰማ። ይህ ሁሉ የተደረገው ብዙ ሕዝብ በታዛቢነት እየተመለከተ ነበር።

ይሁን እንጂ፡ ትግሉ በዚህ አላበቃም። መጥመቁ ዮሐንስ ከታሠረ በኋላ በዚያው ስፍራ እየሱስ በየአደባባዩ ወንጌልን መስበክ እንደጀመረ ሁሉ እነዚያ አምስት መቶ ክርስቲያኖች ከታሠሩ በኋላ እንኳ እንደ ጆርጅ ቪን እና ሆሬብን የመሳሰሉ እውነተኛ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በድፍረት ወደ ማዕከላዊው ኮሚኒስት ፓርቲ ጽህፈት ቤት በመሄድ አቤቱታቸውን ማሰማት ጀመሩ። የመጥምቁ ዮሐንስ ወንጀል— "የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ" ብሎ መስበኩ ነበር። እርሱ ቢታሠርም እየሱስ በስፍራው ተተክቶ የመጥምቁ ዮሐንስን ስብከት ማወጅ ጀመረ።

በጌታ ወንድማችን ቪን እና ሆሬብ የታሠሩት ምዕመናንን የት እንዳደረሷቸው እና በአስቸኳይ እንዲፈቱ የኮሚኒስት ፓርቲውን መወትወት ያዙ። ወዲያውኑ እነርሱ ራሳቸው እንኳ የት እንደገቡ ሳይታወቅ ጠፉ። በኋላ ግን ሎስቶርቭስኪያ በሚባል ወህኒ እየማቀቁ እንደሆኑ ተሰማ።

ታድያ፡ በዚህ ሁሉ ክርስቲያኖች የፈሩ ይመስላችኋል? በፍጹም! ሌሎች በስፍራቸው ተተክተው በኅቡዕ በሚታተሙ ጽሁፎች ክርስቲያኑን ሕብረተሰብ ማጽናናትና አይዞአችሁ ማለቱን ተያያዙት። በተሰራጩት ጹሁፎች የሚከተሉት የቅዱሳት መፃሕፍት ቃሎች ነበሩባቸው፡— "ክርስቶስን የማገልገል ዕድል የተሰጣችሁም—በእርሱ በማመናችሁ ብቻ ሳይሆን በእርሱ ምክንያት መከራ በመቀበላችሁ ጭምር ነው" ፊልጲስዩስ 1፡29 "በዚህ መከራ ማንም እንዳይናወጥ ለዚህ እንደተመረጥን ራሳችሁ ታውቃላችሁና"(ተሰሎንቄ 3፡3)"የእምነታችን አመንጪና ጀማሪ ፈጻሚ የሆነው እየሱስ—ወደፊት በሚያገኘው ደስታ

ምንያት በመስቀል ላይ የመሞትን ውርደት ከምንም ሳይቆጥር የመስ ቀል መከራና ሞት ታገሠ፤ በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝም ተቀመጠ።" (ዕብራውያን 12፡2)

ክርስቲያኖች በሮስቦቭ፣ በሞስኮና በመላው ሩሲያ፣ መንግሥት እግዚአብሔር የለም የሚል ትምህርትን በማስተማር የወጣቱን አእምሮ መመረዙን እንዲያቆም ተቃውሞአቸውን አሰሙ። በጽሁፍ ያሰፈሩትን ተቃውሞ አክቶበር 4፡1966 የወጣው ፕራቭዳ አኩሪያኒ "በዘመናችን ሰይጣናዊ ትምህረት እየተስፋፋ ነው ቤተክርስቲያንም የኮሚኒስቱ ሥርአት የሚያስጠው ውሣኔ ከእግዚአብሔር ትዕዛዝ የሚቃረን ቢሆንም ቤተክርስቲያን ግን አሜን በማለት እየተቀበለች ነው" በማለት ጽፎ ነበር።

ፕራቭዳ ቦስቶካ ደግሞ ከአሜሪካ የሚተላለፍ የወንጌል መልእክት እንዲያዳምጡ ሰዎችን በቡድን አደራጅታችኋል በመባል በአሌክሲ ኒቨሮቭ—ሰቦሪስ ጋርማሽቭ እና አክሲን ዙቮቫ ላይ ስለተካሄደው ምር መራ ጽፎ ነበር። እነዚህ ሰዎች የወንጌል መልእክትን ቴፕ ቀድተው ለአድማጭ አከፋፍለዋል። "የሸርሸር ቡድን" በሚል ሽፋን ሰዎችን በማሰባሰብ ሃይማኖት አስተምራችኋል በመባል ነበር የተከሰሱት፣ የጥንት ክርስቲያኖች ካታኮምቡ በሚባል የመቃብር ስፍራ እንኳ ሣይቀር ወንጌልን እንዳስፋፉ ሁሉ፣ እነዚህም ወገኖች ክህደት በሰፈነበትና ኮሚኒስታዊ ሥርአት በተስፋፋበት አገር ባገኙት፣ አጋጣሚ ሁሉ የምሥራቹን ቃል ያስፋፋሉ።

ሴፕቴምበር 15/1966 የወጣው ሶቭ የትስከያ ልጃቫ ደግሞ ምንም እንኳ በሕግ የተፈቀደ ባይሆንም ክርስቲያናዊ ጽሁፎችን በማተም ለሕዝብ እያዳረሱ እንደሆነ በማማረር ጽፎ ነበር። ይኸው ጋዜጣ ጽሁፉን በመቀጠል ሬንቲ ከሚባል ስፍራ ወደ ቼስያኑ ይመጣ በነበረ ባቡር ውስጥ ሶስት ወጣት ወንዶችና አራት ልጃገረድ ክርስቲያኖች "የወጣትነት ጊዜያችንን ለክርስቶስ እናቅርብ" በማለት ይዘምሩ እንደነበር አመልክ ቷል። ጋዜጠኛው የክርስቲያኖች እንቅስቃሴ ምን ያህል እንዳበሸቀው ሲገልጽ— "በአደባባዮች፣ በባቡርና በአውቶቡስ ጣቢያዎች፣ በታክሲዎ ችና በመንግሥታዊ ድርጅቶች እንኳ ሣይቀር እየሰበኩ ነው ይህ ደግሞ ያናድደኛል" ብሏል ይህ የሚያመለክተን ቤተ ክርስቲያን ምን ያህል

በመንቀሳቀስ ላይ እንደሆነችና የወንጌልም መስፋፋት ምን ያህል ለኮሚኒስቶች ራስ ምታት እንደሆነባቸው ነው።

በአደባባይ ዘምራችኋል ተብለው የቀረቡት ክርስቲያኖች የተላለፈውን ክስ ሲሰሙ እዚያው ፍርድ ቤት ተንበርክከው ራሳቸውን ለጌታ አደራ ሰጡ። "ጌታ ሆይ ለዚህ እምነት መከራ እንድንቀበል ፈቃድህ ስለሆነም እናመሰግንሃለን" በማለት እግዚአብሔርን አመሰገኑ። ስደቱና መከራው የክርስቲያኖችን እምነት ሊያዳክመው አልቻለም። እንዲያውም ይበልጥ እንዲጠናከሩና በቁጥርም እንዲበዙ ነው ያደረጋቸው።

ኦክቶበር 4/1966 ፕራቭዳ አከራኒ የሩሲያ ኅቡዕ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች አንዱ ስለሆነው ስለ ወንድማችን ፕሮኮፊቭ ሲጽፍ ሶስት ጊዜ ቢታሠርም እንኳ በድብቅ የሃይማኖት ስብሰባዎችን ከማድረግ አልተቆጠበም። አሁን ደግሞ እንደገና ታስሯል" ብሏል።

ወንድማችን ፕሮኮፊቭ ከመታሠሩ በፊት በአንድ በኅቡዕ በሚሠራጭ ክርስቲያናዊ ጽሁፍ— "መንግሥታዊ እውቅና ያላት ቤተ ክርስቲያን (ኦፊሻል ቸርች) ምንም እንኳ የኮሚኒስቶችን ወዳጅነት ብታተርፍም የእግዚአብሔርን በረከት ግን ማግኘት አልቻለችም" ብሎ ነበር። በኮሚኒስት አገር መታሠር ማለት መራብ ማለት ነው። መሠቃየት ማለት ነው። ሰብአዊ ክብርን ማጣት ማለት ነው።

በ1966 የወጣው "ሣይንስና ሃይማኖት" የተሰኘው ቁጥር 6 መጽሔት ደግሞ ክርስቲያኖች በረቀቀ ዘዴ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ያሠራጫሉ፣ ይህንንም የሚያደርጉት ሽፋኑ መንግሥታዊ መጽሔትን ወይም ጋዜጣን በሚመስል ውስጡ ግን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ባሉበት ጽሁፍ ነው። በማለት ወቅሷቸው ነበር። ፕራቭዳ ካዛክስታንካያ ደግሞ ጁን 30/1966 በወጣው እትም "በአደባባይ ይዘምራሉ የሚዘምሩት መዝሙር ግን ዜማው "ዓለም አቀፍ" በመባል የሚታወቀው የኮሚኒስቶች መዝሙር ቢሆንም ቃላቶቹ ግን ክርስቶስን የሚያወድሱ ናቸው። ብሎ ነበር፣ ካህናት፣ ጳጳሳትና ፈሪሣውያን እየሱስን ለጲላጦስ አሣልፈው እንደሰጡ ሁሉ የመንግሥት መጠቀሚያ የሆኑ የሃይማኖት መሪዎችም እውነተኛ ክርስቲያኖችን አሣልፎ ለኮሚኒስቶች በመስጠት የቤተ ክርስቲያንን ሕልውና እየተፈታተኑ ነው" ሲል አንድ የክርስቲያኖች ኅቡዕ ጽሁፍ አጋልጧል።

የክርስቶስ ሙሽራ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ዛሬም ቢሆን እያገለገ ለችው ነው! ይህም ራሣቸው ኮሚኒስቶቹ ሣይቀሩ የሚመሰክሩት ሐቅ ነው። ኮሚኒስቶችን ወደ እምነት ማምጣት ይቻላል።

አንድ ጊዜ ደግሞ ታኒያ ሲዮጎኑቫ የተባለች የወጣት ኮሚኒስት ሊግ አባል በአስደናቂ ሁኔታ በክርስቶስ አመነች። ባኪንስኪ ሮባቺ (የባኩ ሠራተኞች) የተሰኘው መጽሔት አፕሪል 27/1966 በወጣው እትሙ ላይ የደብዳቤውን ክፊል ጽሁፎች አውጥቶ ነበር እንደዚህ ይነበባል።

"ውድ አክስቴ ናዴያ—በጌታ በኢየሱስ ስም በረከቱ ይድረስሽ ጌታ ምን ያህል እንደሚወደኝ ልገልጽልሽ አልችልም! ማንኛችንም ብንሆን በእርሱ ፊት ኢምንት ነን፤ እየሱስ ክርስቶስ—"ጠላቶታችሁን ውደዱ የሚረግማቸችሁን መርቁ፣ ለሚጠሉዋችሁ መልካም አድርጉ ስማችሁ ንም ለሚያጠፉ ፀልዩ" ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ እንደሚገባሽ እርግጠኛ ነኝ"።

ይህ ደብዳቤ በኮሚኒስቶች እጅ ከገባ በኋላ ይህችን ክርስቲያን እህት ወደ ጌታ ያመጣት ፒተር ሴሬቤሬኒኮቭ የተባለው ወንድም ወህኒ እንዲወርድ ተፈረደበት። ይህ ወንድም "የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች እንዳደረጉት ሁሉ በአዳኛችን በክርስቶስ በሙሉ ልብ ማመን አለብን። የእኛ መመሪያ መጽሐፍ ቅዱስ ነው፣ ሌላ መመሪያ የለንም። ሰዎችን ከኀጢአት ስለሚያድነው አምላክ ለመናገር መፍጠን አለብን፣ በተለይም ደግሞ ለወጣቱ ስለ ክርስቶስ ልንነግረው ይገባል" በማለት መናገሩን የኮሚኒስቶቹ ጋዜጣ አስፍሮታል። "ታዲያ'ኮ" የኮሚኒዝም መመሪያ ለወጣቱ ሃይማኖት መስበክን በጥብቅ ይቃወማል" በማለት ለቀረበለት ጥያቄ የሰጠው መልስ "መመሪያችን መጽሐፍ ቅዱስ ነው" የሚል ነበር። አዎን፣ ክህደትና አምባ—ገነንነት ለሰፈነበት ሥርአት መስጠት የሚገ ባው ትክክለኛ መልስ ነው።

የኮሚኒስት ወጣቶች አባል የሆኑ ብዙ ወጣቶችና ልጃገረዶች በየጊዜው ክርስቲያን እየሆኑ እንደሆነ ከላይ የተጠቀሰው መጽሔት ጠቁሟል። "የኮሚኒስት ትምህርት መስጫ ማዕከሎች ምንኛ ደካሞች ናቸው። —እግዚአብሔርን የሚቃወመው ትምህርታቸው ብርሃን የለሽ ጨለማ ነው፣ ሕዝቡን ከዚህ ጨለማ ልናወጣው ይገባል።" ማለታቸው

ንም ለማስረጃነት አቅርቦታል። ክርስትና በኮሚኒስት ወጣቶች መካከል በአስደናቂ ፍጥነት እየተስፋፋ ነው።

ክርስቲያኖች ወንጌልን በመስበካቸው ብቻ እንደ ወንጀለኞች ተቆጥረው ፍርድ ቤት ሲቀርቡ ለኮሚኒስት ባለሥልጣኖች የሚሰጡዋቸው መልስ በጣም ያስደንቀኛል ። አንድ ጊዜ ዳኛው— "ለምንድነው ሕዝቡን ሁሉ ወደ እምነታችሁ የምትስቡት?" በማለት ለአንዲት ክርስቲያን እህት ላቀረበላት ጥያቄ የሰጠችው መልስ— "ዋናው ዓላማችን ሕዝብ በሙሉ በክርስቶስ እንዲያምን ማድረግ ነው" የሚል ነበር ።

"ሃይማኖታችሁ ፀረ–ሣይንስ ነው" አለ ዳኛው እፊቱ የቀረበችውን ልጃገረድ ። ለመሆኑ እርስዎ ከአልበርት አንስታይን ወይም ከኒውተን ይልቅ ስለ ሳይንስ ያውቃሉ? ሁለቱም ታላላቅ ሳይንቲስቶች ቢሆኑም አማኞች ነበሩ ፤ እንዲያውም አነስታይን— "የአይሁድ እምነት ነቢያት ባስተማሩት መሠረት ቢስተካከል ኖር ክርስትናም ኢየሱስ ባስተማረው መሠረት ከካህናቱ ወገና ሥርዓት ቢላቀቅ ኖሮ ዓለማችንን ካለበት ችግርና ጣጣ የሚታደግ ሃይማኖት ይኖረን ነበር ፤ እንዲህ አይነቱ ሃይማኖት እንዲስፋፋ ማድረግ ደግሞ ከእያንዳንዱ ሰው የሚጠበቅ የተቀደሰ ተግባር ነው" በማለት ጽፎአል ይህ ያለንበት ዓለም (ዩኒቨርስ) "የአነስታይን ዩኒቨርስ" እንደሚባል በሁለተኛ ደረጃ በነበርኩበት ጊዜ መማሬን አስታውሳለሁ ። ታላቁ ሩሲያዊ ሳይኮሎጂስት ፓቭሎቭ ክርስቲያን እንደነበር ዘነጉት..? ካርል ማርክስ እንኳ ዳስ ካፒታል ለተሰኘ ሥራው በጻፈው መቅድም ላይ "ክርስትና — በተለይም የፕሮቴስታንቱ አይነት ክርስትና በኃጢአት ምክንያት ለተበላሸው የሰው ልጅ ባሕርይ ፍቱን መፍትሔ ነው" በማለት ጽፎአል ። እኔ በበኩሌ በኃጢአት የተበከለ ባሕርይ ያለኝ ሰው ነኝ" ብሏል ። ባሕርዩን ለማደስ ክርስቲያን ሆንሽ ብለው ይወነጅሉኛል ዳኛውም ምንም መልስ አልሰጠም ። ግን ምላሽ አጥቶ እንጂ ወዶ አልነበረም ።

ሌላ ወጣት ደግሞ "የምትከተለው ሃይማኖት ከሳይንስ ጋር አይስማማም" በማለት ለቀረበለት ተቃውሞ— "የተከበሩ ዳኛ ምን ያህል በሳይንስ የመጠቁ ቢሆኑም ፣ ክሎሮፎርምንና ሌሎች መድኃኒቶችን ካዘጋጀው ከሲምፕሰን ይበልጥ ሳይንቲስት መሆን የሚችሉ አይመስለኝም ፤ አንድ ጊዜ ለሲምፕሰን "እስከ አሁን ከተረዳኸው ነገር ሁሉ

የሚበልጠው የትኛው ነው ..?" የሚል ጥያቄ ቀርቦለት ነበር። እርሱ ግን— "ከተረዳሁት ነገር ሁሉ የሚበልጠው ኃጢአተኛ መሆኔንና የምድነውም በእግዚአብሔር ፀጋ ብቻ መሆኑን መገንዘቤን ነው" የሚል መልስ ነበር የሰጠው ።

ጃንዋሪ 15,1966 የወጣው ፕራቫዳ ቮስቶካ ለአንዲት ወጣት "ለመሆኑ ወደዚህ እምነት ያመጣሽ ማነው?" በማለት ለቀረበላት ጥያቄ — "ወደጉባኤው ያመጣኝ እግዚአብሔር ራሱ ነው" በማልት እንደተናገረችና መሪያችሁ ማነው? ለሚለው ጥያቄ ደግሞ ሌላዋ ወጣት "የሰው መሪ የለንም" ማለቷን አስፍሮ ነበር፤ ይህን የሚያደርጉት ሌሎችን ለእስራት አሳልፎ ላለመስጠት ነበር ።

ጃንዋሪ 30,1964 የወጣው ኡቼልስካያ ጋዜጣ ደግሞ ቬሬኖን በሚባል ስፍራ እግዚአብሔር የለም የሚል ሌክቸር ያሰማ የነበረውን ሰው ክርስቲያኖች እንደተቃወሙትና "መቼም በተግባር ባታውላቸውም እንኳ" "አትስረቅ" "አትግደል" የሚሉትን ሞራላዊ ሃሣቦችን እንደም ትቀበል እርግጠኞች ነን ፣ ታዲያ እግዚአብሔር ከሌለ እነዚህን ሞራላዊ መመሪያዎች ከየት አገኘሃቸው?" የሚል ጥያቄ እንደገጠመው አስፍሮ ነበር ።

በኮምኒስት አገሮች ማንኛውም አማኝ ተጽእኖ ቢደረግበትም የኮሚኒስቶች ስደት መረብ የሚያነጣጥረው ግን ወንጌልን በኅቡዕ በሚያስፋፉት እውነተኞቹ ክርስቲያኖች ላይ ነው። ብዙ ክርስቲያኖች ስብሰባ ሲያደርጉ ታፍሰው መታሰራቸውን የራሳቸው ዜና ብዙኃን በየጊዜው ያውጃል። በአንድ ስፍራ አእምሮአችሁ ጤነኛ አይደለም ተብለው ሰማንያ ሁለት ክርስቲያኖች እብዶች ሐኪም ቤት እንዲገቡ ሲደረግ—ከጥቂት ቀናት በኋላ ሃያ አራቱ ሞተዋል ። እንዴት እንደሞቱ ለቀረበው ጥያቄ ደግሞ "በፀሎት ብዛት" የሚል መልስ ነበር የተሰጠው ። ለመሆኑ ፀሎት ማንን እንደገደለ ነው እነዚያን ክርስቲያኖች የገደላቸው? ማን እንደገደላቸው ግን መገመት አያዳግትም።

በአንዳንድ አካባቢ ደግሞ ወላጆች ለሕፃናት መንፈሳዊ ትምህርት ሲያስተምሩ ስለተገኙ ልጆቻቸው በመንግሥት ተወስደውባቸዋል ። ልጆቻቸውን እንደገና እንዲያሳድጉ ወይም እንዲጎበኙ እንኳ አልተፈቀደላቸውም ። ይህ ደግሞ በጣም ልብን የሚሰብር ኀዘን ነው ። ይህን ሁሉ

የምታደርገው ኮሚኒስትዋ ሶቪየት ዩኒየን "ማንም ወላጅ ሃይማኖታዊም ሆነ ያመነበትን ሞራላዊ መመሪያ ለልጁ የማስተላለፍ ወይም የማስተማር መብቱ የተጠበቀ ነው" የሚለውን አዋጅ ፈርማ ተቀብላለች ። ለኮሚኒስ ቶች ያደረውና የባፕቲስት ዩኒየን ቤተ ክርስቲያን መሪ የነበረው ካሬቭ "ሶቭየት ሕብረት የሰው ልጅን ሰብአዊ መብት ታከብራለች" በማለት ሲጽፍ ትንሽ እንኳ እፍረት አልተሰማውም ። ይህን የሚቀበሉት ሞኞች ናቸው ።

ጁን 4,1963 የወጣው ሶውጀስካያ ሩሲያ የተባለ መጽሔት አንዲት የስድስት ልጆች እናት ሕፃናቶችዋን ክርስትና በማስተማርዋና የኮሚኒ ስት ሕፃናት መለያ የሆነውን ክራባት እንዳያደርጉ በመከልከልዋ ስድስቱም ልጆችዋ እንደተወሰዱባት ጽፎአል ። ልጆቿን ሲነጥቋት— "ይህ ሁሉ የደረሰበኝ በእምነቴ ምክንያት ነው" በማለት ነበር የተናገረ ችው ። በጣም የሚገርመው ለልጆቹ የሚያስፈልገውን ማንኛውንም ወጪ እንድትሸፍን መደረጓ ነው ። በአሁኑ ጊዜ ጨቅላ አእምሮአቸው በክህደት ትምህርት ተመርዞ ይሆናል ። ክርስቲያን እናቶች እስቲ ይህች ሴት ምን ሊሰማት እንደሚችል ገምቱት ።

ሐዋርያው ጳውሎስ "እግዚአብሔርን ለሚወዱ እንደ ሃሣቡም ለተጠሩ ነገር ሁሉ ለበጐ ይደረግላቸዋል" ይላል አንዳንድ ጊዜ በዚህ ሁኔታ ከወላጆቻቸው የተነጠቁ — ሕፃናት በኮሚኒስቶች ትምህርት አእምሮአቸው ሣይበከል ካደጉ በኋላ ከወላጆቻቸው ጋር ይገናኛሉ ።

መጽሐፍ ቅዱስ ማንም ከኢየሱስ ይበልጥ ልጁን የሚወድድ ተከታዩ ሊሆን እንደማይችል ይናገራል ። እነዚህ ቃላት ይበልጥ ትርጉም የሚኖራቸው ግን በኮሚኒስት አገሮች ነው። እስቲ ከልጆቻችሁ ተለይታ ችሁ ለሳምንት ለመቆየት ሞክሩ ፤ ምናልባትም በሩሲያ ያሉ ወላጆች ችግር የሚገባችሁ ያን ጊዜ ብቻ ሊሆን ይችላል ። ሕፃናትን ከወላጆቻቸው ነጥቆ መውሰድ ዛሬም ቢሆን በሩሲያ የተለመደ ነው ማርች 29,1967 የወጣው ዝናሚያ ኢዮሮስቲ የተሰኘ መጽሔት በፈሪሃ እግዚአብሔር ስላሳደገችው ልጅዋ ስለተወሰደባት ሴት ጽፎአል ። በሀባሮቭክ ነዋሪ የሆነችው ዛባቪና የተባለችም ሴት ሃይማኖታዊ ሥነ ምግባር ስላስተማ ረች እንደ ወንጀል ተቆጥሮባት በማደጎነት የምታኖረው የሙት ልጅ ተወስዶባታል ይህንንም የሃይማኖታዊ ሥነ ምግባር ትምህርት —

"ጤናማ ያልሆነ ትምህርት" ብሎታል ። የኮሚኒስቶች ጋዜጣ (ሶቭየት ሰክያ ሮዚና ጃንዋሪ 13,1968 የወጣ እትም! ።

በኅቡዕ ወንጌልን ስለሚያስፋፉ ፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ብቻ መፃፉ ትክክል አይደለም። በሩሲያ ያሉ የኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች በጣም እየተለወጡ ነው። ብዛት ያላቸው የቤተ ክርስቲያናቱ መሪዎችና ምዕመናን ለእምነታቸው የተለያየ መከራ ተቀብለዋል። በእሥር ቤት ለአረጋውያን መቁጠሪያ ሊኖራቸው አይችልም ። የጌታን ስቅለት የሚያመለክት መስቀል ፣ የቅዱሳን ምስል ፣ እጣን ወይም ጧፍ ሊኖራቸው አይችልም ፤ ካህናቱ ልብስ ተክህኖ የላቸውም ፤ ለቅዱሳን ቁርባን የሚጠቀሙበት ያማረ የስንዴ ሕብስት ወይም ወይን ፣ ወይም የፀሎት መጻሕፍት የላቸውም ። ምንም እንኳ እነዚህ ነገሮች ሁሉ ባይኖሯቸውም በቀጥታ ወደ አምላካቸው ፊት በፀሎት ይቀርባሉ ። እግዚአብሔርም መንፈሱን እያፈሰሰላቸው ነው ።በሩሲያ ባሉ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ታላላቅ ሰማዕታት ተገኝተዋል ።ለመሆኑ በዕድሜ የገፉት ጳጳስ የሮሞጊን የት እንደደረሱ የሚያውቅ ማነው? እኚህ የእግዚአብሔር ሰው ቤተ ክርስቲያን ከከሃዲዎቹ ኮሚኒስቶች ጋር የምታደርገውን ጤናማ ያልሆነ ግንኙነት በድፍረት ተቃውመዋል ።

ኮሚኒዝም ከሃምሣ ዓመት በላይ ተንሰራፍቷል። ይሁን እንጂ በኅቡዕ ወንጌልን የምታስፋፋው እውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን ስለ ተቀዳጀችው ድል የራሣቸው ዜና ብዙኀን እንኳ በግልጽም ይሁን በተዘዋዋሪ እየመሰከሩ ነው። በእርግጥ ክርስቲያኖች በተለያየ መከራ አልፈዋል፤ ይሁን እንጂ፣ ይበልጥ ለእምነታቸው ታማኞች ሆነዋል፣ ይበልጥ እያደጉና እየተስፋፉ ነው።

በሩማንያ ያለነው ለወራሪዎቹ የሩሲያ ሠራዊት የወንጌልን ዘር ዘራን፣ በሩሲያና በሌሎችም ሩሲያ በወረረቻቸው አገሮች ያሉ ክርስቲያኖችም ለወራሪው ጦር የወንጌልን ዘር ዘሩ። የተዘራው ዘር ፍሬ እየሰጠ ነው፣ እንደማንኛችንም ሁሉ ክርስቲያኖች መሆን ይችላሉ ጨቋኙም ሆኑ ተጨቋኙ ክርስቶስን በልባቸው ውስጥ ማንገሥ ይችላሉ እኛ ግን የሚቻለንን አድርገናል።

በሶቭየት ሕብረት በቻይናና በሌሎችም ኮሚኒስት አገሮች ወንጌል እንደ ሰደድ እሣት መስፋፋቱ ለዚህ እውነት ማስረጃ ሊሆነን ይችላል።

ክርስቲያኖች በእሥር ቢማቀቁም እንኳ ምን ያህል የእምነት ጽናት እንዳላቸው ለማሣየት የሚከተሉትን ከእሥር ቤት የተላኩ ደብዳቤዎችን አቅርበናል። ቀጥሎ የምታነቡት ቫሪያ የምትባለውን እህት ወደ ጌታ ያመጣች ማርያ የምትባል ልጃገረድ የፃፈችው ደብዳቤ ነው።

## አንደኛ ደብዳቤ፡

....ዛሬም ቢሆን እዚሁ ነኝ። ሰዎች ሁሉ በተለይም፡ አንዳንድ የወጣት ኮሚኒስት አባሎች በጣም ነው የሚወዱኝ። አንዳንዶች በጣም ይጠሉኛል፡ እኔ ግን የሚወዱኝንም የሚጠሉኝንም እኩል እወዳለሁ። ታዲያ ይህን ሁሉ ትታዘብ የነበረች አንዲት የወጣት ኮሚኒስት አባል የሆነች ልጃገረድ—"በጣም የምትገርሚ ሰው ነሽ እንደማየው ብዙዎች ቢሰድቡሽና ቢያንጓጥጡሽም፡ አንቺ ግን ለሁሉም ፍቅርን ስታሣዪ እመለከታለሁ፡ ለምንድን ነው?" በማለት ጠየቀችኝ። እኔም ጌታ እየሱስ ክርስቶስ ወዳጆቻችንን ብቻ ሣይሆን ጠላቶቻችንንም እንድንወድ አዞናል" አልኳት። ይህች ልጅ ከዚህ ቀደም ብዙ አሣዝናኛለች፡ ብዙ ጎድታኛለች፤ እኔ ግን ሽክም ተሰምቶኝ እየፀለይኩላት ነበር።

ታድያ አንድ ቀን ወደ እኔ መጥታ—"ሌሎችን ስትወጂ እኔንስ ትወጂኛለሽ?" ብትለኝ ተቃቅፈን ተላቀስን። እንደምወዳትም ነገርኳት። ዛሬ አብረን እንፀልያለን። ወደ ጌታ እንድትመጣ ፀልይላት ስምዋ ቫርያ ይባላል።

አንዳንዶቹ አፋቸውን ሞልተው "እግዚአብሔር የለም" በማለት ሲናገሩ ስንሰማ ከልባቸው ሊመስለን ይችላል፤ እውነቱ ግን እንዲህ አይደለም። በአንደበታቸው እግዚአብሔርን ቢሰድቡትም በልባቸው ውስጥ በቃል ሊገለጽ የማይቻል ጭንቀትና ሁከት አለባቸው... የልባቸውን ጭንቀትና መቃተት ያስታገሰላቸው እየመሰላቸው ነው በየአጋጣሚው "እግዚአብሔር የለም" የሚሉት።

በክርስቶስ እህትሽ ማሪያ

## ሁለተኛ ደብዳቤ

"ባለፈው ደብዳቤዬ ቫርያ ስለምትባል ልጃገረድ ጽፌልሽ ነበር። ደስ ይበልሽ ቫርያ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደግል አዳኝና ጌታ ተቀብላለች። ለጓደኞችዋ ሁሉ ስለ እምነትዋ እየተናገረች ነው፤ እግዚአብሔር የለም የሚለውን ኮሚኒስታዊ ትምህርት በማስፋፋት ያሳለፈችው ጊዜ ክፉኛ ይቆጫታል። ዛሬ ግን ላለፈው በደልዋ ካሣ እንዲሆን ያለ መታከት የጌታን ታላቅነትና አዳኝነት እየመሰከረች ነው።

እኔና ቫርያ አብረን ወደ አንድ የኮሚኒስቶች ስብሰባ ሄደን ነበር፤ ምንም እንኳ አንድም ቃል እንዳትናገር ብነግራትም፥ እርስዋ ግን በሕዝቡ ፊት ቆማ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደግል አዳኝዋ መቀበልዋን መሰከረች፤ እስከ አሁን ድረስ መንፈሳዊ ዓይኖቿ ታውረው ስለነበሩ ራስዋ ጠፍታ ብዙዎችንም በጥፋት መንገድ እንደመራችና አሁን ግን ለዚህ ሁሉ በደልዋ ይቅርታ እንዲያደርጉላት ጓደኞቿን ጠየቀቻቸው። በጉባኤው ለነበሩት ሁሉ የሃጢአትና የክህደትን መንገድ ትተው በእምነት ወደ ክርስቶስ እንዲመጡ በድፍረት ነገረቻቸው።

ማንም ያቋረጣት አልነበረም፤ ሁሉም በፀጥታ አዳመጧት። ንግግሯን ከጨረሰች በኋላም— "በክርስቶስና በመስቀሉ ኃይል አላፍርም" የሚለውን መዝሙር ልዩ ጣዕም ባለው ድምፅዋ አዜመችላቸው።

ከዚያ በኋላ·· ከዚያ በኋላ ግን ቫርያን ወሰዷት የት እንዳለች አናውቅም እግዚአብሔር ግን ባለችበት ቦታ ሊጠብቃት ኃይል አለው ፀልዩ።

ያንቺው ማሪያ

## ሶስተኛ ደብዳቤ

"ትናንት ጳጉሜ ሁለት ቀን ቫርያን እሥር ቤት አገኘኋት። ሳያት ልቤ በሃዘን ተሰበረ፤ በጣም ከስታለች፤ ገርጥታለች፤ በዕድሜዋም ሆነ በእምነትዋ ልጅ ብትሆንም፥ ማንኛውንም አይነት መስዋዕትነት ለመክፈል ቆርጣለች። ያለችበትን እሥር ቤት ካወቅን በኋላ አንዳንድ ነገሮችን እንልክላታለን፤ ግን የሚደርሣት በጣም ጥቂቱ ነው።

እንደነገርኩሽ ሰውነትዋ ተጎሳቁሏል፤ ይሁን እንጂ ምድራዊ

ያልሆኑ ሰላምና ደስታ ከአይኖችዋ ይንፀባረቃሉ። ይህንን ግን አስደናቂ ውን የክርስቶስ ሰላም ያልተለማመዱ ሰዎች ሊረዱት አይችሉም።

በእሥር ቤቱ የብረት አጥሮች ውስጥ አፌን አሾለኩና—"ቫሪያ ስላደረግሽው አይጸጽትሽም?" በማለት ጠየቅኋት "በፍጹም ስለ ክርስ ቶስ ፍቅር ከመናገር ወደ ኋላ አልልም፤ ስለ እርሱም ይህን መከራ ለመቀበል በመታደሌ ደስ ይለኛል" የሚል ነበር የሰጠችኝ መልስ።

ልብሶቿንና ያሉዋትን ነገሮች ሁሉ ወስደውባታል፤ የቀራት ነገር በውስጥዋ ያለው ነገር ብቻ ነው። ምንም ዘመድ የላትም፤ በጣም ለሚያስፈልጉዋት ነገሮች አንዳንድ እርዳታ ልናደርግላት ይገባል ምናልባ ትም ወደ ሳይቤሪያ ሳይወስዱዋት አይቀሩም። ፀልዩ።

ያንቺው ማሪያ

# አራተኛ ደብዳቤ

"ውድ እህቴ ማሪያ—ካምፓችን ከከተማው አሥር ማይሎች ያህል ወጣ ይላል። በሰላም ደርሰናል ስላለንበት ሁኔታ ልንገልጽልሽ አልች ልም። ስለ ጤንነቴ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። አንዲት ክርስቲያን እህት ጋር አብረን እንሠራለን፤ ጤንነትዋ ከከባድ ሥራ የተነሣ ተጎድ ቷል። የእኔን ሥራ ከጨረስሁ በኋላ እንደገና እርስዋን እረዳታለሁ። ከአሥራ ሁለት እስከ አሥራ ሶስት ሰዓቶች ያህል ያሰሩናል። በዚህ ላይ በቂ ምግብ የለንም።

ባንቺ በኩል የደኅንነትን መንገድ ስላመለከተኝ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። ለማን እንደምሰቃይም አውቃለሁ። ለመሆኑ፣ ከክርስቶስ ፍቅር ሊለየን የሚችል ማነው…? በየጊዜው ስለጌታ እመሰክራለሁ። እኔን ፀጥ ያሰኙ እየመሰላቸው ተጨማሪ የሥራ ጫና ይጭኑብኛል። ወደ ካምፑ

ስንሄድ ብዙ ወንድሞችና እህቶች አግኝተናል። ወንድሞችና እህቶችን ስናገኝ መንፈስ ቅዱስ ራሱ የእግዚአብሔር ልጆች መሆናቸውን ይመሰክ ርልናል። በባቡር ጣቢያው አንዲት ሴት ምግብ ሰጠችን፤ ሶስት ቃላት ብቻ ነው የተናገረችው— "እግዚአብሔር ሕያው ነው!" በማለት። እሥረኞቹ ከግማሽ በላይ ክርስቲያኖች ናቸው። አሥራ ዘጠነኛ ዓመቴን

ለመጀመሪያ ጊዜ እሥር ቤት ላከብር ነው። ለሌሎች ክርስቲያኖች በሙሉ ሰላም በይልኝ ዕብራውያን 12፡1—3 አንብቢ። እዚያ ያሉ ክርስቲያኖች ሁሉ ሰላም ይሉሻል።

ያንቺው ቫሪያ

# አምስተኛ ደብዳቤ

በእግዚአብሔር ፀጋ እኔና ክርስቲያን እህቴ ደኅና ነን "ወደ.... ወስደውናል። የላክሽልንንም ተቀብለናል፤ በተለይም መጽሐፍ ቅዱስን በታላቅ ደስታ ነበር የተቀበልነው። ስለ ትብብራቸው ሌሎች ክርስቲያኖ ችንም ሁሉ አመስግኚልን።

እግዚአብሔር ጥልቅ ፍቅሩን ስለ ገለጠልኝ በጣም ደስተኛ ነኝ። የሚደርስብኝንም መከራ እንደ ልዩ ፀጋ ነው የምቆጥረው፤ እስከ መጨረሻው በእምነት እንድንፀና ፀልዩልን። ስለ እኛ አትጨነቁ በሰማ ያት የሚጠብቀን ዋጋ ከፍተኛ ነው። ማቴዎስ5፡11—12

ያንቺው ቫሪያ

ይህ ቫሪያ የተባለች ልጃገረድ በክርስቶስ በማመንዋ ከታሠረች በኋላ የፃፈችው የመጨረሻ ደብዳቤዋ ነው።

ከዚህ በኋላ ግን አልፃፈችም በምን ሁኔታ ላይ እንዳለችም ማንም አያውቅም።